
# ስምዓ፡ጽድቅ፡
# ብሔራዊ።

# ስምዓ፡ጽድቅ፤
# ብሔራዊ።

ብጥንታውያን ፡ የኦርቶዶክስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መምህራን ፡ ፍለጋ ።




ከመሠረት ፡ ስብሐት ፡ ለአብ ፡

አዲስ ፡ አበባ ፤ ፲፱፻፺፩ ፡ ዓ ፡ ም ።
አርቲስቲክ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ።
1628

Reprinted 1992
by
Mekane Yesus Seminary
Cultural Department

ያለ፡ደራሲው፡ፈቃድ፡ማሳተም፡ክልክል፡ነው።



ጌታውን፡፫፡ጊዜ፡የካደው፡ጴጥሮስ፡ዶሮ፡ሲጮህ፡ስሕተቱን፡
አስቦ፡ስለማልቀሱ።

ትብል፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ኢታርኅቀኒ፡እግዚኦ፡
እምትእዛዝከ፤ወኢይኩን፡ከመ፡ሰቃልያን፡እለ፡
ከዐዉ፡ደመከ፡ዲበ፡ዕፀ፡መስቀል፡አላ፡ረስየኒ፡
እትቀነይ፡ለከ፡ለዘበእንቲአነ፡ዲበ፡ዕፀ፡ተሰቀልከ።

## መቅድም ።

ከፀሐይ ፡ በታች ፡ ለሚኖር ፡ ሰው ፡ የማድረግ ፡ ምክንያትና ፡ መነሻ ፡ የሚሆኑ ፡ ነገሮች ፡ እፊቱ ፡ ባይዘረጉና ፡ ባያጋጥሙት ፡ ኖሮ ፡ አንድን ፡ ነገር ፡ ለማድረግ ፡ ይችል ፡ እንዳልነበረና ፤ አሁን ፡ በዓለም ፡ ያሉት ፡ መንፈሳውያን ፡ ወይም ፡ ሥጋውያን ፡ የሰው ፡ ድርጊቶች ፡ ወደ ፡ መታየት ፡ ሳይደርሱ ፡ ይቀሩ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ጥርጥር ፡ የለውም ።

ይህና ፡ ይህ ፡ ቢደረግ፡ ይሻላል ፡ እንዲህና ፡ እንዲህ ፡ ቢሆን ፡ አስፈላጊ ፡ ወይም ፡ ተገቢ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ እንደዚህ ፡ ቢሆን ፡ ምንኛ ፡ መልካም ፡ ኖሮአል ! የሚል ፡ አገባብና፡ ፍላጎት ፡ ምኞትም ፡ በሰው ፡ ልብ ፡ እንዲፈጠር ፡ ምክንያት ፡ ወይም ፡ መነሻ ፡ ስላለ ፤ ሲጀመር ፡ ጀምሮ ፡ የፀሐይ ፡ ትኩሳትና ፡ ብርድ ፡ ዝናምም ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ በጥቃት ፡ ረገድ ፡ ባጋጠሙት ፡ ጊዜ ፡ መጠለያ ፡ መከለያ ፡ የሚሆኑትን ፡ ቤት ፡ ልብስ ፡ መሥራቱን ፤ እስከ ፡ አሁን ፡ ድረስም ፡ ለመከላከያና፡ ለጥቅም ፡ ለምቾትም ፡ ሲደክም ፡ መኖሩን ፤ በሥራውና ፡ በድካሙ ፡ መጠንም ፡ መንፈሳውያንን ፡ ሥጋውያንን ፡ ድርጊቶች ፡ እያበረከተ ፡ መሄዱን ፤ ማንም ፡ የሚያውቀው ፡ ነው ።

ከእነዚሁ ፡ ድርጊቶችም ፡ አንዱ፡ የሥነ ፡ ጽሑፍ፡ ነገር ፡ መሆኑ፡ ሲታወስ ፤ መጽሐፍንም ፡ ለማዘጋጀት ፡ መነሻና ፡ ምክንያት ፡ አለ ። ይኸውም ፡ «የጽሑፍ ፡ ብዛት ፡ መንፈሱንና ፡ አእምሮውን ፡ ያንፅለት ፡ ዘንድ ፡ አስፈላጊ ፡ የሚሆነው ፡ በጕድለቱ ፡ ብዛት ፡ ለሚሰናከል ፡ ሰው ፡ ነው ፤» ቢባል ፡ እንኳ ፡ የዓለም ፡ ሁናቴ ፡ እንደ ፡ መለዋወጡ ፡ መጠን ፡ በየጊዜው ፡ ለየጊዜያቱ ፡ ተስማሚን ፡ መንገድ ፡ መፈለግ ፡ መንሥኤ ፡ እየሆነ ፡ የመጻሕፍትን ፡ ዐይነቶች ፡ እንዳበዛ ፡ የሚረሳ ፡ እንዳይደለ ፤ በዘመናቱ ፡ ሁሉ ፡ በቂ ፡ ማስረጃነቱን ፡ ጠብቆ ፡ በመታየት ፡ ላይ ፡ የሚገኝ ፡ ነው ።

ይህ ፡ ስምዓ፡ ጽድቅ ፡ የተባለው፡ መጽሐፍም ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ይጻፍ ፡ ዘንድ ፡ ያስፈለገበት ፡ ምክንያት ፡ በምኞት ፡ የሚጠብቁት ፡ ተግባሮች ፡ ሥራንም ፡ የሚጠይቁ ፡ ክንውኖች ፡ እፊቱ ፡ ስላሉ ፡ ነውና ፤ የተባሉት ፡ ጉዳዮች ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ተጽፈው ፡ ሲገኙ ፡ አንባቢው ፡

"እስመ ፡ መፍቅደ ፡ ግብር ፡ ያበጽሕ ፡ ለአጽሕፎ፡" ያለውን ፡ የሊቁን ፡ የአፈ ፡ ወርቅን ፡ ቃል ፡ እያሰላሰለ ፡ እንደሚያስብባቸው ፡ ተስፋ ፡ ከማድረግ ፡ አንገታም ።

ሀ/ እነሆ ፡ ዛሬ ፡ ሰው ፡ በደረሰበት፡ ጥበብና ፡ ዕውቀት ፡ አንዱ ፡ ክፍለ ፡ ዓለም ፡ ከሌላው ፡ ክፍለ ፡ ዓለም ፡ መንግሥትም ፡ ከሌላው ፡ መንግሥት ፡ ጋር ፡ ወዳጅነትን ፡ እያጸና ፡ ኅብረትንና ፡ መገባባትን ፡ ለማድረግ ፡ ሲጣጣር ፡ ተራርቀው ፡ የኖሩት ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናትም ፡ በየበኩላቸው ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ በመተዋወቅ ፡ ተግባራቸውን ፡ ቀጥለዋል ። ይህም ፡ በመሆኑ ፡ አንዱ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከሌላው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን፡ እንዴት፡ እንደሚመሳሰል፡ወይም፡ እንዴት፡ እንደሚለያይ፡ ባዕድነቱ፡ ሩቅነቱ ፡ ቅርብነቱስ፡ እምን፡ ድረስ፡ እንደ ፡ ሆነ፡ ማጥናት ፡ የእያንዳንዱ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጉዳይ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ። በዚህም ፡ ጊዜ፡ የሚፈለገው ፡ አንዱ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሌላውን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዶክትሪን ፡ (የሃይማኖትን ፡ መሠረት ፡) በቀላሉ ፡ ለማጥናት ፡ እንዲችል ፡ በአንድ ፡ ምዕላድ ፡ ተሰናድቶ ፡ ሲገኝለት፡ በመሆኑ ፡ ያኛው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ማዘጋጀት ፡ እንደሚኖርበት ፡ ልክ ፤ ይህኛው ፡ ደግሞ፡ የሃይማኖቱን ፡ መሠረት ፡ በአንድ ፡ ምዕላድ፡ አዘጋጅቶ፡ ይገኝ ፡ ዘንድ ፡ አገባብ ፡ ከመሆኑ ፡ በላይ ፡ "ሰዎች ፡ ሊያደርጉላችሁ ፡ የምትወዱትን ፡ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ እንዲሁ፡ አድርጉላቸው ።" ለሚለው ፡ ቃል ፡ አድራጊው ፡ በሚሆንበት ፡ ጊዜ ፡ ፈጻሚነቱን ፡ ያረጋግጣል ። (ማቴ ፡ ፯ ፡ ፲፪ ፡) ስለሆነም ፡ ይኸው ፡ ሁናቴ ፡ ሠራተኛን ፡ ለከንቱ ፡ ያስነሣ ፡ ዘንድ ፡ የሚያባብል ፡ መነሻ ፡ መሆኑን ፡ እንጅ ፡ በንግግር ፡ ብቻ ፡ አለመፈጸሙንና ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ በመጠበቅ ፡ መቈየቱን ፡ እየጠየቀ ፡ መታየቱ ፡ ኀሳብን ፡ የማያስጥል ፡ ተግባር ፡ ነው ።

ለ/ በሌላው ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ የሃይማኖቱ ፡ ሙቀት ፡ ያልቀዘቀዘበት ፡ ክርስቲያን ፡ ሁሉ፤ በጥንትዋ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን ፡ ሃይማኖት፡ መሠረት ፡ ምንና ፡ ምን ፡ መያዝ ፡ እንደሚገባው ፡ ከምንና ፡ ከምንስ ፡ መለየት ፡ እንዳለበት ፡ ለማወቅ ፡ ይችልበት ፡ ዘንድ ፤ እንደዚሁም ፡ ሁሉ ፡ ምናልባት ፡ አይቀርም ፡ ይሆናልና ፡ በያዘው ፡ እርምጃው ፡ ወይም ፡ በዓላማው ፡ ወይም ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያኑና ፡ በጥንታውያን ፡ መምህራኑ ፡ ታሪክ ፡ በትምህርታቸውም ፡ ከሌላ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለሚመጣበት ፡





ድንገተኛ ፡ ጥያቄ ፡ ጠንቅቆ ፡ መልስ ፡ ይሰጥበት ፡ ዘንድ ፤ በብሉይና ፡ በሐዲስ ፡ ኪዳን ፡ መሠረትነት ፡ በጥንታውያን ፡ ሊቃውንትም ፡ ማስረጃነት ፡ ተሰባቅለው ፡ የተስማሙ ፡ አንቀጾች ፡ ያሉት ፡ መጽሐፍ ፡ እንደሚያስፈልገው ፡ ግልጽ ፡ ነው ።

ስለዚህም ፡ መጽሐፉ ፡ ለዚህ ፡ ሁሉ ፡ እንዲጠቅም ፡ አብነቱ ፡ ከብሉይና ፡ ከሐዲስ ፡ ኪዳን ፡ ሆኖ ፡ በጥንታውያን ፡ የኦርቶዶክስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን፡ አባቶች፡ ጕዳና፡ ተያይዞና፡ ተጠናቅቆ ፡ ተጽፎአል ። የአጻጻፉ ፡ ጕዳናም ፡ በትምህርት ፡ አሰጣጥ ፡ ስልት ፡ እምብዛም ፡ ባይመሳሰል ፡ ሃይማኖተ ፡ አበውና ፡ አዕማደ ፡ ምሥጢር ፡ በተባሉ ፡ መጻሕፍት ፡ አያያዙ ፡ ተጀምሮ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ለአገራችን ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ ሊሆንባቸው ፡ አለመቻሉ ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

እንግዲህ ፡ ለመጻፍ ፡ ያነሣሣኝ ፡ ምክንያት ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባጭሩ ፡ እንደ ፡ ገለጽሁት ፡ ሲሆን ፡ በጽሑፉ ፡ ላይ ፡ ያለኝ ፡ ምኞትና ፡ ዓላማ ፡ ደግሞ ፡ ነፃነት ፡ ያገኘችው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያናችን ፡ በብሔራዊ ፡ አንድነት ፡ ቀዋሚውን ፡ ሃይማኖት ፡ ሳይሆን ፡ ያለኀሳብ ፡ የገባውን ፡ ልማድ ፡ እንድታሻሽልና ፡ ጥንታዊውን ፡ የሃይማኖት ፡ መሠረት ፡ ግልጽ ፡ አድርጋ ፡ በማስተማር ፡ እንድትታደስ ፡ ነው ።

እነሆ ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ በግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ አድሮ ፡ የመንግሥትንና፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ብርሃናዊ ፡ ነፃነት ፡ ካወጣልን ፡ ወዲህ ፡ ብዙ ፡ አስገራሚዎችን ፡ ሁኔታዎች ፡ አይተናል ። በተለይም ፡ መንግሥቱ ፡ በትምህርት ፡ ቤቶች ፡ በሚደረጉት ፡ የትምህርት ፡ አሰጣጥ፡ ዘዴዎች ፡ ምክንያት ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ አስደናቂዎች ፡ የሆኑትን ፡ ልዩ ፡ ልዩን ፡ ፕሮግራሞች ፡ በአጭር፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ በማከናወኑ፡ የዛሬዪቱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በደረሰችበት ፡ የዕውቀት ፡ ሁናቴ ፡ ደስ ፡ እንደሚለን ፡ ሁሉ ፤ ቤተ ፡ ክርስቲያንዋም፡ በበኩልዋ፡ የትምህርትዋን ፡ አሰጣጥ ፡ በተሻለ ፡ ዘዴ ፡ እንድታስፋፋ ፡ ሁላችን ፡ የምንመኘው ፡ ነገር ፡ ነው ። ምክንያቱም ፡ ይህን ፡ በመንግሥት ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ በሥጋዊ ፡ ዕውቀት ፡ የጐለመሰውን ፡ ትውልድ ፡ በልማድ ፡ የያዛቸውን ፡ እምነቶች ፡ የሚያስንቁትና ፡ እንዲያቃልላቸውም ፡ የሚያደርጉት ፡ አስተያየቶች ፡ ቶሎ ፡ ብለው ፡ እንደሚያጋጥሙት ፡ ልንዘነጋ ፡ የማይቻለን ፡ በመሆኑ ፡ ነው ። ስለ ፡

ሆነም ፡ በቂ ፡ ማስረጃን ፡ በመስጠት ፡ የክርስትናን ፡ እምነትና ፡ የክርስቲያንን ፡ ኑሮ ፡ ግልጽ ፡ አድርጎ ፡ ማስገንዘብ ፡ ያስፈልጋል ። ግን ፡ ይህ ፡ ሳይሆን ፡ ቀርቶ ፡ ያልተማሩና ፡ የክርስቲያንን ፡ ኑሮ ፡ በሙሉ ፡ ያላወቁ ፡ መሃይምናን ፡ እንደኖሩበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፤ እንዲያው ፡ በደፈናው ፡ "በልማደ ፡ ሀገር ፡ እምነት ፡ ኑር ፡" ቢሉት ፡ ልዩ ፡ ልዩን ፡ አስተያየቶች ፡ በመመርመር ፡ ለበሰለ ፡ አእምሮና ፡ ማናቸውንም ፡ ነገር ፡ ማመዛዘን፡ ልምድ፡ ላደረገ፡ ሕሊና፡ በጄ፡ ብሎ፡ መቀበል፡ መቼውንም፡ ቀንበሩ ፡ ነው ። ለዚያውስ ፡ ምን ፡ ችግር ! በክርስቲያኖች ፡ ይቅርና ፡ በአሕዛብ ፡ ስንኳ ፡ "እውነት ፡ አለው ፡" ተብሎ ፡ ከተመሰከረለት ፡ ከወንጌል ፡ ትምህርት ፡ የሚበልጥ ፡ አእምሮንና ፡ ሕሊናን ፡ የሚያረካ ፡ በቂ ፡ ማስረጃነት ፡ ያለው ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ አለመኖሩ ፡ ሲታወቅ ፡ ይህም ፡ ወንጌል ፡ የእኛ ፡ የእምነታችን ፡ መሠረት ፡ ሆኖ ፡ በእጃችን ፡ ሲገኝ ፡ እውነትን ፡ አጥርተን ፡ በቂ ፡ ማስረጃን ፡ እንዳንሰጥ ፡ የሚያስፈራን ፡ አንዳች ፡ ነገር ፡ እንደሌለ ፡ እናውቅ ፡ የለምን ? እንደማወቃችን ፡ መጠን ፡ ግን ፡ ቅብዓ ፡ ርኅራኄን ፡ ጨምረንበት ፡ በተከታዩ ፡ ጊዜ፡ የሚሠማራውን ፡ ወገናችንን ፡ በወንጌል ፡ እውነት ፡ ብናጽናናውና ፡ ተከታትሎ ፡ ከሚደርስበትም ፡ ፈተና ፡ ብንታደገው ፡ ጽድቅን ፡ የሚያውቅ ፡ አስተዋይ ፡ ትውልድ ፡ ስለሚሆንልን ፡ የእኛ ፡ አበባነት ፡ ሲረግፍ ፡ በሚተካው ፡ ንጹሕ ፡ ፍሬያችን ፡ የበለጠ ፡ ደስታ ፡ ሊኖር ፡ ይችላል ። ምሳ ፡ ፲፬ ፡ ፴፬ ።

ይኸውና ፡ በብሉይ ፡ ኪዳን ፡ ዘመን ፡ በኢያሱ ፡ ጊዜ ፡ የነበረ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አምላኩን ፡ የሚያውቅ ፡ ትውልድ ፡ ምድረ ፡ ከነዓንን፡ በርስትነት ፡ ሲወርስ ፡ ከኢያሱ ፡ በኋላ ፡ የተነሣው ፡ አምላኩን ፡ የማያውቅ ፡ ትውልድም ፡ በዙሪያው ፡ በነበሩት ፡ አሕዛብ ፡ ሲቀጠቀጥና ፡ ሲማረክ ፡ የመኖሩን ፡ ታሪክ ፡ ማየት ፡ ወይም ፡ ማስታወስ ፤ እግዚአብሔርን ፡ በማወቅና ፡ እግዚአብሔርን ፡ ባለማወቅ ፡ ባለው ፡ ልዩነት ፡ በአንዱ ፡ ትውልድ ፡ የሚገኘውን ፡ ደስታና ፡ በሌላው፡ ትውልድም ፡ የሚደርሰውን ፡ ችግር ፡ ለመመዘን ፡ ይቻልበታል ። (ኢያ፡ ፳፫ ፡ ፫-፳ ። መሳ ፡ ፪ ፡ ፲-፲፭ ።) "ለተከታዩ ፡ ትውልድ፡ መውደቁ ፡ ወይም ፡ መነሣቱ ፡ አሁን ፡ ባሉት ፡ መምህራን ፡ እጅ ፡ በመሆኑ ፡ የኃላፊነታቸው ፡ ሸክም ፡ እጅግ ፡ ከባድ ፡ ነው ።" ሲባል ፡ በየፊናው ፡ የምንሰማው ፡ ይህንኑ ፡ ማስረጃን ፡ በመመልከት ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ።





በእውነትም ፡ ስለ ፡ ራስ ፡ ከማሰብና ፡ ለተከታይ ፡ ትውልድም ፡ ልዩ ፡ ልዩን ፡ ጥቅም ፡ ከማዘጋጀት ፡ ከማከማቸትም ፡ በላይ ፡ "ብፁዕ ፡ ሕዝብ ፡ ዘእግዚአብሔር ፡ አምላኩ ፡" እንደ ፡ ተባለ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላኩ ፡ የሆነለት ፡ ሕዝብ ፡ ሊደነቅ ፡ የተገባው ፡ መሆኑን ፡ ተመስክሮለት ፡ እንደ ፡ ማስመከቱ ፡ መጠን ፤ ሠራዒ ፡ መጋቢ ፡ ረዳኢ ፡ ማሕየዊ ፡ የሆነውን ፡ እውነተኛውን ፡ አምላክ ፡ መያዝ ፡ ብልጫ ፡ ያለው ፡ ዐይነተኛ ፡ ጉዳይ ፡ ነውና ፤ ተከታዩን ፡ ትውልድ ፡ በእምነተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከማጽናት ፡ የተሻለ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ዕድገት ፡ ሌላ ፡ ጠቃሚ ፡ አገልግሎት ፡ የለም ፡ ቢባል ፡ እውነተኛ ፡ ነገር ፡ ነው ። (መዝ ፡ ፴፫፡፲፪።

እንግዲህ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያናችን ፡ ይህንኑ ፡ በማመዛዘን ፡ ለሕዝብዋ ፡ ብሔራዊን፡ የሃይማኖት፡ ትምህርት፡ እየፈረጁ ፡ በመስጠትዋ ፡ የምታከናውን ፡ ብትሆን ፤ በቅርቡ ፡ ባገኘችው ፡ ነፃነት ፡ መታደስዋን ፡ ልታስመሰክር ፡ ነፃ ፡ ባልነበረችበት ፡ ጊዜም ፡ ምን ፡ ያህሉን ፡ የምታከናውን ፡ እንደ ፡ ነበረች ፡ ልታስገምት ፡ ትችላለች ፡ ማለት ፡ ነው ። ግን ፡ ደግሞ ፡ ስለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን፡ መታደስ ፡ ስንናገር፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ በብዙዎች ፡ ዘንድ ፡ መታደስ ፡ የተባለው ፡ ቃል ፡ በሃይማኖት ፡ ላይ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ ወይም ፡ አዲስ ፡ ኀሳብ ፡ እንደማምጣት ፡ ስለሚገመት ፤ አንዳንዶቹም ፡ በቅርታ ፡ መንፈስ ፡ እየተመለከቱት ፡ ስለሚታይ ፤ ይህን ፡ ለማወቁ ፡ አስቸጋሪ ፡ ያልነበረውን ፡ ነገር ፡ እስቲ ፡ እንነጋገርበት !

በውኑ ፡ መታደስ ፡ ማለት ፡ ከልብ ፡ አፍልቆ ፡ አዲስን ፡ ነገር ፡ ወይም ፡ አዲስን ፡ ኀሳብ ፡ መፍጠር ፡ ማለት ፡ ይሆን ? አይደለም ፡ መታደስ ፡ ማለት፡ ጥንቱኑ ፡ ሊገለጽ ፡ ተገቢ፡ በሆነበት ፡ ጊዜ ፡ በአንድ ፡ ምክንያት ፡ ተሸፍኖ ፡ የኖረውን ፡ ነገር ፡ አሁን ፡ ግልጽ ፡ አድርጎ ፡ አብራርቶ ፡ ማሳየት ፡ ማለት ፡ መሆኑን ፡ በቃሉ ፡ ዐይነተኛ ፡ ፍቺ ፡ ማንም ፡ የሚያውቀው ፡ ነው ። ይህም ፡ ይታወቅ ፡ ዘንድ ፡ ሌላው ፡ ምሳሌ ፡ ይቈይና፤ ከአንድ ፡ ሺ ፡ ስድስት፡ መቶ፡ ዓመታት ፡ በላይ ፡ ከወገንዋ ፡ ጳጳስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ፡ ሳትሾም፡ ትኖር ፡ የነበረች ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዛሬ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ ከወገንዋ፡ ጳጳስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ መሾምዋንና ፡ መንፈሳዊ፡ ነፃነትዋን፡ ማግኘትዋ፡ "የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መታደስ ፡" እንደ ፡ ተባለ፡ ማስተዋል ፡

ነው ። እንግዲህ ፣ ይህች ፣ ቤተ ፣ ክርስቲያን ፣ መንፈሳውያን ፣ መሪዎ
ችዋን ፣ በራስዋ ፣ መብት ፣ ለመሾም ፣ የቻለችው ፣ በእኛ ፣ ዕድሜ ፣
ውስጥ፣ ሲሆን፣ ያን፣ ያህል፣ ዘመን ! መንፈሳዊ፣ ነፃነትዋን ፣ አሳጥቶአት፣
የነበረው ፣ ለሰው ፣ ፊት ፣ የማያደላ ፣ እግዚአብሔር ፣ በመከልከሉ ፣ ሳይ
ሆን ፣ የግብፅ ፣ ሰዎች፣—"ወሰብአ ፣ ኢትዮጵያ፣ ኢይሚሙ፣ ጳጳሰ ፣ እማ
እምራኒሆሙ ፣-" የሚለውን ፣ ቃል ፣ የሠለስቱ ፣ ምእት ፣ አስመስለው ፣
በፍትሐ ፣ ነገሥት ፣ ውስጥ ፣ አግብተው ፣ ጳፉና ፣ ያው ፣ በጊዜው ፣
ይዘላቸው ፣ የጭቆና ፣ ምክንያት ፣ ስለ ፣ ሆነ ፣ ነው ። ይህም ፣ በመጨ
ረሻው ፣ ድል ፣ የሆነው ፣ ሐሰተኛ ፣ ቃል ፣ ቅዱስ ፣ ጴጥሮስ ፣ ወደ ፣
ቆርነሌዎስ ፣ ቤት ፣ በገባ ፣ ጊዜ ፤ "አማን ፣ ርኢኩ ፣ ከመ ፣ ኢያደሉ ፣
እግዚአብሔር ፣ ለገጽ ፣ አላ ፣ በኵሉ ፣ አሕዛብ ፣ ዘይፈርሆ ፣ ወይገብር ፣
ጽድቀ ፣ ኅሩይ ፣ ውእቱ ። እግዚአብሔር ፣ ለሰው ፣ ፊት ፣ እንዳያደላ ፣
ነገር ፣ ግን ፣ በአሕዛብ ፣ ሁሉ ፣ እርሱን ፣ የሚፈራና ፣ ጽድቅን ፣ የሚያ
ደርግ ፣ በእርሱ ፣ የተወደደ ፣ ነው ።" ብሎ ፣ በመንፈስ ፣ ቅዱስ ፣ የተና
ገረውን ፣ ቃል፣ የሚቃወም፣ ከመሆኑም ፣ በላይ ፣ (የሐዋ ፣ ፲ ፣ ፴፬፣፴፭።)
ነፃ ፣ መሆን ፣ የሚገባትን ፣ ቤተ ፣ ክርስቲያን ፣ ጨቁኖ ፣ የወንጌል ፣
ሥራዋን ፣ በደንብ ፣ እንዳታካሂድ ፣ የሚያደናቅፍ ፣ የጨለማ ፣ ዕንቅ
ፋት ፣ ሆኖ ፣ መኖሩን ፣ ከቶ ፣ የማይረሳን ፣ ነው ።

ስለሆነም ፣ ለመታደስ ፣ ማስረጃ ፣ ብለን ፣ ከጠቀስነው ፣ የሚ
ያዘው ፣ ዋናው ፣ የነገሩ ፣ ፍሬ ፣ ኢትዮጵያ ፣ ክርስትናን ፣ እንደ ፣ ተቀበ
ለች ፣ ወዲያውኑ ፣ እጅ ፣ ልታደርገው ፣ ይገባት ፣ የነበረውን ፣ ከራስዋ ፣
የጳጳስን ፣ መሾም ፣ መብት ፣ በጭቆና ፣ ምክንያት ፣ ለብዙ ፣ ዘመናት ፣
ሳትይዘው ፣ ኖራ ፣ አሁን ፣ ግን ፣ በመታደስዋ፣ ተረጋግጦ ፣ የሚታየው ፣
የመብትዋን ፣ ሥልጣን ፣ መጨበጥ ፣ ዛሬ ፣ በልብ ፣ ወለድ ፣ የመጣ ፣
የኅሳብ ፣ ድርጊት ፣ ሳይሆን ፣ ከጥንቱ ፣ በእግዚአብሔር ፣ የተፈቀደ ፣
ነገር ፣ ሆኖ ፣ መኖሩን ፣ ነው ።

እንግዲህ ፣ የቤተ ፣ ክርስቲያን፣ መታደስ ፣ በአንድ ፣ በኵሉ ፣
በዚህ ፣ ማስረጃ ፣ እንዳየን ፤ እንደዚሁም ፣ ሁሉ ፣ በሌላም ፣ ወገን ፣
ሊብራሩ ፣ ሲገባቸው፣ በዘመን ፣ ብዛትና፣ በአገር ፣ ላይ ፣ በሚሆን ፣ ተለ
ዋዋጭ ፣ ሁናቴ ፣ በመንፈሳዊ ፣ ዕውቀት ፣ ማነስና ፣ በመናፍቃን ፣ ስሕ
ተቶች ፣ ምክንያት ፣ የተቀበሩና ፣ የተሸፈኑ ፣ ጥንታውያን ፣ የቤተ ፣ ክር





ስቲያን ፣ መምህራን ፣ ዋና ፣ ዓላማ ፣ አድርገው ፣ ሲሠሩባቸውና ፣ ሲያስ
ተምሩባቸው ፣ የኖሩ ፣ ብዙ ፣ ነገሮች ፣ እንዳሉ ፤ የአሁኖቹ ፣ ደጋጎች ፣
መምህራን ፣ ሁሉ ፣ የሚያውቁት ፣ ነገር ፣ ነው ። እንግዲያውማ ፣ ሰላ
ማዊ ፣ ጊዜን ፣ ባገኘንበት ፣ ዕድለኛ ፣ ሕይወታችን ፣ የተመለከቱትን ፣
ሁኔታዎች ፣ ከተሠወሩበት ፣ የጨለማ ፣ ስፍራ ፣ እያወጣን ፣ አብራርተን፣
ከመግለጽ ፣ የሚበልጥ ፣ አስደሳች ፣ ሥራ ፣ ምን ፣ ነገር ፣ ሊኖረን ፣
ይገባል ? (መክብ ፣ ፫ ፣ ፲፪ ።)

መቼም ፣ ቢሆን ፣ ማደስ ፣ ከዓለም ፣ ሥነ ፣ ተፈጥሮ ፣ የተነሣ ፣
እንሠራው ፣ ዘንድ ፣ አንደዬ ፣ የዘወትር፣ ግዳጃችን፣ ሆኖአልና ፤ ግር ፣
የምንሰኝበት ፣ አዲስ ፣ ነገር ፣ አይደለም ። ለምሳሌ ፣ ለማናቸውም ፣
ነገር ፣ ሁሉ ፣ መልኩ ፣ ጌጹ ፣ ሲሆን ፣ ጌጹ ፣ ደግሞ ፣ መጠኑና ፣ ልኩ ፣
ኅብሩም ፣ ነውና ፤ የእውነት ፣ ምሳሌ ፣ እንኳ ፣ ከዚህ ፣ የተነሣ ፣ ነው ፣
እንላለን ። ሆኖም፣ ብዙዎቹን፣ ተቃዋሚዎች ፣ ናቸው፣ በማለት ፣ ውሳኔ ፣
ባንሰጥም ፤ በዓለማችን ፣ ያሉትን ፣ የመልክን ፣ መጠንና ፣ ኅብርን ፣
የሚያደብዙ ፣ ወይም ፣ ፈጽመው ፣ የሚለውጡ ፣ በመሆናቸው ፣ ተቃራ
ኒነታቸውን፣የምናምን፣ በአንጻራቸው፣የተሰለፉ፣ ነገሮች፣ እምድር፣ላይ ፣
መኖራቸውን፣ እናያለን። እነዚያን፣ እነዚህን፣ የሚመለከት፣ ሰው፣ ግን ፤
የመልክን ፣ ልክ ፣ የሚያጠፉትን ፣ ሁሉ ፣ ዘወትር ፣ ሲያስወግዳቸው ፣
ይታያል ። እነሆ ፣ በብዙ ፣ ነገሮች ፣ ተዋድዶ ፣ የተቋቋመው ፣ ቤት ፣
እንደ ፣ መፍረስ ፣ ሲል ፣ ንቃቃቱን ፣ እንጠግናለን ፣ እንጅ ፣ ዝም ፣ ብለን፣
አንመለከተውም ። በማደግ ፣ ላይ ፣ ያለውን ፣ ጥፍራችንን ፣ ጠጉራችንን፣
ከመጠን ፣ በላይ ፣ ሆኖአል ፣ ብለን ፣ እንቈርጣለን ። "ቅድም ፣ ታጥበ
ናል ፣" ብለንም ፣ እጃችንን ፣ ወይም ፣ ገላችንን ፣ ሳንታጠብ ፣ አንቀ
ርም ። በአዲስነቱ ፣ የለበስነው ፣ ልብስም ፣ ሳያድፍ ፣ አለመቅረቱን ፣
ስናውቅ ፣ ለወደፊቱ ፣ መታጠብ ፣ እንደሚኖርበት ፣ እንገነዘባለን ።
ባጭሩም ፣ የመልክን ፣ መጠን ፣ ወይንም ፣ ኅብር ፣ ከሚያጠፉ፣ ተቃራኒ
ዎች ፣ ሁሉ ፣ ጋር ፣ እየታገለ ፣ ማስወገድ ፣ የነገርን ፣ መልክ ፣ መጠን ፣
ኅብርም ፣ መግለጽ ፣ ራሱ ፣ ሰው ፣ የሚሠራበት ፣ የሚኖርበት ፣ ዓለመ ፣
ተሐድሶ ፣ ነው ፣ ሊባል ፣ ይቻላል ።

የቤተ ፣ ክርስቲያን ፣ ሥነ ፣ መልክም ፣ የክርስቶስ ፣ ልክ ፣ ሲሆን፤
አናቅጸ ፣ሲኦል ፣ (የገሃነም ፣ ደጆች) ሊበራቱባት ፣ በእርስዋ ፣ ትይዩ ፣

ተከፍተው ፡ በሰልፍ ፡ ይታያሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ ሐዋርያ ፡ ጳውሎስ ፡ “እግዚአብሔር ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ አንዳንዶቹ ፡ ሐዋርያት ፡ ሌሎችም ፡ ነቢያት ፡ ሌሎችም ፡ ወንጌልን ፡ ሰባኪዎች ፡ ሌሎችም ፡ ጠባቂዎችና ፡ አስተማሪዎች ፡ እንዲሆኑ ፡ የሰጠበት ፡ ምክንያት ፤ ሁላችን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ልጅ ፡ በማመንና ፡ በማወቅ ፡ ወደሚገኝ ፡ አንድነት ፡ ሙሉ ፡ ሰውም ፡ ወደ ፡ መሆን ፡ የክርስቶስም ፡ ሙላቱ ፡ ወደሚሆን ፡ ወደ ፡ ሙላቱ ፡ ልክ ፡ እስክንደርስ ፡ ድረስ ፤ ቅዱሳን ፡ አገልግሎትን ፡ ለመሥራትና ፡ ለክርስቶስ ፡ አካል ፡ ሕንፃ ፡ ፍጹማን ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ ነው።” ሲል ፡ ያስረዳናል ። (ኤፌ ፡ ፬ ፡ ፲፩-፲፫ ።)

በሐዋርያው ፡ ቃልም ፡ ተዘርዝሮ ፡ እንደተመለከተው ፡ ከምዕመናን ፡ ተንጠባጥቦ ፡ ወደ፡ ሲኦል ፡ ደጃፍ ፡ እንዳይወድቅ ፡ በአንድ ፡ መንፈስ ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ሥጋ ፡ የቅዱሳንን ፡ አንድነት ፡ የሚያጸኑ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ስጦታዎች ፡ ያሉአቸው ፡ ሰዎች ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንዳሉአት ፡ ይታያል ። (ማቴ ፡ ፲፰ ፡ ፲፱ ።)

ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ሰብአዊ ፡ ኀሳብ ፡ ያልተቀላቀለበት ፡ ንጹሕ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ የሚሰማባት ፡ ወንጌልም ፡ ተጣርቶ ፡ የሚሰበክባት ፡ ምሥጢረ ፡ ጥምቀትና ፡ ምሥጢረ ፡ ቊርባንም ፡ በቀሳውስቱ ፡ የሚገለገሉባት ፡ መሥዋዕተ ፡ ስብሐትና ፡ ጸሎተ ፡ አኰቴት ፡ የሚያርግባት፡ ጉባኤ ፡ መንፈስ ፡ እንደ ፡ መሆንዋ ፤ አንድነትዋን ፡ የሚያጸኑ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ስጦታ ፡ ያላቸው ፡ ሰዎችዋን ፡ በውስጥዋ ፡ እንደ ፡ ያዘች ፡ በጠቅላላው ፡ ንጽሕትና ፡ ቅድስት ፡ ለመባል ፡ የበቃችው ፡ በደሙና ፡ በማየ ፡ ቃሉ ፡ መታጠብ ፡ መሆኑን ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የዘወትር ፡ አሳሳቢነት ፡ ስለምታውቅ ፡ አጥብቀው ፡ ከሚፈታተኑአት ፡ ከገሃነም ፡ ደጆች ፡ በምትጋደልበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ የምትከላከልበት ፡ ዋናው ፡ መሣሪያዋ ፡ ባመነችበት ፡ በእግዚአብሔር ፡ በጸጋ ፡ ቃሉና ፡ በተዋጀችበት ፡ ደሙ ፡ በመንጻትና ፡ በመታጠብ ፡ ነው ። (ኤፌ ፡ ፭ ፡ ፳፭-፳፯ ። የሐዋ ፡ ፳ ፡ ፳፰ ፡ ፴፪ ። ፩ ፡ ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፯-፱ ።)

እንግዲህ፡ በአንድ ፡ መንፈስ ፡ ወደ ፡ አንድ፡ ሥጋ፡ የቅዱሳንን ፡ አንድነት ፡ ማጽናት ፡ ከኖረ ፡ ዘንድ ፤ መንጻት ፡ መታጠብም ፡ ካለ ፡ ዘንድ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መታደስ ፡ አለመኖሩን ፡ የሚያምን ፡ ማነው ? የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መንጻት ፡ መታጠብስ ፡ በአንድ ፡ መንፈስ ፡





ሆኖ ፡ ስሕተትንና ፡ አሮጌ ፡ ልማድን ፡ ከማስወገድ ፡ ሌላ ፡ ፍቺው ፡ ምንድን ፡ ነው ? (ሮሜ ፡ ፲፪ ፡ ፩-፫ ።)

ይህን ፡ ሁሉ ፡ ማተታችን ፡ መምህራኑ ፡ የማያውቁት ፡ ሆነው ፡ እነእርሱን ፡ ለማስተማር ፡ አይደለም ። ነገር ፡ ግን ፡ የዚህን ፡ ኀሳብና ፡ ምሥጢር ፡ ቃለ ፡ መጻሕፍትን ፡ መመገብ ፡ የሚያዘወትሩ ፡ ሊቃውንት፡ እያወቁት ፡ ሳለ ፤ ብዛት ፡ ያላቸው ፡ መሃይምናን ፡ አያውቁትም ። አያውቁምና ፡ መምህራን ፡ ለማነፅ ፡ ጠቃሚ ፡ መሆኑን ፡ ተረድተው ፡ የሚደግፉትን ፡ “ለሕዝበ ፡ ክርስቲያንም ፡ ይረባል፡ ” ሲሉ ፡ የሚያቁዱትን ፡ ጥልቅ ፡ አስተያየት ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ትምህርት ፡ ያልጸና ፡ የመሃይምናኑ ፡ አእምሮ ፡ እንደማይደርስበት ፡ የታወቀ ፡ ቢሆንም ፤ (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፪ ፡ ፲፬ ።) መሃይምናኑ ፡ ራሳቸው ፡ ስለ ፡ ሃይማኖት ፡ ያላቸው፡ ዕውቀት ፡ ዝቅተኛ ፡ መሆኑን፡ መዝነው ፡ ስፍራውን ፡ ይለቅቁላቸው ፡ ዘንድ ፡ ተገቢ ፡ በሚሆንበት ፡ ፋንታ ፤ ሊቃውንቱን ፡ በመናፍቃን ፡ ስም ፡ ቀብተው ፡ “አብዝኆ ፡ መጻሕፍት ፡ ያዘነግዕ ፡ ልበ ።” የሚል ፡ የአረማዊውን ፡ የፊስጦስን ፡ ቃል ፡ እየጠቀሱ ፤ (የሐዋ ፡ ፳፮ ፡ ፳፬ ።) ወዲያውኑ ፡ እንደተለመደው ፡ በሠለስቱ ፡ ምእት ፡ ሊቃውንት ፡ ወንበር ፡ ላይ ፡ ተቀምጠው ፡ ሊፈርዱባቸው ፡ እንዳይቸኩሉና ፡ በዚሁ ፡ አስገራሚ ፡ አኳኋን ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንዋ ፡ መሻሻል፡ ዕድል፡ እንዳይሰበር ፡ አስጊ ፡ መሆኑን ፡ ብቻ ፡ ለማሳሰብ ፡ ነው ።

ይኸውም ፡ ማሻሻል ፡ ከመሻሻል ፡ ምንጭ ፡ የሚፈልቅ ፡ ነገር ፡ ስለሆነ ፡ ሰላማዊ ፡ ኅብረትን ፡ እያለመለመ ፡ ከማሳደጉ ፡ በቀር ፡ የአዋኪነትና ፡ የሞገደኝነት ፡ ባሕርይ ፡ እንደማይጠጋው ፡ ቢታወቅም ፤ እሬቱ ፡ የቆመው ፡ አለማሻሻል ፡ ግን ፡ ፀጥታን ፡ ነሺና ፡ የሁከት ፡ መነሻ ፡ በመሆኑ ፡ ከላይ ፡ ተሽቈልቍሎ ፡ የሚወርደውን ፡ የመንፈሳዊ ፡ ዕውቀትን ፡ ጐርፍ ፡ በገዛ ፡ ፈለጉ ፡ እንዳያልፍ ፡ ላለመጠቀም ፡ ይገድበው ፡ ዘንድ ፡ ተጋፍጦ ፡ እሬቱ ፡ ሲደቀንበት ፡ ከማየት ፡ ለአርቆ ፡ ተመልካች ፡ ሰብአዊ ፡ አእምሮ ፡ ሌላ ፡ የባሰ፡ አስጊ፡ ሁናቴ ፡ ይኖረዋል፡ እንደማይባል ፡ ቅን ፡ ኀሳብ ፡ ባለው ፡ ሁሉ ፡ ዘንድ፡ ተገምቶና ፡ ታውቆ፡ ያደረ ፡ ነው ። (ያዕ ፡ ፫ ፡ ፲፫-፲፰ ።)

ነገር ፡ ግን ፡ ለዚህ ፡ ሁሉ ፡ አብነቱ ፡ ቅድም ፡ እንዳልን ፡ በዓለማዊ ፡ ዕውቀት ፡ ለበሰሉ ፡ ተማሪዎች ፡ የመንፈስ ፡ ጥልቅ ፡ ትምህርት ፡

ካልተሰጣቸው ፡ አእምሮአቸው ፡ ሊረካ ፡ አለመቻሉን ፡ መገንዘብና ፤ ያልተማሩ ፡ መሃይምናን ፡ እንደኖሩበት ፡ ጊዜ ፡ እንዳይሆን ፡ ደርዝ ፡ ባለው ፡ የትምህርት ፡ አሰጣጥ፡ ዝግጅት ፡ የቤተ፡ ክርስቲያንዋ ፡ መታደስ ፡ አስፈላጊ ፡ ሲሆን ፤ በሌላው፡ በኩል ፡ ደግሞ፡ ዕንቅፋትን ፡ ለማስወገድ ፡ መምህራን ፡ የሆኑት ፡ ሁሉ ፡ ቀለል ፡ ባለው ፡ ትምህርት ፡ መሃይምናኑን፡ ማስረዳትና ፡ ቅንነት፡ እንዲኖራቸውም፡ መምከር ፡ ጠቃሚ ፡ ነገር ፡ ከመሆኑ ፡ በላይ ፡ ለደጉ ፡ አስተያየት ፡ መንገድ ፡ የሚጠርግለት ፡ ይሆናል ።

ዛሬ ፡ በመንግሥታችን ፡ ሰላማዊ ፡ አቀዋምና ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያናችን ፡ ነፃ ፡ መሆን ፡ የደረስንበትን ፡ ደረጃና ፡ ያለንበትን ፡ ሁናቴ ፡ በመገንዘብ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ሆነን ፡ ለማደስ ፡ ለማሻሻል ፡ መልካም ፡ ምኞት ፡ ቢኖረንም ፤ እግቡ ፡ ለማድረስ ፡ የሚያበረታታን ፡ ይሆናልና ፡ መለስ ፡ ብለን ፡ ባለመመልከት ፡ ባለፉት ፡ ጊዜያት ፡ የሚያሳፍር ፡ ነገር ፡ እንደነበረ ፡ መርሳትን ፡ አያስከትልብንም ።

ሌላውስ ፡ ይቅርና ፡ እስቲ ! ጥገኛ ፡ መሆን ፡ የሚገባቸው ፡ ሊያስጠጉ ፡ የሚችሉትን ፡ እናስጠጋችኋለን ፡ ሲሉ ፡ ሊያስጠጉ ፡ ችሎታ ፡ ያላቸው ፡ ደግሞ ፡ ጥገኛ ፡ ሊሆኑ ፡ ከሚገባቸው ፡ ጥገኞች ፡ ሆነው ፡ ሲኖሩ ፡ ምንም ፡ የማይታሰብበት ፡ ጊዜ ፡ መኖሩን ፡ እንዘነጋ ፡ ይሆን ? ይህን ፡ ጨለማ ፡ ላሳለፈ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይሁንና ፡ ዘወትር ፡ በነፃነት ፡ በምትኖረው ፡ የክርስቲያን ፡ መንግሥት ፡ ዛሬ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳቱ ፡ ጳጳሳቱም ፡ መብታቸውን ፡ ያገኙ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ተወላጆች ፡ ናቸው ። ስለዚህም ፡ ወደ ፡ ብዙዎቹ ፡ አህጉሮች ፡ ከመድረሱ ፡ በፊት ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ በኢትዮጵያ ፡ መኖሩ ፡ የታወቀውን ፡ ቅዱስ ፡ መጽሐፍን ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ጋር ፡ ተስማሚነት ፡ ካላቸው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ከሚገኙት ፡ የሊቃውንት ፡ መጻሕፍት ፡ እያደጋገፍን፡ ቤተ ፡ ክርስቲያናችንን፡ ያለአንዳች ፡ ጭቅጭቅ ፡ ሌሎች ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ወደ ፡ ደረሱበት ፡ የሥራ ፡ እርምጃ ፡ ማድረስ ፡ ከሕዝበ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በተለይም ፡ በቤተ ፡ ክህነት ፡ ትምህርት ፡ ካደግነው ፡ የሚፈለግብን ፡ ከባድ ፡ ኃላፊነት ፡ ነው ።

ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ምሥራውያን ፡ ምዕራባውያን ፡ እየተባባሉ ፡ ያለ ፡ ስሙ ፡ ስም ፡ ያለ ፡ መልኩ ፡ መልክ ፡ እየተሰጣጡ ፡ እርስ ፡ በርስ ፡





ከመፋጀት ፡ የታየው ፡ ውጤት ፡ የብዙ ፡ ሺ ፡ ነፍሳት ፡ እልቂት ፡ የብሔራዊ ፡ አንድነትም ፡ ኃይል ፡ መድከም ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ ራስን ፡ ጠቅሞ ፡ ለሌላው ፡ የመትረፍ ፡ ዋጋ ፡ እንዳልታየበት ፡ መገንዘብን ፡ ተቀዳሚ ፡ ተግባር ፡ አድርገን ፡ ለእንግዲሁ፡ እንዳይደገም፡ እንጣጣር ። ምሥራዊ ፡ ምዕራባዊ ፡ እየተባባሉ ፡ መነቃቀፍ ፡ እኮ ! ትምክህቱ ፡ በሰው ፡ አገር ፡ ከመሆኑ ፡ በላይ ፡ የትምክህቱ ፡ ውጤት ፡ የሆነው ፡ ጥላቻ ፡ ግን ፡ ለተወለዱባት ፡ አገር ፡ ከአእምሮ ፡ ጉድለት ፡ የተወነጨፈ ፡ የውርጅብኝ ፡ ጉዳት ፡ ነው ።

የዚሁ ፡ ጉዳት ፡ አመጣጥም ፡ መካከለኛውን ፡ ስፍራ ፡ ይዞ ፡ ለሚመለከት ፡ ሰው ፡ መነሻው ፡ ከምን፡ መሆኑን ፡ በሚያይበት፡ ቍጥር፡ የኀዘን ፡ ድንጋጤ ፡ እየወረረ ፡ ሲያቃትተው ፡ እንደሚገኝ ፡ በሌላ ፡ በኩል ፡ ሆነ ፡ በዚሁ ፡ መንገድ ፡ ሆነ ፡ የዚህን፡ ዐይነት ፡ ነገር፡ የተረዳ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በደረሰበት ፡ ጭንቀቱ ፡ መጠን ፡ ሳይረዳለት ፡ እንደማይቀር ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

ብቻ ፡ እንዳይደረግ ፡ እንመኛለን ፡ እንጅ ፡ ይህ ፡ ደካማው ፡ አስተያየት ፡ በግራም ፡ በቀኝም ፡ ኃይል ፡ የሚያገኝ ፡ ከሆነ ፤ መላውን ፡ የአንድ፡ አገርን ፡ ሕዝብ፡ አእምሮ ፡ ስለሚነካ ፡ ለተከበረችው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተመዛዛኝ ፡ የማይኖረው ፡ ትልቅ ፡ አሣር ፡ እንደሚሆን ፡ ማን ፡ ያጣዋል ? በዚያም ፡ ላይ ፡ በጠንካሮች ፡ ተራሮች ፡ ላይ ፡ ያለችው ፡ ኢትዮጵያ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ክንውን ፡ ያስገኘችው ፡ ያለእንከን ፡ የመሆን ፡ ገናና ፡ ብርሃንዋ ፡ በማንጸባረቅ ፡ እንዳይገለጽ ፡ በሙሴ ፡ መጠምጠሚያ፡ አምሳል ፡ ሸፍኖአት፡ የሚገኝ ፡ ይኸው፡ መነቃቀፍ ፡ እንዳይሆን፡ እጅጉን ፡ የሚያስፈራ ፡ ነው ። (፪ ፡ ቆሮ ፡ ፫ ፡ ፲፫ ፡ ፲፩ ። ማቴ ፡ ፭ ፡ ፲፬ ።)

በእውነቱም ፡ የብሔራዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ግላዊ ፡ ነፃ ፡ መብታችን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ የተሠራ ፡ መሆኑን ፡ ካወቅን ፡ በምሥር ፡ በብሔረ ፡ ምዕራብ ፡ ሥልጣንና ፡ ድርጅት ፡ ከምንመካ ፡ ይልቅ ፡ ከፍ ፡ ባሉት ፡ የሰላም ፡ ተራሮቻችን ፡ ላይ ፡ ወጥተን ፡ እንደ ፡ ደወል ፡ በጠራ ፡ ድምፅ ፡ ብሔራዊት ፡ ቀርነ፡ ሃይማኖታችንን፡ አሰምተን ፡ ከመናገር ፡ የሚያግደን ፡ ማን ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ? "ማን ፡ ሊሆን ፡ ይችላል፡" ማለቱም ፡ በፍቅር ፡ መንፈስ፡ ቁም ፡ ነገርን ፡ ስለምናስብ ፡ የተዝረከረከውን ፡ የሰይጣንን ፡ ነገር ፡ እንንቃለንና ፡ መቼውንም ፡

የእርሱን ፡ ሥራ ፡ አንሠራም ፤ ብዬ ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ ሁልጊዜ ፡ እውነትንና ፡ መልካምን ፡ ጥቅም ፡ በመቃወም ፡ ላይ ፡ የሚገኝ ፡ የቅንዓትና ፡ የምቀኝነት ፡ የተንኰልና ፡ የዕብሪት ፡ የትዕቢትና ፡ የመጥፎ ፡ ድፍረት ፡ የክፋትም ፡ ሁሉ ፡ መንፈስ ፡ በዓለማችን ፡ ውስጥ ፡ መኖሩን ፡ አልዘነጋሁም ። ይሁን ፡ እንጅ ፡ "ስለ ፡ ሃይማኖት ፡ ተቈርቋሪ ፡ ነኝ ፡" የሚል ፡ ሁሉ ፡ የገዛ ፡ ራሱ ፡ ከምን ፡ መንፈስ ፡ መሆኑን ፡ እንደማወቁ ፡ መጠን ፡ እነዚህን ፡ የሰይጣንን ፡ ሥራዎች ፡ እየተቃወመ ፡ መኖር ፡ እንደሚገባው ፡ መርሳት ፡ ስለሌለበት ፡ ዘወትር ፡ ይህን ፡ ከመሳሰለ ፡ ተግባር ፡ ሁሉ ፡ ገለልተኛ ፡ መሆን ፡ ይሰማዋል ። (ሉቃ ፡ ፱ ፤ ፶፩-፶፮ ። ፪ ፡ ጢሞ ፡ ፪ ፡ ፲፱ ።)

መሰማት ፡ ወይም ፡ ስሜት ፡ ግን ፡ ፈቅዶ ፡ ከመታዘዝ ፡ ጋር ፡ ሲተባበር ፡ ኃይል ፡ ያገኛል ፡ እንጅ ፡ ፈቅዶ ፡ በማይታዘዝ ፡ በሕሊና ፡ ገዳይ ፡ ፊት ፡ ብቻውን ፡ ቆሞ ፡ የመመከት ፡ ተግባር ፡ የለውምና ፡ ምን ፡ ጊዜም፡ ቢሆን ፡ ለዕርቅና ፡ ለአንድነት፡ አምላክ ፡ ባሕርይ፡ እንደማይበጀውና ፡ እንደማይስማማው ፡ ቢያውቅ ፡ እንኳ ፡ የጋፊኛ ፡ በልቡ ፡ ድፍረት ፡ "የምሠራው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ነው ፤" እያለ ፡ ቂምንና ፡ በቀልን ፡ ተጐንጭቶ ፡ ተከፍሎ ፡ በኃይሉ ፡ ሲመካ ፡ ተከፍሎም ፡ በነፃነቱ ፡ ሲኮራ ፡ የኃይልና ፡ የነፃነት ፡ ምንጭ ፡ የሆነውን ፡ መካከለኛውን፡ የአንድነት ፡ ስፍራ ፡ ባዶ፡ ወደ ፡ መሆን ፡ ሲያደርሰው ፡ የሚታየው ፡ ያው ፡ ቅን ፡ ስሜቱ ፡ የቀዘቀዘበት ፡ የዚሁ ፡ መንፈስ ፡ ሰው ፡ መሆኑ ፡ ነው ። (ምሳ ፡ ፲፰ ፡ ፩ ።)

ኃይልና ፡ ነፃነትም ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ሁሉ ፡ አስፈላጊዎችና ፡ ጠቃሚዎች ፡ ሆነው ፡ ሳለ ፡ ከመሥመራቸው ፡ ወይም ፡ ከመደባቸው ፡ እያወጡ ፡ አዙረው ፡ ለክፋት ፡ መሣሪያዎች ፡ ቢያደርጉአቸው ፡ አንድነትን ፡ የሚያፈርሱ ፡ የሥራ ፡ ፍሬያቸው፡ ያልተባረከ፡ ሊሆኑ ፡ ይችላሉ።

ስለዚህም ፡ ኃይል ፡ የሚሰማው ፡ ክፍል ፡-በእልከኝነት ፡ ወይም፡ በስሕተት ፡ በተመሠረተው ፡ እምነት ፡ መካከልና ፡ እንደ ፡ አዳም ፡ ኃጢአት ፡ በዘር ፡ በሚወረስ ፡ እምነት ፡ ሳይሆን ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጸጋ ፡ ወንጌልን ፡ ተምረን ፡ በምናገኘው ፡ በእውነተኛዋ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ልዩነት ፡ አስቀድሞ ፡ ባለማወቁ ፤ ሁለተኛም ፡ ይህችኛዋ ፡ ወንጌልን ፡ ተቀብላ ፡ ያመነችው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲ





ያን ፡ በመጀመሪያዎቹ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ዓመታት፡ ውስጥ ፡ በልብዋ ፡ ያለውን ፡ የእምነት ፡ ሁናቴ ፡ ለማስለወጥ ፡ ያለዚያም ፡ ድራሽዋን ፡ ለማጥፋት ፡ በአሕዛብ ፡ መንግሥታት ፡ ጽኑ ፡ ሥቃይ ፡ እንደ ፡ ተፈተነች ፤ ቢሆንም ፡ በእግዚአብሔር፡ ጸጋ ፡ በልብዋ፡ የተሠራው፡ እምነት፡ ሊለወጥ ፡ አለመቻሉን፡ እስከ ፡ ሞት፡ ድረስ ፡ በታመኑ ፡ ሰማዕታትዋ ፡ እንዳስመሰከረች ፤ ራስዋ ፡ ባለመጥፋትዋና ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ በመኖርዋ፡ ከነአካቴውም ፡ በብዙ ፡ ታላላቅ፡ መንግሥታት ፡ እየሰፈነች ፡ እየተዘረጋች ፡ በመሄድዋ ፡ ዘላቂ ፡ መሆንዋን ፡ የሚያረጋግጥ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ማስረጃ ፡ እንዳላት ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ታሪክ ፡ ባለመረዳቱ ፤ ከልብ ፡ ተረጋግጦ ፡ የታመነበትን ፡ ጽኑ ፡ እምነት ፡ በኃይልና ፡ በብርታት ፡ ሊያስለውጥ ፡ ሲነሣ ፡ ወድዶ ፡ መታዘዝ ፡ ባሕርዩ ፡ የሆነውን ፡ የሰውን ፡ ፈቃድ ፡ ደረቅ ፡ ዕንጨት ፡ ይመስል ፡ በተቻለ ፡ ሥልጣን ፡ ሊሰብርና ፡ ሊቀለጥም ፡ ሲጣጣር ፡ የመሰብሰብ ፡ ኀሳቡ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ መበተንን ፡ ሲያስከትልበት ፡ ታይቶአል ። ኢዮ ፡ ፲፫ ፡ ፯-፲፪ ።

ሌላው ፡ ደግሞ ፡ እኛ ፡ በጥንታዊትዋ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እምነት ፡ መሠረት ፡ ማመናችን ፡ ከታመነ ፡ ፈጣሪ ፡ የተያያዘ ፡ ነው ፡ እንጅ፤ ነፋስን ፡ ተቈራኝቶ ፡ የሚከተል ፡ አይደለምና ፡ ከእውነተኛው ፡ መለኮታዊ ፡ ምንጭ ፡ ካልፈለቀ ፡ እምነትና ፡ ተስፋ ፡ በቀር ፡ "መስሎኛል፡ " በማለት ፡ ሃይማኖታውያን ፡ ሆነን ፡ ለመኖር ፡ አንፈልግምና ፡ ስንል ፡ ዱሮ ፡ የጣልነውን ፡ "መሰለኝ፡ " የሚሉትን ፡ የሰው ፡ ሠራሹን ፡ እምነት ፡ ይዞ ፡ ከቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አንድነት ፡ ውጭ ፡ በገለልተኝነት ፡ ለመኖር ፡ ይፈልጋል ። ይህም ፡ ክፍል ፡-ለሕይወት ፡ ተስፋና ፡ ለሰው ፡ ደኅንነት ፡ በወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ምስክርነቱ ፡ ዕሙን ፡ የሆነውን ፡ ሃይማኖት ፡ ትቶ ፡ ውል ፡ በሌለውና ፡ የእምነት ፡ ቃል ፡ ሊሆን ፡ በማይገባ ፡ "በመሰለኝ፡ " አምኖ ፡ ስድ ፡ ተለቅቆ ፡ መኖርን ፡ ሲሻ ፡ ራሱ ፡ ይህ ፡ ስሕተቱ ፡ ቅጣት ፡ ሆኖበት ፡ የሕሊናን ፡ ዘለፋ ፡ ለጣሰ ፡ ሰው ፡ በመጀመሪያ ፡ የሚሰጠውን ፡ መቅሰፍት ፡ ተሸክሞ ፡ ይገኛል ። (፪ ፡ ተሰ ፡ ፪ ፡ ፲-፲፪ ። ሮሜ ፡ ፩ ፡ ፳፬ ።)

እንግዲህ ፡ ጠቃሚዎቹ ፡ ኃይልና ፡ ነፃነት ፡ ከመሥመራቸው ፡ ቢወጡ ፡ ጉዳትን ፡ ማስከተላቸው ፡ በዚህ ፡ ለመረዳት ፡ ይቻላል ።

በውኑ ! ኃይልስ ፡ ቢኖር ፡ ስለ ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ ክፉን ፡ ነገር፡ ማድረግ ፡ ይገባልን ? ነፃነት ፡ ቢገኝስ ፡ ራስን ፡ በስሕተት ፡ ጐዳና ፡ አስማርቶ ፡ የአንድነትን፡ ኃይል፡ ማፈራረስ፡ ጥቅም፡ ያመጣልን? "ሰንበት ፡ ስንኳ ፡ ለሰው ፡ ተፈጠረች ፡ እንጅ ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ሰንበት ፡ አልተፈጠረም፡ " የሚለውን ፡ የጌታችንን ፡ ቃል ፡ አንብበን ፡ ወይም ፡ ሰምተን ፡ እንሆን ! (ማር ፡ ፪ ፡ ፳፯ ።)

በዚሁ ፡ ረጅምና ፡ ዝርግ ፡ በሆነው ፡ በዓለም ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ትንሹን ፡ ትልቅ ፡ ትልቅንም ፡ ትንሽ ፡ የማድረግ ፡ ጉዳይ ፡ በፈጣሪ ፡ እጅ ፡ መሆኑን ፡ ባይካድ ፡ እንኳን ፤ ትንሹ :-«ትልቅ ፡ የመሆን ፡ ዕድል ፡ ሳይገጥመኝ ፡ አይቀርም ፡» ብሎ ፡ ከማኅበራዊ ፡ ኃይል ፡ ቢነጠል ፡ አይቈጨውም ፡ ይሆናል ። ትልቅ ፡ የሆነውም :-«መቼውንም ፡ አላንስ ! ሲል ፡ ከንዑሳን ፡ የአንድነት፡ ችሎታ፡ ቢለይ ፡ አያሳዝነውም፡ ይሆናል። የሁለቱ ፡ ተባህትዎ ፡ ግን ፡ ለጊዜው ፡ ፈጥሮት ፡ የሚታየው ፡ ዓይኑ ፡ እንደ ፡ ታወረው ፡ ሶምሶን ፡ ሁሉ ፡ ትልቅና ፡ ትንሽ ፡ ድንጋይ ፡ ተዋድዶ ፡ የተቋቋመበትን ፡ የሰላምን ፡ ምሰሶ ፡ ሲነቅልና ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ንዶ ፡ ሲከምር ፡ ነው ፡ እንጅ ፤ የመጭውን ፡ ጊዜ ፡ ዕድል ፡ ለየትኛው ፡ ወገን ፡ እንደሚሆን ፡ በግምት ፡ እንኳ ፡ አቅጣጫውን ፡ ሲያመለክት ፡ አይገኝም ። (ኤር ፡ ፳ ፡ ፬ ፡ ፳ ። መሳፍ ፡ ፲፮ ፡ ፳፱ ፡ ፴ ።)

ይህም ፡ ሁሉ ፡ ከታሰበበት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቀስቃሽነት ፡ የቆመ ፡ የሕሊና ፡ ዘለፋ ፡ መሆኑ ፡ ነውና ፤ እርሱን ፡ ዳምጦ ፡ ለመሄድ ፡ መሞከር ፡ ልክ ፡ በተሳለ ፡ ብረት ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ መርገጥ ፡ ይሆናል ። እንግዲህ፡ በዚያም፡ በዚህም፡ ብሎ ፡ ቅሬታው፡ ከልብ፡ የማይጠፋውን ፡ የብሔራዊ ፡ አንድነትን ፡ ነገር ፡ ለማጽናት ፡ የኃይል ፡ ቁጣንና፡ ችኮ ፡ ጠባይን ፡ እየቀነሱ ፡ መሻትን ፡ በመግዛት ፡ አርቆም ፡ በመመልከት ፡ ደኅናው፡ ጊዜ ፡ እንዳይጠፋብን፡ ከዚሁ፡ እንቅልፍ፡ መንቃት፡ አስፈላጊያችን ፡ መሆኑ ፡ አልቀረም ። በእውነቱም ፡ የማይቀር ፡ ነገር ፡ ነውና ፡ እኔም ፡ በበኩሌ፡ የአገሬን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መታደስ ፡ የምወድ ፡ ከመሆኔ ፡ የተነሣ ፡ በመከፋፈልና ፡ በመለያየት ፡ መከራከርንና ፡ መንቃቀፍን ፡ እንጅ ፤ ዕርቅና ፡ ሰላም ፡ አለመኖሩን ፡ በመረዳቴ ፡ ብቻ ፡ ወደዚሁ ፡ የኀሳብ ፡ ዓላማ ፡ እንደ ፡ ተመራሁ ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ቢያውቅልኝ ፡ እወዳለሁ ። (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፩ ፡ ፲-፲፫ ። ም ፡ ፫ ፡ ፩-፱ ። )





ስለዚህም ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘመደ ፡ ክህነት ፡ በመሆኔ ፡ ከዚያው ፡ ዘንድ ፡ በብዙ ፡ ልፋት ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያንዋ ፡ ትምህርትና ፡ ተግሣጽ ፡ በማደጌና ፡ በብሔራዊ ፡ መብቴ ፡ የሚነካኝን ፡ ነገር ፡ ተገንዝቤ ፡ ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ ብጽፍ ፡ ቀዋሚውን ፡ ሃይማኖት ፡ ሳይሆን ፡ አንዳንድን ፡ ነገር ፡ በማሻሻል ፡ ለማደስ ፡ ከማስገንዘብ ፡ በቀር ፡ ራሴን ፡ ጠቅሜ ፡ ሌላውን ፡ ለመጕዳት ፡ የታሰበ ፡ ነገር ፡ የሌለበት ፡ መሆኑን ፡ አረጋግጣለሁ ። (፪ ፡ ቆሮ ፡ ፩ ፡ ፳፬ ። )

እንደዚሁም ፡ ለማንም ፡ ቢሆን ፡ አስተያየቴን ፡ መዝኖ ፡ በመደገፍ ፡ በገዛ ፡ ፈቃዱ ፡ እንዲያጸናው ፡ ወይም ፡ እንዲያጸድቀው ፡ ከምመኘለት ፡ በቀር ፡ "መሆን ፡ አለበት ፡" በሚል ፡ ስሜት ፡ በማንም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ክብር ፡ ላይ ፡ አለመነሣቴንና ፡ የማልደርስ ፡ መሆኔን ፡ ተመልካች ፡ ሁሉ ፡ ይወቅ ፤ ይህ ፡ ሳይቀር ፡ የነገሩ ፡ ቅንነት ፡ በብዙ ፡ ጥናትና ፡ ሐተታ ፡ ከጸሎት ፡ ጋር ፡ አመዛዝኘው ፡ ልክና ፡ እውነት ፡ ሆኖ ፡ ያገኘሁትን ፡ ግን ፡ መሠወሩን ፡ አልሻም ።

እርግጥ ፡ ነው፡ አእምሮውን ፡ ለመግዛት ፡ የሚችል ፡ ሰው ፡ ለመታወቁ ፡ አይቸገርበትምና ፤ እንደ ፡ ዕውቀቱ ፡ መጠን ፡ ራሱን ፡ ጠብቆ ፡ ከነገሩም ፡ ሁሉ ፡ ዝም ፡ በማለትና ፡ በአርምሞ ፡ ለመኖር ፡ በእውነቱ ፡ የሚቻለው ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ይህንም ፡ በአንድ ፡ ወገኑ፡ ሲመለከቱት ፡ የማይቻል ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ። ማለት ፡ በራስ ፡ ይሁን ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ የሰው ፡ አርቆ ፡ ተመልካችነት ፡ ዘንድ ፡ ጠቃሚነቱ ፡ ለእግዚአብሔርና ፡ ለወገን ፡ መሆኑን ፡ በእውነትና ፡ በትክክል፡ ፍርድ ፡ መዝነው ፡ ያስተዋሉትን ፡ ነገር ፡ ቢደብቁት ፤ የጊዜውን ፡ ልሳንና ፡ የባለጊዜውን ፡ ድምፅ ፡ ብልጫ ፡ በሚለኩበት ፡ የአእምሮ ፡ ሚዛን፡ ሲታይ ፡ በአንጻሩ ፡ ያለው፡ "አውቆ ፡ ለሚያጠፋ ፡ ሎሌ፡ በዕውቀቱ ፡ ብዛት ፡ ልክ ፡ የሚቀጣ ፡ ፈራጅ ፡ አምላክ ፡" ከሁሉ ፡ የሚበልጥ ፡ ከባድና ፡ ባለግርማ ፡ ሆኖ ፡ በመገኘቱ ፡ እጅጉን ፡ ያስፈራል ፡ ማለት ፡ ነው ። ከዚሁም ፡ ጋር ፡ ከልብ ፡ ለሚወዱት ፡ ወገንና ፡ ለሚያፈቅሩት ፡ ሕዝብ ፡ በተቻለ ፡ ዕውቀት ፡ መጠን ፡ ለመግለጽ ፡ ከማሰብ ፡ ያነሰ ፡ አገልግሎት ፡ ያለ ፡ አይመስልምና ፡ አያስችልም ።

እንኪያስ ፡ የዓቅሜን ፡ ጽፌ፡ ለማበርከት ፡ የቃጣሁ ፡ ይህንኑ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ነው ። በቅንነት ፡ የተሠራ ፡ ሁሉ ፡ ለቅኖች ፡

ብቻ ፡ በመሆኑ ፡ በዚሁ ፡ መጽሐፍ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ ያስተውሉ ፡ ዘንድ፡ እግዚአብሔር ፡ ቅንን ፡ ልብ ፡ ለአገሬ ፡ ልጆች፡ እንዲሰጣቸው ፡ እመኛለሁ ። (ሆሴ ፡ ፲፬ ፡ ፱ ።)

መሠረት ፡ ስብሐት ፡ ለአብ ።



## ማስታወቂያ ።

፩ኛ ፤ ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ ስምዓ ፡ ጽድቅ ፡ ብለን ፡ የሰየምንበት ፡ ምክንያት ፡ የእውነትና፡ የጽድቅ ፡ ምስክርነቱ፡ በየአንቀጹ ፡ ሁሉ ፡ የጐላና ፡ የተብራራ ፡ ሆኖ ፡ መገኘቱን ፡ መላውን ፡ መጽሐፉን ፡ ያነበበ ፡ ሰው ፡ በሚያስተውለው ፡ ገንዘብ ፡ ነው ።

ደግሞ ፡ በመጽሐፉ ፡ አርባ ፡ ስድስት ፡ አንቀጾች ፡ እንዳሉበትና ፡ "እናምናለን፡" የሚል፡ ቃል ፡ በየአንቀጹ ፡ ሁሉ ፡ ተደጋግሞ ፡ እንደሚገኝ ፡ ግልጽ ፡ ነው ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ይህም ፡ ስለ ፡ ተባለ ፡ በመንፈሱ ፡ ዕድገት ፡ ያለው፡ ሰው ፡ ሁሉ፡ እንደሚያውቀው ፡ ከአንዱ ፡ እግዚአብሔር ፡ የምትሆን ፡ ሃይማኖት ፡ አንዲት ፡ ናትና ፡ የምናምናቸው ፡ ብዙ ፡ ነገሮች ፡ እንደሆኑ ፡ ማስታወቃችን ፡ አለመሆኑን ፡ በጥንቃቄ ፡ እናሳስባለን ።

ሐዋርያው ፡ ጳውሎስ ፡ ወደ ፡ ሮሜ ፡ ሰዎች ፡ በጻፈው ፡ መልእክቱ ፡ "ሁሉ ፡ ከእርሱና ፡ በእርሱ ፡ ለእርሱም ፡ ነው።" ሮሜ ፡ ፲፩፡፴፮ ሲል ፡ የተናገረውን ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መምህራን ፡ ሲያትቱ ፡ "ከእርሱ ፡ ያለውን ፡ ለአብ ፡ በእርሱ ፡ ያለውን ፡ ለወልድ ፡ ለእርሱ ፡ ያለውን ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ፡" ሰጥተው ፡ ሥራ ፡ ሥራቸውን ፡ ገልጸውበታል ። የአገባቦቹ ፡ መነሻ፡ ማድረጊያ፡ መድረሻ ፡ ምንጭ ፡ ከአንድ ፡ መሆንም ፡ የሥላሴን ፡ አንዲት ፡ መለኮትነት ፡ አስረድተዉበታል ።

ይህን ፡ አስደግፈው ፡ የእግዚአብሔርን ፡ አንድነትና ፡ ሦስትነት ፡ ከጻፉት ፡ መምህራን ፡ መካከል ፡ ቅዱስ ፡ ሳዊርያኖስ ፡ ጳጳስ ፡ ዘሀገረ ፡ ገብልህ ፡ ሃይማኖት ፡ በአብ ፡ ተጀምራ ፡ ወደ ፡ ወልድ ፡ እንደምታደርስ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እንደምትፈጸም ፡ ሲናገር ፡ "ሃይማኖት ፡ እንተ ፡ እምኀበ ፡ አብ ፡ ተወጥነት ፡ ኀበ ፡ ወልድ ፡ ታበጽሕ ፡ ኀበ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ትትፌጸም ፤" ብሎአል ።

በቅዱስ ፡ ሳዊርያኖስ ፡ ትምህርት ፡ ያሉትን ፡ ሁለት ፡ ቀዋምያን ፡ ነገሮች ፡ ልብ ፡ ማድረግ ፡ ያስፈልጋል ።

አንደኛው ፡ ነገር ፡ ይህች ፡ አንዲትዋ፡ ሃይማኖት፡ በሥላሴ ፡ አካላት ፡ ተገኝታ ፡ የሥላሴን ፡ ተዋህዶ ፡ ማስረዳትዋን ፡ ነው ።

ሁለተኛውም ፣ በአብ ፡ ተጀምራ ፣ እወልድ ፣ ዘንድ ፣ አድርሳ ፣ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በመፈጸምዋ ፣ ከአንዱ፡ እግዚአብሔር፡ ወጥታ ፡ ለሌላ ፡ የማትተርፍ ፡ መሆንዋን ፡ ነው ።

እነዚህ ፡ አርባ ፡ ስድስት ፡ አንቀጾችም፡ ምንም ፡ እንኳ፡ በአገላለጽ ፡ ረገድ ፡ ራስ ፡ ራሳቸውን ፡ የቻሉ ፡ ቢሆኑ ፣ በሦስት ፡ ታላላቅ ፡ ክፍሎች፡ ተከፍለው፥ “ተጋብእና፡ ተከፍሎ፡ ” ባለበት፡ የአንድነትና ፡ የሦስትነት ፡ ምሥጢር ፣ የእግዚአብሔር ፡ አብን ፡ ሥራ ፣ የእግዚአብሔር ፡ ወልድን ፡ ሥራ ፣ የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ሥራ ፡ በማስገንዘብ ፡ ይገኛሉ ። የዚህም ፡ አጭር ፡ ትርጉም ፣ ሕፀፅ ፡ ተውሣክ ፡ በሌለበት ፡ ሦስትነት ፡ አንድነትን ፤ ባዕድ ፡ አምላክ ፡ በሌለበት ፡ አንድነትም ፣ ሦስትነትን ፡ አሰናስሎ ፡ የሚገለጽበትን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ጠቅላላ ፡ ምሥጢርና ፡ ሥራ ፡ ማመን ፡ ማለት ፡ ነው ።

ስለዚህም ፣ ስምዓ ፡ ጽድቅ ፡ የተባለውን ፡ መጽሐፋችንን ፡ ስንጽፍ ፣ የሌላውን ፡ ድርሻ ፡ እንዳንነካ ፡ መታገዳችንን ፤ በአዕማደ ፡ ምሥጢር ፡ አከፋፈል ፡ ደንብ ፡ አምስት ፡ ክፍል ፡ ለማድረግ ፡ ቢቻል ፡ እንኳ ፣ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ያመለከትነውን ፡ ኀሳብ ፡ በመከተል ፣ አምስቱን ፡ አዕማደ ፡ ምሥጢር ፡ በምሥጢረ ፡ ሥላሴ ፡ ውስጥ ፡ ማጠቃለላችንን ፡ እናስገነዝባለን ።

፪ኛ ፤ እንዲሁም ፡ እያንዳንዱ ፡ አንቀጽ ፡ ብዙ ፡ ገጾች ፡ ለመሆን ፡ ሲችል ፣ በብዙ ፡ ቃላት ፡ የሚገለጸውን ፡ ጽሑፍ ፡ በዶክትሪን ፡ ደንብ ፡ ለማሳጠር ፡ ፈልገን ፣ ባጭር ፡ ለመግለጽ ፡ የሚያስችሉትን ፡ ቃላት ፡ ከአማርኛ ፡ እንዲሆኑ፡ ተጣጥረን፥ ሳይቻልም ፡ ከግዕዝ ፡ መርጠናል ።

፫ኛ ፤ በዚሁ ፡ መጽሐፍ፡ ውስጥ ፣ በእያንዳንዱ፡ አንቀጽ፡ የጥንታውያን ፡ አርቶዶክሳውያን ፡ መምህራን ፡ ኀሳብ ፣ ለእያንቀጹ ፡ በሚስማማው ፡ መጠን ፡ ተጠቅሶ ፡ ይገኛል ። እነሆም ፡ ጥቅሱ ፡ በግዕዙም ፡ እንዳለ ፡ መሆኑ ፡ ሳይቀር ፣ ወደ ፡ አማርኛም ፡ ተርጉመንዋል። እንግዲህ ፡ የግዕዙን ፡ አርእስት ፡ ጥቅስ ፡ ብለነው፥ የአማርኛውንም፡ አርእስት ፡ ትርጓሜ ፡ ብለነው ፡ የሚገኝ ፡ ሁሉ ፣ ያው ፡ የሊቃውንት ፡ ማስረጃ ፡ መሆኑን ፡ ለአንባቢ ፡ እናሳስባለን ።





፬ኛ ፤ በጽሑፋችንም ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ የጥንታውያን ፡ ሊቃውንትን ፡ ትምህርት ፡ ብንጠቅስ ፣ መሠረታችን ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ መሆኑን ፡ መግለጽ ፡ ስለሚገባ ፣ በየሐረጎቹ ፡ መክፈያና ፡ በየዓረፍተ ፡ ነገሩ ፡ ማቆሚያ ፡ ትይዩ ፣ ማለት ፡ እዚያው ፡ መሥመር ፡ ከወደቀኝ ፡ አቅጣጫ ፣ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ ጥቅስ ፡ ጽፈናል ። ይህንም ፡ ያደረግንበት ፡ ምክንያት ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ትምህርት ፡ ማጥናት ፡ የሚሻ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፣ በጥቅሶቹ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንዋ ፡ ትምህርት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ መሠረት ፡ መጽናቱን ፡ ወይም ፡ አለመጽናቱን ፡ ይመረምርባቸው ፡ ዘንድ ፡ አስፈላጊ ፡ እንደ ፡ መሆኑ ፣ ጥቅሶቹ ፡ ይቀሩ ፡ ዘንድ ፡ የሚገባ ፡ ስላልሆነ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ጥቅሶቹን ፡ በብዙ ፡ ለማግባት ፡ ሲቻለን ፡ በቦታ ፡ መጥበብ ፡ ምክንያት ፡ አሳንሰናቸዋል ።

እነርሱንም ፡ እንኳ ፣ በሚፈለጉበት ፡ ቦታ ፡ ሁሉ፡ እያሰባቀልን ፡ በሙሉ ፡ ብናገባቸው ፡ ብዙ ፡ ከመሆናቸው ፡ የተነሣ ፣ አንባቢን ፡ ከማስቸገር ፡ ጋር ፡ የጽሑፍን ፡ ገጸ ፡ ንባብ ፡ አያሳምሩም ። ስለዚህም ፡ አንባቢን ፡ ሳያስቸግሩና ፡ የገጸ ፡ ንባብም ፡ ሥርዐት ፡ ሳይጐዳባቸው ፣ መርማሪን ፡ የሚጠቅሙበት ፡ ዘዴን ፡ ስፈልግ ፣ በመሥመሩ ፡ ጐን ፡ ሆነው ፡ ለንዑስና ፡ ለዐቢይ ፡ ሐረግ ፡ መክፈያ ፡ ለዐረፍተ ፡ ነገርም ፡ ማቆሚያ ፡ በተመደቡ ፡ ሠረዞች ፡ ወይም ፡ ነጥቦች ፡ ተመልክተው ፡ ቢጻፉ ፣ የተሻለ ፡ ነገር ፡ መስሎ ፡ ታየኝ ።

ኮከብ ፣ ወይም ፡ ሌላ ፡ ምልክት ፡ ማድረግ ፡ ለጊዜው ፡ አድካሚ ፡ መንገድ ፡ ስለሆነ ፣ ሠረዞቹን ፡ ወይም ፡ ነጥቦቹን ፡ ሁለቱንም ፡ ነገር ፡ ልናስይዛቸው ፡ እንችላለን ። ማለት ፣ ለሐረጉ ፡ ወይም ፡ ለዐረፍተ ፡ ነገሩ ፡ መክፈያ ፡ ማቆሚያ ፡ ሆነው ፡ በሚገኙበት ፡ ትይዩ ፡ በጥቅሱ ፡ መጀመሪያ ፡ መነሻ ፡ ሆነው ፡ ይገኛሉ ። እንደዚህም ፡ ሲሆን ፣ አንባቢው ፡ በጥቅሱ ፡ መነሻ ፡ ያለውን ፡ ሠረዝ ፡ አይቶ ፡ እንደ ፡ ገናም ፣ ጥቅሱ ፡ ባለበት ፡ በዚያው ፡ መሥመር ፡ መለስ ፡ ብሎ ፡ ሲመለከት ፣ ሠረዙን ፡ ሊያገኘው ፡ ነው ። ወዲያውም ፡ ጥቅሱ ፡ መክፈያ ፡ ወይም ፣ ማቆሚያ ፡ ለሆነበት ፡ ሐረግ ፡ መረጃ ፡ መሆኑን ፡ ሊያውቅ ፡ ነው ።

የሐረግና ፡ የዐረፍተ ፡ ነገር ፡ መክፈያ ፡ ወይም ፡ ማቆሚያ ፡ ከመሆናቸው ፡ ጋር ፣ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ጥቅሶችን ፡ እንዲያመለክቱ ፡

የምንጠቀምባቸው ፡ ሠረዞች ፡ ወይም ፡ ነጥቦች ፡ እንደሚከተለው ፡ ተጽፈዋል ።

፡ ፤ ?

። !

ከእነዚህ ፡ አንዱ ፡ በጥቅሱ ፡ መጀመሪያ ፡ ለምሳሌ ፡—፡ ማቴ ፡ ፭ ፡ ፳፭ ። እንደዚህ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ በዚያው ፡ መሥመር ፡ ስታነብ ፡ የእርሱን ፡ ዐይነት ፡ ሠረዝ ፡ ታገኛለህ ። ጥቅሱም ፡ በዚያው ፡ ሐረግ ፡ ለተነገረው ፡ ቃል ፡ ማስረጃ ፡ መሆኑን ፡ ታውቃለህ ።

፩ኛ ፤ በመጽሐፉ ፡ መጀመሪያ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ ለክርስቲያናዊ ፡ ቤተ ፡ መንግሥትዋ ፡ የብርሃን ፡ በር ፡ የተከፈተበት ፡ የአቡነ፡ ሰላማ፡ ከሣቴ ፡ ብርሃን ፡ አጭር ፡ ታሪክ፡ ይገኝበታል።

እንደዚሁም፡ ከብዙ፡ ጊዜ፡ ጀምሮ፡ የቤተ፡ ክርስቲያን፡ አንድነትና፡ እውነተኛ ፡ አምልኮ ፡ ጸንቶባቸው ፡ የሚገኝ ፡ በቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ መንፈስ ፡ የተዘጋጁና ፡ የሐዋርያት ፡ ሰምቦሎን ፡ የኒቅያ ፡ ጸሎተ ፡ ሃይማኖት ፡ የቅዱስ ፡ አትናቴዎስ ፡ ትምህርተ፡ ሃይማኖትና፡ የሐዋርያት ፡ አመክንዮ ፡ በመባል ፡ የታወቁት ፡ የሃይማኖት ፡ ሥርዐቶች ፡ ገሚሶችን፡ በግዕዝና ፡ በአማርኛ ፡ ገሚሶቹን ፡ ግን ፡ በአማርኛ፡ ብቻ፡ ጽፌ፡ አለሁ ።

ዳግም ፡ በመግቢያው ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የመምህርነቱ ፡ ማስገንዘቢያና ፡ የሊቀ ፡ ካህንነቱ ፡ ጸሎት ፡ ይገኛል ። በመጨረሻውም ፡ የቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ማስገንዘቢያና ፡ ጸሎት ፡ መዝጊያ ፡ ሆኖ ፡ ተጽፎአል ።

ደራሲው ፡



## ዋ ዜ ማ ፡

ንዜንወክሙ ፡ ዜና ፡ ሠናየ ፡ ዘሰማዕነ ፡ ወዘርኢነ ፡ ወዘነገሩነ ፡ አበዊነ ፤ ጳጳሳት ፡ ቀሳውስት ፡ ወዲያቆናት ፡ ወኵሎሙ ፡ መሃይምናን ፡ ብፁዕ ፡ ውእቱ ፡ አባ ፡ ሰላማ ፡ ከሠተ ፡ ለነ፡ ብርሃነ ፡ ዜናሁ፡ ለመድኃኒነ።



ቅዱስ ፡ ፍሬምናጦስ ፡
(አቡነ ፡ ሰላማ ፡ ከሣቴ ፡ ብርሃን ።)

ዝንቱሰ ፡ ብእሲ ፡ መምህርነ ፡
ዘተፈነወ ፡ ውስተ ፡ ምድርነ ፡
ይክሥት ፡ ብርሃነ ።

ቅ. ያሬድ ፡

## የብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ሰላማ ፡ ከሣቴ ፡ ብርሃን ፡ ታሪክ ።

### ኢትዮጵያ ፡ ታበጽሕ ፡ እደዊሃ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ።

ነቢዩ ፡ ዳዊት፡—"ኢትዮጵያ፡ እጆችዋን ፡ ወደ፡ እግዚአብሔር ፡ ትዘረጋለች፡ " ሲል ፡ የተናገረው ፡ ትንቢት ፡ በተስፋ ፡ ሲጠበቅ ፡ ቈይቶ ፡ የሚፈጸምበት ፡ ጊዜ ፡ ሲደርስ ፡ ምሥጢሩ ፡ ተመርምሮ ፡ የማይደረስበት ፡ አምላክ ፡ ጥልቅ ፡ በሆነው ፡ ጥበቡ ፡ በንግድ ፡ ምክንያት ፡ ባሕሩንና ፡ የብሱን ፡ እየዞረ ፡ አገርንና ፡ የሰዎችን ፡ አኳኋን ፡ እየመረመረ ፡ የሚያጠናውን ፡ ሜሮጵዮስ ፡ የሚባለውን ፡ ሰው ፡ ከጢሮስ ፡ አስነሥቶ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ጥንታዊ ፡ ወደብ ፡ ወደ ፡ አዱሊስ ፡ እንዲመጣ ፡ አደረገ ።

በዚህም ፡ ለሕዝበ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ነዋሪን ፡ በረከት ፡ ባመጣው ፡ ጉዞ ፡ ሜሮጵዮስን ፡ የተከተሉ ፡ አንደኛው ፡ ፍሬ ፡ ምናጦስ ፡ ሁለተኛውም ፡ ኤዴስዮስ ፡ (ሲድራኮስ) ፡ የተባሉ ፡ ሁለት ፡ ወጣቶች ፡ ነበሩበት።

ሜሮጵዮስም ፡ እወደቡ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ ዕቃውን ፡ ከመርከቡ ፡ አውርዶ ፡ ከሁለቱ ፡ ልጆቹ ፡ ጋር ፡ የእግር ፡ መንገድ ፡ እንደ ፡ ጀመሩ ፡ ለገንዘቡ ፡ የሳሱ ፡ ሽፍቶች ፡ እርሱን ፡ ገደሉት ። ልጆቹን ፡ ግን ፡ ከመግደላቸው ፡ በፊት ፡ ወዲያው ፡ ባላገሮች ፡ ደርሰውላቸው ፡ ታደጉአቸው ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ወጣቶቹን ፡ ወደ፡ ባሕረ፡ ነጋሽ ፡ ወሰዱአቸውና ፡ እርሱም ፡ እልዓሜዳ ፡ (ታዚር) ፡ ወደ ፡ ተባለው ፡ ወደ ፡ አክሱም ፡ ንጉሥ ፡ ላካቸው ። በንጉሡም ፡ ፊት ፡ ቀርበው ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ እንደ ፡ መጡ ፡ እንዴትስ ፡ ይህ ፡ አደጋ ፡ እንደ ፡ ደረሰባቸው ፡ ተናገሩና ፤ እርሱም ፡ ራርቶ ፡ የበጎነት ፡ ሥራ ፡ አደረገላቸው ። ወዲያውም ፡ ንጉሡ ፡ ሞተና ፡ ልጆቹ ፡ ለዙፋን ፡ ያልደረሱ ፡ ሕፃናት ፡ ስለሆኑ ፡ እሕየዋ ፡ (ሶፍያ) ፡ የተባለችው ፡ እናታቸው ፡ በሞግዚትነት ፡ የመንግሥቱን ፡ ሥራ ፡ ታካሂድ ፡ ነበረች ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ለኤዴስዮስ ፡የጸሐፊነትንና ፡ የአዛዥነትን ፡ ማዕርግ ፡ ሰጥታ ፡ ፍሬምናጦስንም ፡ የቤተ፡ መጻሕፍት ፡ ኀላፊና ፡ ልዑላን፡ ልጆችዋን ፡ እንዲያስተምር፡ አደረገች ።

ፍሬ ፡ ምናጦስ ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ወንጌል ፡ ትምህርት ፡ ንቃት ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ነበርና ፡ የክርስትናን ፡ እምነት ፡ ለንጉሡ ፡ ልጆች ፡ ከማ





ስተማሩ ፡ በላይ ፡ በአክሱም ፡ ከነበሩት ፡ ካህናተ ፡ ኦሪት ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ እያደረገ ፡ ጥቂት ፡ በጥቂት ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ብርሃን ፡ ይገልጥላቸው ፡ ነበር ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ኢዛና ፡ የተባለው ፡ ትልቁ ፡ ልጅ ፡ አድጎ ፡ በዙፋኑ ፡ ላይ ፡ በነገሠ ፡ ጊዜ ፡ ኤዴስዮስ ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ወደ ፡ ጢሮስ ፡ ተመለሰና ፡ ቄስ ፡ ሆኖ ፡ ተቀመጠ ። ፍሬ ፡ ምናጦስ ፡ ግን ፡ በስንብት ፡ ወደ ፡ እስክንድርያ ፡ ሄዶ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ከነበረው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ከቅዱስ ፡ አትናቴዎስ ፡ ሐዋርያዊ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ወንጌልን ፡ የሚሰብክና ፡ የሚያጠምቅ ፡ አስተማሪ ፡ እንዲላክ ፡ ጥያቄ ፡ አቀረበ ።

አትናቴዎስ ፡ ሐዋርያዊም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፍቅርና ፡ በመንፈሳዊ ፡ ቅንዓት ፡ ትጋት ፡ ያለው፡ እንደዚሁም፡ በአስፈላጊነቱ ፡ ልክ ፡ የአገሩን ፡ ቋንቋና ፡ የሕዝቡን ፡ ልማድ፡ የሚያውቅ ፡ ከቅዱስ ፡ ፍሬ ፡ ምናጦስ ፡ ወዲያ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ አለመኖሩን ፡ በማድነቅ ፡ ተገንዝቦ ፡ ሢመተ ፡ ጵጵስናን ፡ ሰጠውና ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ላከው ።

ሰላማ ፡ የተባለው ፡ ፍሬ ፡ ምናጦስም ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተመልሶ ፡ መጥቶ ፡ አክሱም ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ እንደ ፡ ገባ ፡ ፊት ፡ እዚያ ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ ባለሰለሰው ፡ በሕዝቡ ፡ ልብ ፡ እርሻ ፡ ላይ ፡ አሁን ፡ ግልጽ ፡ አድርጎ ፡ ስለ ፡ ክርስቶስና ፡ ስለ ፡ ክርስትና ፡ ሃይማኖት ፡ ስብከቱን ፡ በዘራ፡ ጊዜ ፡ ያለ፡ አንዳች፡ ችግር ፡ ትምህርቱ፡ በቅሎለት፡ ወዲያው ፡ ለፍሬ ፡ ደረሰለት ።

በሕፃንነቱ፡ ወራት፡ ከእርሱ ፡ የተማረው፡ ኢዛና ፡ ከአባቶቹ ፡ ተያይዞ ፡ የመጣውን ፡ ልማድና ፡ አምልኮ ፡ ፈጥኖ ፡ ለመተው ፡ የሚያዳግቱት ፡ ብዙ ፡ ምክንያቶች ፡ ቢኖሩ ፡ እንኳ ፡ አቡነ ፡ ሰላማ ፡ ወንጌሉን ፡ ገልጾ ፡ ባስተማረ ፡ ጊዜ ፡ በቁርጥ ፡ ክርስቲያን ፡ ሆኖ ፡ ተጠመቀና ፡ ስሙ ፡ አብርሃ ፡ ተባለ ። ሳይዘናስ ፡ የተባለው ፡ ወንድሙም፡ አጽብሐ ፡ ተብሎ ፡ ተሰየመ ። ከካህናተ ፡ ኦሪትም ፡ ብዙዎቹ ፡ በክርስቶስ ፡ ስም ፡ አመኑ ። በልዩ ፡ ልዩ ፡ አምልኮ ፡ የኖሩ ፡ አረማውያን ፡ ደግሞ ፡ አምልኮ፡ ባዕድንና ፡ ክፉ ፡ ልማድን ፡ እየተዉ ፡ ለክርስቶስ ፡ መንግሥት ፡ ተገዙ ።

እንግዲህ ፡ ዐይነተኛው ፡ ኢያሱ ፡ ጠላቶቹን ፡ ከእግሩ ፡ ጫማ ፡ በታች ፡ አስገዝቶ ፡ እስኪመለስ ፡ ድረስ ፡ ሳይገባ ፡ ያለማቋረጥ ፡ አብ

ርቶ ፡ የምናየው ፡ የወንጌል ፡ ፀሐይ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ገባያን ፡ ላይ ፡ የቆመው ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ነው ። ይህም ፡ የሆነው ፡ ከ፫፻፴-፫፻፴፭ ፡ ዓ. ም. ነው ።

አቡነ ፡ ሰላማም ፡ የአሪት ፡ ቀንበርና ፡ የአሕዛብ ፡ ልማድ ፡ አጨልሞአት ፡ ከነበረችው ፡ ከብሔረ ፡ አግዓዚ ፡ ይህን ፡ ከንቱነት ፡ በወንጌል ፡ ብርሃን ፡ ስላስወገደ ፡ በብርሃኑ ፡ ደስታቸውን ፡ ያዩ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡—"ሰላማ ፡ ከሣቴ ፡ ብርሃን ፡" ሲሉ ፡ ሥራውን ጨምሮ ፡ የሚገልጽ ፡ የክብርን ፡ ስም ፡ ሰጥተውታል ።

ለነፍሳቸው ፡ ደኅንነትም ፡ እንደ ፡ መልካም ፡ አባት ፡ ያስብላቸው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ፍቅሩ ፡ ተሰምቷቸው ፡ "አቡነ ፡" ብለውታል ።

አቡነ ፡ ሰላማ ፡ ምሥጢረ ፡ ሥላሴንና ፡ ምሥጢረ ፡ ሥጋዌን ፡ አጥርቶ ፡ ያስተምር ፡ የነበረውን ፡ የቅዱስ ፡ አትናቴዎስ ፡ ሐዋርያዊን ፡ ፍለጋ ፡ ተከትሎ ፡ ሰውና ፡ እግዚአብሔር ፡ አንድ ፡ የሚሆኑበት ፡ መካከለኛነትን ፡ በሚያረጋግጥ ፡ በክርስቶስ ፡ ፍጹም ፡ አምላክነትና ፡ ፍጹም ፡ ሰውነት ፡ እምነት ፡ (፩ ፡ ጢሞ ፡ ፪ ፡ ፭ ፡ ፮ ።) ጠንክሮ ፡ እያስተማረ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ምዕመናን ፡ አጐልምሶአቸው ፡ መኖሩን ፡ የምናውቅበት ፡ ማስረጃ ፡ አለን ። ይኸውም ፡ የታላቁ ፡ ቈስጠንጢኖስ ፡ ልጅ ፡ ቍንስጣ ፡ የአርዮስን ፡ ሃይማኖት ፡ ይወድ ፡ ነበረና ፡ በእርሱ ፡ አማካይነት ፡ ቴዎፍሎስ ፡ ህንዳዊ ፡ የሚባል ፡ አርዮሳዊ ፡ ክፉ ፡ እንክርዳዱን ፡ በእነዚህ ፡ አዳዲስ ፡ ተክሎች ፡ ላይ ፡ ሊዘራ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ትምህርቱን ፡ የሚቀበል ፡ ታጥቶ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ አፍሮ ፡ መመለሱን ፡ ነው ።

ከሣቴ ፡ ብርሃን ፡ ሰላማ ፡ ይህን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ክፍሎች ፡ አንዳንዶቹን ፡ ከፅርዕና ፡ ከቅብጢ ፡ ወደ ፡ ግዕዝ ፡ እንደ ፡ መለሰ ፡ በአንዳንድ ፡ መጻሕፍቶቻችን ፡ ታሪክ ፡ እናገኛለን ።

ብእሴ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰላማ ፡ እንደ ፡ ስሙ ፡ በክርስቶስ ፡ ማዕከላዊነትና ፡ በመስቀሉ ፡ ደም ፡ በእግዚአብሔርና ፡ በሰው ፡ ስለ ፡ ተፈጸመው ፡ የዕርቅ ፡ ሥራ ፡ መልእክተኝነቱን ፡ ለሕዝበ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በማስታወቁ ፡ ሰላማዊነቱን ፡ አስረድቶአል ። (፪ ፡ ቆሮ ፡ ፭ ፡ ፲፱ ፡ ፳ ።)

በአፍሪካ ፡ ውስጥ ፡ ታላላቅ ፡ መምህራን ፡ የነበሩባቸው ፡ ብዙ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ሲጠፉ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የተቋቋሙት ፡ ቤተ ፡





ክርስቲያንና ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ግን ፡ የአይሁድንና ፡ የመሐመዳውያንን ፡ ትግል ፡ አልፈው ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ በመቈየታቸው ፡ ወንጌልንም ፡ አጽንተው ፡ በመገኘታቸው ፡ ለመጀመሪያው ፡ ሐዋርያቸውና ፡ ወንጌላዊያቸው ፡ ለአቡነ ፡ ሰላማ ፡ ከሣቴ ፡ ብርሃን ፡ የትጋቱና ፡ የፍቅር ፡ አገልግሎቱ ፡ ፍሬ ፡ መሆናቸውን ፡ ከማስደነቅ ፡ ጋር ፡ ያስረዳሉ ።

## የሐዋርያት፡ የሃይማኖት፡ ሥርዓት ።

ሁሉን ፡ በሚችል ፡ ሰማይንና ፡ ምድርን ፡ በፈጠረ ፡ በእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ እናምናለን ።

በአንድ ፡ ልጁም ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የተፀነሰ ፡ ከማርያም ፡ ድንግል ፡ የተወለደ ፡ በጲላጦስ ፡ ጴንጤናዊ ፡ ዘመን ፡ መከራ ፡ የተቀበለ ፡ የተሰቀለ ፡ የሞተ ፡ የተቀበረ ፡ ወደ ፡ ሲኦልም ፡ የወረደ ፡ በሦስተኛው ፡ ቀንም ፡ ከሙታን ፡ የተነሣ ፡ ወደ ፡ ሰማይም ፡ ያረገ ፡ ሁሉን ፡ በሚችል ፡ በእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ቀኝ ፡ የተቀመጠ ፡ ከዚያም ፡ በሕያዋንና ፡ በሙታን ፡ ሊፈርድ ፡ በሚመለስ ፡ እናምናለን ።

ደግሞም ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ፡ በአንዲት፡ ቅድስት፡ ሐዋርያዊት፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በቅዱሳን ፡ አንድነት ፡ በኃጢአትም ፡ ሥርየት ፡ በሥጋም ፡ ትንሣኤ ፡ በዘለዓለምም ፡ ሕይወት ፡ እናምናለን ። አሜን ።

## የ፫፻ ፡ ጸሎተ ፡ ሃይማኖት ፡ በግዕዝ ።

ነአምን ፡ በአሐዱ ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ አኃዜ ፡ ኵሉ ፤ ገባሬ ፡ ሰማያት ፡ ወምድር ፡ ዘያስተርኢ ፡ ወዘኢያስተርኢ ፤

ወነአምን ፡ በአሐዱ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወልደ ፡ አብ ፡ ዋህድ ፡ ዘህልው ፡ ምስሌሁ ፡ እምቅድመ ፡ ይትፈጠር ፡ ዓለም፡ ብርሃን ፡ ዘእምብርሃን ፡ አምላክ ፡ ዘእምአምላክ ፡ ዘበአማን ፡ ዘተወልደ፡ ወአኮ ፡ ዘተገብረ ፡ ዘዕሩይ ፡ ምስለ ፡ አብ ፡ በመለኮቱ ፡ ዘቦቱ ፡ ኵሉ ፡ ኮነ ፤ ወዘእንበሌሁሰ ፡ አልቦ ፡ ዘኮነ ፡ ወኢምንትኒ ፡ ዘበሰማይኒ ፡ ወዘበምድርኒ ፡ ዘበእንቲአነ ፡ ለሰብእ ፡ ወበእንተ ፡ መድኃኒትነ ፡ ወረደ ፡ እምሰማያት፡ ተሰብአ፡ ወተሠገወ፡ እመንፈስ፡ቅዱስ፡ ወእማርያም፡ እምቅድስት ፡ ድንግል ፡ ኮነ ፡ ብእሴ ፡ ወተሰቅለ ፡ በእንቲአነ ፡ በመዋዕለ ፡ ጲላጦስ ፡ ጴንጤናዊ ፡ ሐመ ፡ ወሞተ ፡ ወተቀብረ ፡ ወተንሥአ ፡ እሙታን ፡ አመ ፡ ሣልስት ፡ ዕለት ፡ በከመ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስተ ፡ ቅዱሳት ፡

መጻሕፍት ፡ ዐርገ ፡ በስብሐት ፡ ውስተ ፡ ሰማያት ፡ ወነበረ ፡ በየማነ ፡ አቡሁ ፤ ዳግመ ፡ ይመጽእ ፡ በስብሐት ፡ ይኰንን ፡ ሕያዋነ ፡ ወሙታነ፡ ወአልቦ ፡ ማኅለቅት ፡ ለመንግሥቱ ፡

ወነአምን ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እግዚእ ፡ ማሕየዊ ፡ ዘሠረፀ ፡ እምአብ ፡ ንስግድ ፡ ሎቱ ፡ ወንሰብሖ ፡ ምስለ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ዘነበበ፡ በነቢያት ።

ወነአምን ፡ በአሐቲ ፡ ቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንተ፡ ላዕለ ኵሉ ፡ ጉባኤ ፡ ዘሐዋርያት ።

ወነአምን ፡ በአሐቲ ፡ ጥምቀት፡ ለሥርየተ ፡ ኃጢአት ፤ ወንሴፎ፡ ትንሣኤ ፡ ሙታን ፡ ወሕይወተ ፡ ዘይመጽእ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፤ አሜን ።

በ፫፻፲፰ወ፳ቱ ፡ ርቱዓነ ፡ ሃይማኖት ፡ የተወሰነ ፡ የኒቅያ ፡
<u>የሃይማኖት ፡ ሥርዓት ፡ በአማርኛ ።</u>

ሁሉን ፡ በሚገዛ ፡ ሰማይንና ፡ ምድርን ፡ የሚታየውንና ፡ የማይ ታየውን ፡ በፈጠረ ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሚሆን ፡ በእግዚአብሔር ፡ አብ፡ እናምናለን ።

ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ የአብ ፡ አንድ ፡ ልጁ ፡ በሚሆን ፡ በአንድ ፡ ጌታ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እናምናለን ። እርሱም ፡ ከብርሃን ፡ የተገኘ ፡ ብርሃን ፡ ከእውነተኛ ፡ አምላክ ፡ የተገኘ ፡ አምላክ ፡ የሚሆን ፡ የተፈጠረ ያይደለ ፡ የተወለደ ፡ በመለኮቱ ፡ ከአብ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ የሆነ ፡ ሁሉ ፡ በእርሱ ፡ የሆነ ፡ በሰማይና ፡ በምድር ፡ ካለው ፡ ሁሉ ፡ ያለ ፡ እርሱ ፡ ምንም ፡ የሆነ ፡ የሌለ ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ ስለ ፡ ሰዎች ፡ እኛንም ፡ ስለ ፡ ማዳን ፡ ከሰማይ ፡ ወረደ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስም፡ ከቅድስት ፡ ድንግል፡ ማርያም ፡ ሥጋን ፡ ለበሰ ፡ ሰውም ፡ ሆነ ፡ በጰንጤናዊ ፡ በጲላጦስ ፡ ዘመን ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ ተሰቀለ ፡ መከራን ፡ ተቀበለ ፡ ሞተ ፡ ተቀበረም ፤ በቅዱሳት ፡ መጻ ሕፍት ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን፡ ከሙታን ፡ ተለይቶ ፡ ተነሣ፡ በክብርም፡ ወደ ፡ ሰማይ፡ ዐረገ ፡ በአባቱም ፡ ቀኝ ፡ ተቀመጠ፡ ዳግመኛም በሕያዋንና ፡ በሙታን ፡ ይፈርድ ፡ ዘንድ ፡ በጌትነት ፡ ይመጣል ፤ ለመን ግሥቱም ፡ ፍጻሜ ፡ የለውም ።





ከአብና ፡ ከወልድ ፡ ጋር ፡ በአንድነት ፡ በሚሰገድለትና ፡ በሚመ ሰገን ፡ ጌታ ፡ ሕይወት ፡ ሰጭ ፡ በሚሆን ፡ ከአብ ፡ በሠረፀ ፡ በነቢያትም ፡ በተናገረ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እናምናለን ።

በሁሉም ፡ ዘንድ ፡ በምትሆን ፡ ሐዋርያት ፡ በሰበሰቡአት ፡ በ አንዲት ፡ ቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እናምናለን ።

ለኃጢአትም ፡ ሥርየት ፡ በአንዲት ፡ ጥምቀት ፡ እናምናለን ። የሙታን ፡ ትንሣኤንና ፡ የሚመጣውን ፡ ዓለም ፡ ሕይወት ፡ በተስፋ ፡ እንጠባበቃለን ። አሜን ።

<u>አመክንዮ ፡ ዘሐዋርያት ፡ በግዕዝ ።</u>

ነአምን ፡ በ፩ዱ ፡ አምላክ ፡ ገባሬ ፡ ኵሉ ፡ ፍጥረት ፡ አብ ፡ ለእግ ዚእነ ፡ ወአምላክነ ፡ ወመድኃኒነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እስመ ፡ አልቦ ፡ ውስተ ፡ ህላዌሁ ፡ አመክንዮ ።

በከመ ፡ አቅደምነ ፡ ነጊረ ፡ አላ ፡ ባሕቱ ፡ ህልው ፡ በኵሉ፡ መዋ ዕል ፡ አልቦቱ ፡ ጥንት ፡ ወኢተፍጻሜት ፡ ወቦቱ፡ ብርሃን፡ ዘኢይጠፍእ ፡ ወአልቦ ፡ ዘይክል ፡ ቀሪበ ፡ ኀቤሁ ፡ ኢኮነ ፡ ፪ተ ፡ ወኢ፫ተ ፡ ወኢይትዌ ሰክ ፡ አላ ፡ ፩ዱ ፡ ውእቱ ፡ ባሕቲቱ ፡ ዘይነብር ፡ ለዓለም ። እስመ ፡ ኢ ኮነ ፡ ሥውረ ፡ ዘኢይትአመር ፡ ዳዕሙ ፡ ጥዩቀ ፡ አእመርናሁ ፡ በኦሪት ፡ ወበነቢያት ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ አኃዜ ፡ ኵሉ ፡ ወሥሉጥ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ ፍጥረት ፡ አሐዱ ፡ እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ለእግዚእነ ፡ ወመድኃኒነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘተወልደ ፡ እምቅድመ ፡ ይትፈጠር ፡ ዓለም ፡ ወ ልድ፡ ዋህድ ፡ ዘዕሩይ ፡ ምስሌሁ ፡ ገባሬ፡ ኵሉ ፡ ሠራዊት፡ ወሢመታት ፡ ወሥልጣናት ፡ ዘሠምረ ፡ ይኩን ፡ ሰብአ ፡ በደኃሪ ፡ መዋዕል ።

ወነሥአ ፡ ሥጋ ፡ እማርያም ፡ እምቅድስት ፡ ድንግል ፡ ዘእንበለ፡ ዘርዐ ፡ ብእሲ ፡ ወተሐፅነ ፡ ከመ ፡ ሰብእ ፡ ዘእንበለ ፡ ኃጢአት ፡ ወአበሳ ፡ ወአልቦ ፡ ጕሕሉት ፡ ውስተ ፡ አፉሁ ፤ ወእምዝ ፡ ሐመ ፡ ወሞተ ፡ በሥጋ፡ ወተንሥአ ፡ እሙታን ፡ በሣልስት ፡ ዕለት ፡ ወዐርገ ፡ ሰማያተ ፡ ኀበ ፡ አብ ፡ ዘፈነዎ ፤ ወነበረ ፡ በየማነ ፡ ኃይል ።

ወፈነወ ፡ ለነ ፡ ጰራቅሊጦስሃ ፡ መንፈሰ ፡ ጽድቅ ፡ ዘወፅአ ፡ እምኀበ ፡ አብ ፡ ወአድኀነ ፡ ዓለመ ፡ ዘህልው ፡ ምስለ ፡ አብ ፡ ወወልድ ።

ንብል ፡ እንከ ፡ ከመ፡ ኵሉ ፡ ሠናይ ፡ ፍጥረተ ፡ እግዚአብሔር፡ ወአልቦ ፡ ግዱፍ ፤ ወመንፈስሰ ፡ ሕይወተ ፡ ሥጋ ፡ ይእቲ ፡ ንጽሕት ፡ ወቅድስት ፡ በኵሉ ።

ወንሕነሰ ፡ ንብል ፡ ከመ ፡ ሰብሳብ ፡ ንጹሕ ፡ ወልደት ፡ ዘአልቦ ፡ ርኵስ ፡ እስመ ፡ ፈጠሮሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለአዳም ፡ ወለሔዋን ፡ ከመ ፡ ይብዝኁ ፡ ሕዝብ ።

ንለቡ ፡ እንከ ፡ ከመቦ ፡ ውስተ ፡ ሥጋነ ፡ ነፍስ ፡ እንተ ፡ ኢትመውት ፡ ወኢትማስን ፡ ምስለ ፡ ሥጋ ፡ ንሕነሰ ፡ ናስቄርር ፡ ኵሎ ፡ ግብሮሙ ፡ ለዕልዋነ ፡ ሃይማኖት ፡ ወኵሎ ፡ ፍልጠተ ፡ ወዐሊወ ፡ ሕግ ፡ እስመ ፡ ርኵሳን ፡ እሙንቱ ፡ በኀቤነ ።

ወካዕበ ፡ ነአምን ፡ ትንሣኤ ፡ ሙታን ፡ ጻድቃን ፡ ወኃጥአን ፤ ወዕለተ ፡ ኵነኔ ፡ አመ ፡ ይትፈደይ ፡ ኵሉ ፡ በከመ ፡ ምግባሩ ።

ወዓዲ ፡ ነአምን ፡ ከመ ፡ ክርስቶስ ፡ ኢኮነ ፡ ሕፁፀ ፡ እምትስብእት ፡ ወኢምንተኒ ፡ አላ ፡ ውእቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ዘኮነ ፡ ሰብአ ፡ በጽድቅ ፡ ወዐረቀ ፡ ትዝምደ ፡ ሰብእ ፡ ምስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሊቀ ፡ ካህናቲሁ ፡ ለአብ ።

ኢንትገዘር ፡ እንከ ፡ ከመ ፡ አይሁድ ፡ ነአምር ፡ ከመ ፡ መጽአ ፡ ዘይፌጽም ፡ ኦሪተ ፡ ወነቢያተ ፡ ዘኪያሁ ፡ ይሴፈዉ ፡ ምጽአቶ ፡ ኵሎሙ ፡ አሕዛብ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘሠረፀ ፡ እምይሁዳ ፡ ወእምሥርወ፡ ዕሤይ ፡ ዘሥልጣኑ ፡ ዲበ ፡ መትከፍቱ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ወአኰቴት ፡ ዕበይ ፡ ወባርኮት ፡ ውዳሴ ፡ ወማኅሌት ፡ ይእዜኒ ፡ ወዘልፈኒ፡ ወለዓለመ ፡ ዓለም ፤ አሜን ።

## የሐዋርያት ፡ አመክንዮ ፡ በአማርኛ ።

የጌታችንና፡ የመድኃኒታችን፡ የኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ አባት ፡ በሚሆን፡ ፍጥረትን፡ ሁሉ፡ በፈጠረ፡ በአንድ፡ አምላክ፡ እናምናለን።





ለህላዌው ፡ ምክንያት ፡ የለውምና ፡ አስቀድመን፡ እንደ ፡ ተናገርን ፡ በዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ ይኖራል ፡ እንጅ ፡ መጀመሪያ፡ ወይም ፡ መጨረሻ ፡ የለውም ። በእርሱም ፡ የማይጠፋ ፡ ብርሃን ፡ አለ ፤ ወደ፡ እርሱ ፡ ለመቅረብም ፡ የሚቻለው ፡ የለም ። ብቻውን ፡ የሚኖር ፡ አንድ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ ሁለተኛ ፡ አይደለም ፡ ሦስተኛም ፡ አይደለም ፡ ተጨማሪም ፡ የለውም ። ሁሉን ፡ የያዘና ፡ በፍጥረቱም ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ የሠለጠነ ፡ መሆኑን ፡ በኦሪትና ፡ በነቢያት ፡ ተረድተን ፡ ያወቅነው ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ የማይታወቅ ፡ የተሠወረ ፡ አይደለም ፡ እኮ ! ከእርሱ ፡ ጋር ፡ የተካከለ ፡ ሢመታትንና፡ ሥልጣናትን ፡ ሁሉ፡የፈጠረ፡ዓለም፡ ሳይፈጠር፡የተወለደ፡ አንዲያ ፡ ልጅ ፡ የጌታችንና ፡ የመድኃኒታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አባት ፡ እግዚአብሔር ፡ አንድ ፡ ነው ። ጌታችንም ፡ በኋለኛው ፡ ዘመን ፡ ሰው ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ወደደ ፤ ያለዘርዓ ፡ ብእሲ ፡ ከቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ሥጋን ፡ ነሣ ፤ ያለ ፡ ኃጢአትና ፡ ያለ ፡ በደል ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ አደገ ፤ በእንደበቱም ፡ ምንም ፡ ሽንገላ፡ አልተገኘም። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በሥጋው ፡ መከራን ፡ ተቀበለ ፤ ሞተም ፤ በሦስተኛውም ፡ ቀን ፡ ከሙታን ፡ ተለይቶ ፡ ተነሣ ። ወደ ፡ ላከውም ፡ ወደ ፡ አብ ፡ ወደ ፡ ሰማያት ፡ ዐረገ ። በኃይልም ፡ ቀኝ ፡ ተቀመጠ ።

በአብና ፡ በወልድ ፡ ዘንድ ፡ ህልው ፡ የሚሆን ፡ ዓለምን ፡ ያዳነ ፡ ከአብ ፡ የሠረፀውን ፡ መንፈስ ፡ ጽድቅ ፡ ጰራቅሊጦስን ፡ ሰደደልን ።

እንግዲህ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ መልካም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግድፈትም ፡ እንደሌለበት ፡ እንናገራለን ። የሥጋ ፡ ሕይወት ፡ የምትሆን ፡ መንፈስ ፡ ግን ፡ ሁለመናዋ ፡ ንጽሕትና ፡ ቅድስት ፡ ናት ።

እኛስ ፡ ጋብቻ ፡ ንጹሕ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መዋለድም ፡ ርኵሰት ፡ እንደሌለበት ፡ እንናገራለን ፤ እግዚአብሔር ፡ ሕዝቡ ፡ ይበዙ ፡ ዘንድ ፡ አዳምንና ፡ ሔዋንን ፡ ፈጥሮአቸዋልና ።

ከሥጋ ፡ ጋር ፡ የማትሞትና ፡ የማትጠፋ ፡ ነፍስ ፡ በሥጋችን ፡ እንዳለን ፡ እናስተውል ፤ እኛስ ፡ ከሃይማኖት ፡ የፉነኑት ፡ በእኛ ፡ ዘንድ፡ የረከሱ፡ናቸውና፡መለያየትን፡ሕገ፡ወጥ፡መሆንንም፡ሁሉ፡እንጸየፋለን።

ዳግመኛም ፡ የጻድቃንና ፡ የኃጥአን ፡ የሙታን ፡ ትንሣኤ ፡ እንዳለ ፤ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ መጠን ፡ ፍዳውን ፡ የሚቀበልበት ፡ የፍርድ ፡ ቀን ፡ እንዳለ ፡ እናምናለን ።

ዳግም ፡- ክርስቶስ ፡ የአብ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ሆኖ ፡ የሰውን ፡ ወገን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋር ፡ ያስታረቀ ፡ በእውነት ፡ ሰው ፡ የሆነ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሰው ፡ በመሆኑ ፡ ምንም ፡ ሕፀፅ ፡ እንደሌለበት ፡ እናምናለን ።

እንግዲህ ፡ እንደ ፡ አይሁድ ፡ አንገዘር ፤ አሪትንና ፡ ነቢያትን ፡ የሚፈጽማቸው ፡ እንደ ፡ መጣ ፡ እናውቃለንና ፤ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ መምጣቱን ፡ በተስፋ ፡ የሚጠባበቁት ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከይሁዳ ፡ ከፅሜይም ፡ ሥር ፡ የተገኘ ፡ ሥልጣኑ ፡ በትከሻው ፡ ላይ ፡ የሆነ ፡ ነው ፤ ለእርሱ ፡ ምስጋና ፡ ገናንነት ፡ ክብር ፡ በረከት ፡ ውዳሴ ፡ ቃለ ፡ መዝሙርም ፡ ይገባዋል ። ዛሬም ፡ ዘወትርም ፡ ለዘለዓለሙም ፤ አሜን ።

## የቅዱስ ፡ አትናቴዎስ ፡ የሃይማኖት ፡ ሥርዐት ።

ለመዳን፡ ፈቃደኛነት፡ ያለው፡ ሰው፡ ሁሉ፡ይህን፡ በሁሉ፡ ዘንድ፡ ያለችው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የምታምነውን ፡ ሃይማኖት ፡ ይጠብቅ ፡ ዘንድ ፡ ይገባዋል ። ስለዚህም ፡ ደኅንነትን ፡ እንዳያጣ ፡ ይህን ፡ እምነት ፡ መጠበቅ ፡ ያስፈልገዋል ።

በሁሉ ፡ ዘንድ ፡ ያለችው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሃይማኖትም ፡- አካላትን ፡ ሳንደባልቅና ፡ ህላዌን ፡ ሳንከፍል፡ አንዱን፡ አምላክ ፡ በሦስትነት ፡ ሦስትነትንም ፡ በአንድነት፡ እናመልክ፡ ዘንድ ፡ ነው ። አንዱ ፡ አካል ፡ የአብ ፡ ሲሆን ፡ ሁለተኛው ፡ የወልድ ፡ ሦስተኛውም ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ የአብና ፡ የወልድ ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ መለኮት ፡ አንዲት ፡ ናት ። ክብራቸውም ፡ የተተካከለ ፡ ነው ። ግርማቸውም ፡ የአንዲት ፡ ዘለዓለማዊነት ፡ ናት ።

አብ ፡ እንዳለ ፡ እንዲሁም ፡ ወልድ ፡ አለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ አለ ። አብ ፡ አልተፈጠረም ፡ ወልድም ፡ አልተፈጠረም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ አልተፈጠረም ። አብ ፡ አይወሰንም ፡ (በማስተዋል ፡ ረገድ) ፡ ወልድም ፡ አይወሰንም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ አይወሰንም ። አብ ፡ ዘለዓለማዊ ፡ ነው ፡ ወልድም ፡ ዘለዓለማዊ ፡ ነው ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ዘለዓለማዊ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ በዘለዓለማዊነት ፡ ያለ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ ሦስት ፡ ናቸው ፡ አንልም ።





እንዲሁም፡ የማንወስነውና፡ ያልተፈጠረ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ እንጅ፡ የማንወስናቸውና ፡ ያልተፈጠሩ ፡ ሦስት ፡ ናቸው ፡ አንልም ። እንደዚሁም ፡ አብ ፡ ሁሉን ፡ ቻይ ፡ ነው ፡ ወልድም ፡ ሁሉን ፡ ቻይ ፡ ነው ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ሁሉን ፡ ቻይ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ሁሉን ፡ የሚችል ፡ አንድ ፡ ነው ፡ እንላለን ፡ እንጅ ፡ ሦስት ፡ ሁሉን ፡ ቻዮች ፡ አንልም ።

እንደዚሁም ፡ አብ ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ ወልድም ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ አምላክ ፡ ነው ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ ሦስት ፡ አማልክት ፡ አንልም ።

እንደዚሁም ፡ አብ ፡ ጌታ ፡ ነው ፡ ወልድም ፡ ጌታ ፡ ነው ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ጌታ ፡ ነው ፤ ስለሆነም ፡ አንድ ፡ ጌታ ፡ እንጅ ፡ ሦስት ፡ ጌቶች ፡ አንልም ። በክርስትና ፡ እውነትነት ፡ እንደምንለው ፡- አካል ፡ ሁሉ ፡ እያንዳንዱ ፡ በየራሱ ፡ አምላክና ፡ ጌታ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፤ ሦስት ፡ አማልክትና ፡ ሦስት ፡ ጌቶች ፡ ከማለት ፡ የሐዋርያዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አምልኮ ፡ እምነት ፡ ትከለክለናለች ።

አብ ፡ ከማንም ፡ አልተሠራም ፡ አልተፈጠረም ፡ አልተወለደም፤ ወልድም ፡ በአብ ፡ ነው ፤ ስለሆነም ፡ ተወልዶ ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ ተሠርቶ ፡ ወይንም ፡ ተፈጥሮ ፡ አይደለም ። መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ በአብ ፡ ነው ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ሠርፆ ፡ እንጅ ፡ ተሠርቶ ፡ ወይንም ፡ ተፈጥሮ ፡ ወይም ፡ ተወልዶ ፡ አይደለም ።

እንግዲህ ፡ አንድ ፡ አብ ፡ አለ ፡ እንጅ ፡ ሦስት ፡ አባቶች ፡ የሉም፤ አንድ ፡ ልጅ ፡ አለ ፡ እንጅ ፡ ሦስት ፡ ልጆች ፡ (ወልዶች) ፡ የሉም ፤ አንድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አለ ፡ እንጅ ፡ ሦስት ፡ መንፈስ ፡ ቅዱሶች ፡ የሉም ። በዚችም ፡ ሦስትነት ፡ መቅደም ፡ መከታተል ፡ የለም ፤ ከባልንጀራውም ፡ የሚበልጥና ፡ የሚያንስ ፡ የለም ። ሦስቱ ፡ አካላቶቻቸው ፡ እየራሳቸው ፡ የአንዲት፡ ዘለዓለማዊነት ፡ ናቸው። እየራሳቸውም፡ የተተካከሉ ፡ ናቸው ። እንግዲያውስ ፡ እንደ ፡ ተባለው ፡ ሁሉ ፡ ሥላሴን ፡ በአንድነት ፡ አንድነትንም ፡ በሥላሴ ፡ ማመን ፡ ይገባል ።

መዳንን ፡ የሚሻ ፡ በሥላሴ ፡ እንደዚሁ ፡ ያስብ ።

ዳግም ፡ ስለ ፡ ዘለዓለም ፡ ሕይወቱ ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ትሥጉት ፡ በሚገባ ፡ ያምን ፡ ዘንድ ፡ ለሰው ፡ ያስፈልገዋል ።

ኦርቶዶክሳዊት ፡ ሃይማኖታችን፡ ስትባል፡ ይህንኑ ፡ ማመናችን ፡ ማለት ፡ እንደ ፡ መሆንዋ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አምላክና ፡ ሰው ፡ ነው ። እምቅድመ ፡ ዓለም ፡ ከአብ ፡ ህላዌ ፡ በመወለዱ ፡ አምላክ ፡ ነው ፤ ድኅረ ፡ ዓለምም ፡ ከእናቱ ፡ ህላዌ ፡ በመወለዱ ፡ ሰው ፡ ነው ። በሰው ፡ ነፍስና ፡ ሥጋ ፡ ጥዩቅ ፡ ሰው ፡ ሆኖ፡ ፍጹም ፡ አምላክ ፡ ነው ። በመለኮቱም ፡ ከአብ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ሲሆን ፡ የባሪያውን ፡ መልክ ፡ ወሰደ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ አምላክና ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ መሆኑ ፡ አንድ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ እርሱ ፡ ሁለት ፡ አይደለም ። አንድ ፡ ነው ፤ ግን ፡ መለኮቱ ፡ ሰውነትን ፡ በመገንዘብ ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ መለኮት ፡ ወደ ፡ ሥጋ ፡ በመለወጥ ፡ አይደለም ። ፈጽሞ ፡ ተዋሐደ ፤ ስለሆነ ፡ በባሕርይ ፡ መደባለቅ ፡ ሳይሆን ፡ በአካል ፡ መዋሐድ ፡ ነው ። ነፍስና ፡ ሥጋ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ እንደሚያሰኝ ፡ ሁሉ ፡ አምላክና ፡ ሰው ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ።

እርሱም ፡ እኛን ፡ ለማዳን ፡ መከራን ፡ ተቀበለ ፡ ወደ ፡ ሲኦልም፡ ወረደ ። በሦስተኛም ፡ ቀን ፡ ከሙታን ፡ ተለይቶ ፡ ተነሣ ። ወደ ፡ ሰማይም ፡ ዐረገ ። ሁሉን ፡ በሚችል ፡ በእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ቀኝ ፡ ተቀመጠ ። በሕያዋንና ፡ በሙታን ፡ ለመፍረድም ፡ ከዚያ ፡ ይመለሳል ።

እርሱም ፡ በሚመጣበት ፡ ጊዜ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በሥጋው ፡ ይነሣል ። ባደረገውም ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ይቈጣጠረዋል ። መልካም ፡ የሠሩ ፡ ወደ ፡ ዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ ክፉ ፡ የሠሩም ፡ ወደ ፡ ዘለዓለም ፡ እሳት ፡ ይገባሉ ።

ከሁሉ ፡ በላይ ፡ የምትሆን ፡ የሐዋርያዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ ይህች ፡ ናት ፤ ያላመናት ፡ ሰውም ፡ ይድን ፡ ዘንድ ፡ አይቻለውም ።

ለአብ ፡ ለወልድ ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፤ በመጀመሪያ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ አሁንም ፡ እንዳለ ፤ ለዘወትርም ፡ እንደሚኖር ፡ ለዘለዓለም ፤ አሜን ።



## የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የመምህርነቱ ፡ ማስገንዘቢያ ።

አንድም ፡ የሚወደኝ ፡ ቢኖር ፡ ቃሌን ፡ ይጠብቃል ፤ አባቴም ፡ ይወደዋል ፤ ወደ ፡ እርሱም ፡ እንመጣለን ፤ በእርሱም ፡ ዘንድ ፡ ማኖሪያ ፡ እናደርጋለን ። የማይወደኝ ፡ ቃሌን ፡ አይጠብቅም ፤ የምትሰሙትም ፡ ቃል ፡ የላከኝ ፡ የአብ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የእኔ ፡ አይደለም ። ከእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ስኖር ፡ ይህን ፡ ነግሬአችኋለሁ ። አብ ፡ በስሜ ፡ የሚልከው ፡ ግን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የሆነው ፡ አጽናኝ ፡ እርሱ ፡ ሁሉን ፡ ያስተምራችኋል ፤ እኔም ፡ የነገርኋችሁን ፡ ሁሉ ፡ ያሳስባችኋል ። ሰላሜን ፡ እተውላችኋለሁ ፡ ሰላሜን ፡ እሰጣችኋለሁ ፤ እኔ ፡ የምሰጣችሁ ፡ ዓለም ፡ እንደሚሰጥ ፡ አይደለም ። ልባችሁ ፡ አይታወክ ፡ አይፍራም ። ዮሐ ፡ ፲፬ ፡ ፳፫-፳፯ ።

## የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የሊቀ ፡ ካህንነቱ ፡ ጸሎት ።

ኢየሱስም ፡ ይህን ፡ ተናግሮ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ዓይኖቹን ፡ አነሣና፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ አባት ፡ ሆይ ፡ ሰዓቱ ፡ ደርሶአል ፤ ልጅህ ፡ ያከብርህ ፡ ዘንድ ፡ በሥጋም ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ እንደ ፡ ሰጠኸው ፡ ሁሉ ፡ ለሰጠኸው ፡ ሁሉ ፡ የዘለዓለምን ፡ ሕይወት ፡ ይሰጣቸው ፡ ዘንድ ፡ ልጅህን ፡ አክብረው ፤ እውነተኛ ፡ አምላክ ፡ የሆንህ ፡ አንተን ፡ ብቻ ፡ የላክኸውንም ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ ፡ ይህች ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ ናት ። እኔ ፡ ላደርገው ፡ የሰጠኸኝን ፡ ሥራ ፡ ፈጽሜ ፡ በምድር ፡ አከበርሁህ። አሁንም ፡ አባት፡ ሆይ ፡ ዓለም፡ ሳይፈጠር ፡ በአንተ ፡ ዘንድ ፡ በነበረኝ ፡ ክብር ፡ አንተ ፡ በራስህ ፡ ዘንድ ፡ አክብረኝ ።

ከዓለም ፡ ለሰጠኸኝ፡ ሰዎች ፡ ስምህን፡ ገለጥሁላቸው። የአንተ ፡ ነበሩ ፡ ለእኔም ፡ ሰጠሃቸው፡ ቃልህንም፡ ጠብቀዋል ። የሰጠኸኝ፡ ሁሉ ፡ ከአንተ ፡ እንደሆነ ፡ አሁን፡ ያውቃሉ ፤ የሰጠኸኝን ፡ ቃል ፡ ሰጥቻቸዋለሁና ፡ እነርሱም፡ ተቀበሉት ፡ ከአንተም ፡ ዘንድ፡ እንደ ፡ ወጣሁ ፡ በእውነት ፡ አወቁ ። አንተም ፡ እንደ ፡ ላክኸኝ ፡ አመኑ። እኔ፡ ስለ፡ እነዚህ ፡ እለምናለሁ። ስለ፡ ዓለም፡ አልለምንም፡ ስለ፡ ሰጠኸኝ ፡እንጅ ፤ የአንተ ፡

ናቸውና ። የእኔም ፡ የሆነ ፡ ሁሉ፡ የአንተ ፡ ነው ፤ የአንተውም፡ የእኔ ፡ ነው ። እኔም ፡ ስለ፡ እነርሱ፡ ተመስግኛለሁ ፡ ከዚህም፡ በኋላ ፡ በዓለም ፡ አይደለሁም ። እነእርሱም ፡ በዓለም ፡ ናቸው ፡ እኔም ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ እመጣለሁ ። ቅዱስ ፡ አባት ፡ ሆይ፡ እነዚህን ፡ የሰጠኸኝን፡ እንደእኛ ፡ አንድ ፡ እንዲሆኑ ፡ በስምህ ፡ ጠብቃቸው ። ከእነርሱም ፡ ጋር ፡ በዓለም ፡ ሳለሁ ፡ የሰጠኸኝን ፡ በስምህ ፡ እኔ ፡ እጠብቃቸው ፡ ነበር ፤ ጠበቅኋቸውም ። መጽሐፉም ፡ እንዲፈጸም ፡ ከጥፋት ፡ ልጅ ፡ በቀር ፡ ከእነርሱ ፡ ማንም ፡ አልጠፋም ። አሁንም ፡ ወደ፡ አንተ፡ እመጣለሁ፤ በእነርሱም ፡ ዘንድ ፡ ደስታዬ ፡ የተፈጸመ ፡ እንዲሆንላቸው ፡ ይህን ፡ በዓለም ፡ እናገራለሁ ። እኔ ፡ ቃልህን ፡ ሰጥቻቸዋለሁ ። እኔም ፡ ከዓለም ፡ እንዳይደለሁ፡ ከዓለም ፡ አይደሉምና፡ ዓለም ፡ ጠላቸው ። ከክፉ፡ እንድትጠብቃቸው ፡ እንጅ ፡ ከዓለም ፡ እንድታወጣቸው ፡ አልለምንም ። እኔ ፡ ከዓለም ፡ እንዳይደለሁ ፡ ከዓለም ፡ አይደሉም ። በእውነትህ ፡ ቀድሳቸው ። ቃልህ ፡ እውነት ፡ ነው ። ወደ ፡ ዓለም ፡ እንደ ፡ ላከኸኝ ፡ እንዲሁ ፡ እኔ ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ ላክኋቸው ። እነርሱም ፡ ደግሞ ፡ በእውነት ፡ የተቀደሱ ፡ እንዲሆኑ ፡ እኔ ፡ ራሴን ፡ ስለ ፡ እነርሱ ፡ እቀድሳለሁ ።

ሁሉም ፡ አንድ ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ ከቃላቸው ፡ የተነሣ ፡ በእኔ ፡ ስለሚያምኑ ፡ ደግሞ ፡ እንጂ ፡ ስለ ፡ እነዚህ ፡ ብቻ ፡ አልለምንም ፤ አንተ ፡ እንደ ፡ ላከኸኝ ፡ ዓለም ፡ ያምን ፡ ዘንድ ፡ አንተ ፡ አባት ፡ ሆይ ፡ በእኔ ፡ እንዳለህ ፡ እኔም ፡ በአንተ ፡ እነርሱ ፡ ደግሞ ፡ በእኛ ፡ አንድ ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ እለምናለሁ ። እኛም ፡ አንድ ፡ እንደሆንን ፡ አንድ ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ እኔም፡ በእነርሱ ፡ አንተም፡ በእኔ ፡ ስትሆን ፡ በአንድ ፡ ፍጹማን ፡ እንዲሆኑ ፡ የሰጠኸኝን ፡ ክብር ፡ እኔ ፡ ሰጥቻቸዋለሁ ። እንዲሁም ፡ ዓለም ፡ አንተ ፡ እንደ ፡ ላከኸኝ፡ በወደድኸኝም ፡ መጠን ፡ እነርሱን ፡ እንደ ፡ ወደድሃቸው ፡ ያውቃል ። አባት ፡ ሆይ ፡ ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ ስለ ፡ ወደድኸኝ ፡ የሰጠኸኝን ፡ ክብሬን ፡ እንዲያዩ ፡ እኔ ፡ ባለሁበት ፡ የሰጠኸኝ ፡ እነርሱ ፡ ደግሞ ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ እወዳለሁ ። ጻድቅ ፡ አባት ፡ ሆይ ፡ ዓለም ፡ አላወቀህም ፤ እኔ ፡ ግን ፡ አወቅሁህ ፤ እነዚህም ፡ እንደ ፡ ላከኸኝ ፡ አወቁ ፤ እኔንም ፡ የወደድህባት ፡ ፍቅር ፡ በእነርሱ ፡ እንድትሆን ፡ እኔም ፡ በእነርሱ ፡ ስምህን ፡ አስታወቅኋቸው ፡ አስታውቃቸውማለሁ ። አሜን ።



## ፩ኛ ፡ ክፍል ።

### ፩ኛ ፡ አንቀጽ ።

### የእግዚአብሔር፡ አምላክነት ።

የማይታይና ፡ የማይወሰን ፡ መለወጥ፡ ወይም፡
ሌላ ፡ ተጨማሪ ፡ ነገር ፡ በሌለበት ፡ ባሕርዩ ፡ በራሱ ፡ ፩ ፡ ጢሞ ፡ ፮ ፡ ፲፮ ። ሚልክ ፡ ፫ ፡ ፮ ።
የሚኖር ፡ አካላዊ ፡ መንፈስ ፡ የፈጠራቸውን ፡ ሰማይ ፡ ዮሐ ፡ ፬ ፡ ፳፬ ።
ንና ፡ ምድርን ፡ ያሉባቸውንም ፡ ሁሉ ፡ እንደ፡ ጠበቀ ፡ ፡ ነህ ፡ ፱ ፡ ፮ ።
የሚታየውንና ፡ የማይታየውን ፡ የሚገዛ ፤ በእውነ ፤ ኤር ፡ ፲ ፡ ፲-፲፫ ።
ተኛ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክነት ፡ ሕያው ፡ ሆኖ ፡ የሚ
ኖር ፤ አንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ አለ ። ። ዳንኤ ፡ ፮ ፡ ፳፮ ፡ ፳፯ ።

እርሱም ፡ በጽድቅና ፡ በርትዕ፡ በፍቅርና፡ በእ
ውነት ፡ በቸርነትና ፡ በጥበብ ፡ ወሰን ፡ የሌለበትን ፡ ዮና ፡ ፬ ፡ ፪ ። ዘፀአ ፡ ፴፫ ፡ ፲፱-፳፪ ።
መለኮታዊ ፡ ባሕርዩን ፡ እየገለጸ ፡ በሦስቱ፡ አካላቶቹ ፡ ፡ ዘዳግ ፡ ፴፪ ፡ ፫ ፡ ፬ ።
አብ ፡ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እንደ ፡ መሆኑና ፡
እንደ ፡ መባሉ ፡ የምክር ፡ የኃይል ፡ የገናና ፡ ክብር ፡ ፡ ማቴ ፡ ፳፰ ፡ ፲፱ ።
የግርማ ፡ የዘለዓለማዊነት ፡ የጋራ ፡ መተካከልንና ፤ ዮሐ ፡ ፲፯ ፡ ፲፫-፲፭ ። ሮሜ ፡ ፰ ፡ ፳፯-፴፬ ።
የፈቃድ ፡ የሥምረት ፡ መስማማትን ፤ መከፋፈልና ፡ ፤ ዮሐ ፡ ፫ ፡ ፴፬ ፡ ፴፭ ።
መጨረሻ ፡ በሌለበት ፡ በሥላሴነቱ ፡ የህላዌ ፡ አንድ
ነት ፡ እንደሚያጠይቅ ፡ እናምናለን ። ሉቃ ፡ ፲ ፡ ፳፪ ። ። ሮሜ ፡ ፲፩ ፡ ፴፮ ።
ዮሐ ፡ ፲ ፡ ፴ ።

ይህንም ፡ አግናጥዮስ ፡ ሰማዕትና ፡ የአንጾኪያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ በሃይማኖተ ፡ አበው ፡—

ጥቅስ ፡ "እግዚአብሔር ፡ ገባሬ ፡ ኵሉ ፡ ፍጥረት ፡ መዋዒ ፡ መዓርግ ፡ ወሣሜተ ፡ ኵሉ ፡ ህላዌ ፡ በሠለስቱ ፡ አካላት ፡ ፍጹመ ፡ መልክዕ ፡ ወገጽ ፡ ነቢሮ ፡ ዲበ ፡ መንበረ ፡ ስብሐቲሁ ፡ ዘይእኅዝ ፡ ኵሎ ።" ካለው ፡ ጋር ፡ ማስተያየት ፡ ነው ። ኢሳ ፡ ፵፫ ፡ ፲-፲፰ ።

በዚሁ ፡ እምነታችንም ፡ በፍጹም ፡ ባሕርዩና ፡ በአምላ ክነቱ ፡ የሚጠራጠሩትን ፤ ወይም ፡ የአምላክነት ፡ መነሻ ፡ ከክፋትና ፡

ከበጎነት ፡ ምንጭ ፡ ነውና ፡ ሁለት ፡ አማልክት ፡ አሉ ፡ የሚሉትን ፤ እንዲሁም ፡ አካልን ፡ በመደባለቅ ፡ አንድ ፡ ገጽ ፡ የሚሉትን ፤ ዳግም ፡ ህላዌን ፡ የሚከፋፍሉና ፡ በሥላሴ ፡ ሕፀፅ ፡ እንዳለ ፡ የሚያስተምሩትን ፡ ሁሉ ፤ እንርቃቸዋለን ።





## ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ አብ ።

በሥሉስ ፡ ቅዱስ ፡ ውስጥ፡ በተለይም፡ ስለ ፡
አካል ፡ ለመናገር ፡ ስንጀምር ፡ ያለ ፡ ልጅ፡ እውነተኛ፡ ፡ ዘፍጥ ፡ ፲፰ ፡ ፪ ።
አባት ፡ እንደማይኖር ፡ በመረዳት ፡ እግዚአብሔር ፡ ፡ ምሳ ፡ ፴ ፡ ፬ ።
አብ ፡ አስቀድሞ ፡ "አብ፡ " የተባለበትን ፡ አኳኋንና ፡
ጊዜ ፡ እንዴት ፡ ይሆን ? ብለን ፡ በምንጠይቅበት ፡
ቅጽበት ፡ ወዲያው ፡- እንደዚህ፡ ዓለም ፡ ልደት ፡ ሳይ
ሆን ፡ በማይመረመር ፡ አኳኋን ፡ ለሚወደውና ፡ በሕ ፡ መዝ ፡ ፪፡ ፯፡ ፲፪ ።
ፁኑ ፡ (በዕቅፉ ፡) ላለው ፡ አንድ ፡ ብቸኛ ፡ ዘለዓለማዊ ፡ ፡ ዮሐ ፡ ፫ ፡ ፴፭ ፡
ልጅ ፡ (ወልድ ፡) አባት ፡ በሆነበት ፡ አገባብና ፡ አባ ማቴ ፡ ፲፩ ፡ ፳፯ ፡
ትነቱ ፡ ከዘለዓለም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እናገኛለን ። ። ዮሐ፡ ፭፡፭፡፲፬-፲፰፡

በሥላሴ ፡ አንድነትም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡
ከአብ ፡ የሠረፀ ፡ የአብና ፡ የወልድ ፡ መንፈስ ፡ እንደ ፡ ፡ ዮሐ ፡ ፲፭ ፡ ፳፮ ፡
መሆኑ ፡ ወልድ ፡ በአብ ፡ አብም ፡ በወልድ ፡ ፡ ዮሐ፡ ፲፬፡ ፲-፲፩፡
የሚኖርና፡ በማናቸውም፡ ረገድ ፡ ሕፀፅ ፡ (ጉድለት ፡) ፡ ዮሐ፡ ፲፬፡ ፱-፲፩ ።
በሌለባት ፡ በአንዲት ፡ ፍጽምት ፡ ህላዌ ፡ ከወልድና ፡ ፡ ኢሳ ፡ ፮ ፡ ፩-፫ ፡
ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጋር ፡ ተተካክሎ ፡ በፈቃድና ፡ በ ፡ ማቴ ፡ ፳፰ ፡ ፲፱ ፡
ሥምረትም ፡ ተስማምቶ ፡ በወልድና ፡ በመንፈስ ፡ ቅ ፡ ዮሐ፡ ፲፬፡ ፳፫-፳፮፡
ዱስ፡ ለሚከናወነው፡ መለኮታዊ፡ ኅሳብ፡ መነሻ፡ ነው። ። ሮሜ፡ ፲፩፡ ፴፮ ።

በዓለም ፡ ላይ፡ ካለው፡ የፍቅሩ፡ ባለጸግነት ፡
የተነሣ ፡ አንድ ፡ ልጁን ፡ ለቤዛነት ፡ በመስጠት፡ ያቆ ፡ ዮሐ ፡ ፫ ፡ ፲፮ ።
መውን ፡ የመሥዋዕትን ፡ ማስተሥረያ ፡ አምነው ፡
ለሚመጡለት ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ኃጢአታቸውን ፡ ፡ ሮሜ ፡ ፫ ፡ ፳፭ ።
ይቅር ፡ ብሎ ፡ ልጆቹ ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ መብት ፡ ስለ ፡ ቈላስ ፡ ፪ ፡ ፲፫ ፡
ሚሰጣቸው ፡ በዚሁ ፡ ልጅነታቸው ፡ "አባ ፡ አባታ ፡ ዮሐ፡ ፩፡ ፲፪፡ ፲፫ ።
ችን ፡ " ብለው ፡ የሚጠሩበት ፡ መንፈስ ፡" የፍጥ ፡ ሮሜ፡ ፰፡ ፲፭፡ ፲፯ ።
ረት ፡ አባት ፡ ካሰኘው ፡ የመፍጠር ፡ ጉዳይ ፡ ይበ
ልጥኑ ፡ የሚያረካ ፡ ነው ። ። ኢሳ፡ ፷፫፡ ፰፡ ፲፯ ።

እነርሱንም፡ ለምስጋናው፡ መመኪያ፡አድርጎ፡ ኤፌ ፡ ፩ ፡ ፭ ፡ ፮ ።
ሲመርጣቸው ፡ በልጁ ፡ መልክ ፡ ምሳሌ ፡ ሆነው ፡ ፡ ሮሜ ፡ ፰ ፡ ፳፱-፴፯ ።
ክብሩን ፡ ይወርሱ ፡ ዘንድ ፡ ከጥንት ፡ በመደበው ፡
ፈቃዱ ፡ መሠረት ፡ ከእጁ ፡ እንደማይጥላቸው ፡ እና ፡ ኤፌ ፡ ፩ ፡ ፲፩ ።
ምናለን ። ። ዮሐ ፡ ፲ ፡ ፳፯-፳፱ ።

ጥቅስ ፡ "ነአምን ፡ በ፩ ፡ አምላክ ፡ ገባሬ ፡ ኵሉ ፡ ፍጥረት ፡ አብ ፡ ለእግዚእነ ፡ ወአምላክነ ፡ ወመድኃኒነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እስመ ፡ አልቦ ፡ ውስተ ፡ ህላዌሁ፡ አመክንዮ።" ትርጓሜውን፡ በሐዋርያት ፡ አመ ክንዮ ፡ ተመልከት ።

በዚህም ፡ እምነታችን ፡ አብ ፡ የወልድና ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ባሕርይ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከሥላሴ ፡ አንዱ ፡ አካል ፡ አይደለም ፤ የሚለውን ፡ ትምህርት ፡ አለመከተላችንን ፡ እንገልጻለን ።



፫ኛ ፡ አንቀጽ ።

## ስለ ፡ መጽሐፍ፡ ቅዱስ ።

የብሉይና ፡ የሐዲስ፡ ኪዳን፡ ቅዱሳት፡ መጻሕ ፡ ማቴ ፡ ፲፫ ፡ ፶፪ ።
ፍት ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሃይማኖት ፡ ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፩ ፡ ፲-፲፪ ።
ለደኅንነታችን ፡ የሚገባ ፡ ትምህርት ፡ የምናገኝባ ዮሐ ፡ ፭ ፡ ፴፱ ፡ ፵፮ ።
ቸው ፤ በተግሣጽና ፡ በምክርም ፡ ለቅን ፡ አድራጎትና፡ ፤ ዮሐ ፡ ፳ ፡ ፴፩ ።
ሰማያዊ ፡ አባታችን ፡ ለሚፈልግብን ፡ ፍጹምነት ፡ ፡ ሚክ ፡ ፯ ፡ ፳ ።
እስክንበቃ ፡ ድረስ ፡ በመልካም ፡ አስተዳደግ ፡ የምና
ድግባቸው ፡ ናቸው ። ። ፪ ፡ ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፲፬-፲፯ ፡

እነዚህም ፡ መጻሕፍት፡ መንፈስ፡ ቅዱስ፡ በተ አሞጽ ፡ ፫ ፡ ፯ ።
ለይ ፡ ለዚሁ ፡ ሥራ ፡ በመረጣቸውና ፡ በመራቸው ፡ ፪ ፡ ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፪ ፡ ፲፮ ።
በቅዱሳን ፡ ነቢያትና ፡ ሐዋርያት ፡ በኩል ፡ ሲጻፉ ፤ ፤ የሐዋ ፡ ሥ ፡ ፳፯ ፡ ፳፱ ፡
በቀኖናቸው ፡ ተወስነው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የመ
ነጩ ፡ እንጂ ፡ መነሻቸው ፡ ፍጥረታዊ ፡ ሰው ፡ እንዳ ፡ ፪ ፡ ቆሮ ፡ ፲ ፡ ፲፫-፲፭ ።
ልሆነ ፡ የገዛ ፡ ራሳቸው ፡ አረጋግጠዋል ። ። ፪ ፡ ጴጥ ፡ ፩ ፡ ፲፱-፳፩ ።

እንደዚሁም ፡ ደግሞ፡ ስለ፡ ዓለም፡ ፍጥረት ፡ ፡ ፪ ፡ ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፭-፯ ።
ስለ ፡ ሰው ፡ መጀመሪያና ፡ መጨረሻ ፡ በሚፈለገው ፡ ፡ ዘፍ ፡ ፩ ፡ ፳፯ ።
ጥናት ፡ ሁሉ ፡ ጥብቅ ፡ በሆነው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፡ ራእ ፡ ፳ ፡ ፯ ፡ ፲፩-፲፭ ፡
ፈቃድ ፡ ክበብ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ መንፈሳዊ ፡ ጠባ
ያቸውን ፡ ሲገልጹ ፡ የኅብረተ ፡ ቃላቶቻቸው ፡ አቅ ፡ ሮሜ ፡ ፱ ፡ ፳፰ ።
ዋም ፡ የዓላማቸው ፡ አንድ ፡ መንፈስ ፡ መሆን፡ ቃሉ ፡ ፡ ሉቃ ፳፬ ፳፯ ፴፬-፴፯
የእግዚአብሔር ፡ የሆነ ፡ ጠቅላላ ፡ አንድ ፡ መጽሐፍ ፡ ፡ ፪ ፡ ቆሮ ፡ ፪ ፡ ፲፯ ።
ቅዱስ ፡ ሊያሰኛቸው ፡ ችሎአል ። ። ፪ ፡ ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፲፭ ።

በውሳኔ፡ ረገድም፡ በዱሮ፡ አመዳደብ፡ ፍሊጋ ፡ (አሠር) ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ ክፍ ሎች ፡ እያንዳንዳቸው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ማሳሰብ ፡
ለመጻፋቸው ፡ መረጃ ፡ የሚመዘኑበት ፡ መጠን ፡ ደራ ፡ ፪ ፡ ቆሮ ፡ ፲ ፡ ፲፫-፲፭ ።
ሲው ፡ ወይም ፡ ጸሐፊው ፡ ማን ፡ መሆኑን ፡ ማወቅ ፡ ደራሲው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡

በርግጥ ፡ መረዳት ፡ የደራሲውም ፡ ጽሑፍ ፡ ከእግዚአ
ብሔር ፡ መንፈስ ፡ ወይም ፡ ኀሳብ ፡ ጋር ፡ ያለስሕ
ተት ፡ የሚስማማ ፡ መሆኑን ፡ በጥንቃቄ ፡ መገንዘብ ፡
ስለ ፡ ሆነ ፤ ዋና ፡ ቀኖናቸው ፡ (የመጻሕፍቶቹ ፡ መለ ፤ ገላ ፡ ፭ ፡ ፳ ፡ ፱ ።
ኪያ ፡) ይህንኑ ፡ የመንፈሳዊ ፡ ጠባያቸው ፡ ድንጋጌ ፡
መሆኑን ፡ የጥንትዋ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን፡ በተስማማች ፤ ምሳ ፡ ፴ ፡ ፭ ፡ ፮ ።
በት ፡ መሠረት ፡ እናምናለን ። ። ራዕ፡ ፳፪፡ ፲፰፡ ፲፱።

ስለዚህም ፡ ዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፦

ጥቅስ ፡ "ይደልወነ ፡ ናጽምዕ፡ ቃላተ ፡ መለኮት፡ ከመ፡ ኢይባዕ፡ ውስተ ፡ አልባቢነ ፡ ቃል ፡ ነኪር ።

ትርጓሜ፡ ባዕድ ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ልባችን ፡ እንዳይገባ ፡ ቃላተ ፡ መለኮትን፡ ማድመጥ፡ ይገባናል፡" ያሰንን፡ በመገንዘብ ፡ በእግዚአብሔር፡ ቃል ፡ ብቻ ፡ ተወስነን ፡ ከቁርዓን ፡ እርሱንም ፡ ከሚመሳሰሉ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የልብ ፡ ወለድ ፡ መጻሕፍት ፡ እምነት ፡ እንርቃለን ። የሐዋ ፡ ፲፱ ፡ ፲፱ ።

ሳዊሮስ ፡ ዘእስሙናይን ፦

ጥቅስ ፡ "መጻሕፍት ፡ አምላካውያት ፡ እስትንፋስ ፡ አፉሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ነዮን ። ወዓዲ፡ ይቤ ፡ እስመ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ቃሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ፈጣሪ ፡ ወውእቱ ፡ ክቡር ፡ ወየዓቢ ፡ እምልብ ፡ ዘፍጡር*።

ትርጓሜ፡ መጻሕፍት ፡ አምላካውያት ፡ የእግዚአብሔር ፡ እስትንፋስ ፡ ናቸው ። እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ሁሉን ፡ የፈጠረ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ነውና ፡ እርሱም ፡ ክቡር ፡ ከፍጡር ፡ ኅሳብም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ፡" ሲል ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቃል፡ ምስጋና ፡ ሰጠ ። ዕብ ፡ ፬ ፡ ፲፪ ። ኤር ፡ ፳፫ ፡ ፳፱ ።

ቄርሎስም ፡ በግጻዌ ፡ ድርሳኑ ፦

ጥቅስ ፡ "ለትምህርተ ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ግሙራ ፡ አልቦ ፡ ዘይጸግቦ ፡ ወኢመኑሂ ፡ ወፈድፋደሰ ፡ እለ ፡ ይሔልዩ ፡ ጥበበ ፡ ወአጥረዩ፡





አእምሮ ፡ ማሕየዌ ፡ ውስተ ፡ አልባቢሆሙ ። እስመ ፡ ጽሑፍ ፡ እኮ ፡ በኀብስት ፡ ዘየሐዩ ፡ ሰብእ ፡ አላ ፡ በኵሉ ፡ ነገር ፡ ዘይወፅእ ፡ እምአፉሁ ፡ ለእግዚአብሔር ። ሲሲተ ፡ ልብ ፡ ቃሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ውእቱ ፡ ወኀብስት ፡ መንፈሳዊ ፡ ዘያጸንዕ ፡ ኃይለ ፡ ሰብእ ።

ትርጓሜ፡ የቅዱሳት ፡ መጻሕፍትን ፡ ትምህርት ፡ ማናቸውም ፡ ቢሆን ፡ ከቶ ፡ የሚጠግበው ፡ የለም ። ይልቁንም ፡ ጥበብን ፡ ለሚሹና ፤ በልባቸው ፡ ውስጥ ፡ ማሕየዊ ፡ አእምሮን ፡ ለተገነዘቡ ፡ ሰው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ አፍ ፡ በምትወጣ ፡ ቃል ፡ እንጅ ፡ በእንጀራ ፡ ብቻ ፡ እንዳይድን ፡ ተጽፎአልና፡ የልቡና ፡ ምግብ፡ ሰውንም ፡ የሚያበረታ ፡ መንፈሳዊ ፡ ኀብስት ፡ የእግዚአብሔር፡ ቃል ፡ ነው።" ሲል ፡ የቅዱሳት ፡ መጻሕፍትን፡ ጥቅም ፡ አስረድቶአል ። መዝ፡ ፻፲፱ ፡ ፺፯-፻፬ ። ማቴ፡ ፬ ፡ ፬ ። ሉቃ ፡ ፲ ፡ ፵፪ ። ም ፡ ፲፭ ፡ ፳፰ ። ፭ ፡ ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፲፫ ።

## <u>ሰው ፡ ምንድን ፡ ነው ?</u>

ሕያው፡ አምላካችን ፡ ፍጥረታትን ፡ ሲፈጥር፡
ይሁኑ ፡ እያለ ፡ ከፈጠረ ፡ በኋላ ፡ ሰውን ፡ በሚፈጥር ፡ መዝ፡ ፻፵፰፡፩-፭ ።
በት ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ "ሰውን ፡ በመልካችን ፡ እንደ ፡
ምሳሌያችን ፡ እንፍጠር፡ " ሲል ፡ ተናግሮ ፡ በጽድ ፡ ዘፍጥ ፡ ፩ ፡ ፳፮ ፡
ቅና ፡ በቅድስና ፡ መልኩ ፡ እንደምሳሌው ፡ ሰውን ፡
ፈጠረ ። በጽድቅና ፡ በቅድስና ፡ መልክም ፡ ዕውቀ ። ኤፌ ፡ ፬ ፡ ፳፬ ።
ትና ፡ ማስተዋል ፡ ያላቸው ፡ ረቂቃን ፡ መናፍስት ፡ ፡ መዝ ፡ ፻፬ ፡ ፬ ፡
ማለት ፡ የእግዚአብሔር ፡ መላእክት ፡ አስቀድመው ፡
ተፈጥረው ፡ ቢኖሩም ፤ ሰውን ፡ የእነርሱ ፡ ቅጅ ፡ (ረ ፤ ኢዮብ ፡ ፴፰ ፡ ፯ ፡
ቂቅ) ፡ ሆኖ ፡ ይወጣ ፡ ዘንድ ፡ ምንም ፡ ሳይሻ ፡ በቀ
ጥታው ፡ የገዛ ፡ ራሱን ፡ እንዲመስል ፡ እግዚአብሔር ፡ ፡ ሕዝቅ ፡ ፩ ፡ ፳፮ ።
ወድዶአል ። ። ፩ዮሐ ፡ ፫ ፡ ፩ ፡ ፪ ፡

እንደዚሁም ፡ ከእንስሳት ፡ በተለየ፡ አእምሮ ፡ ፡ ኢዮብ ፡ ፴፭ ፡ ፲፩ ።
በነፃነት ፡ ነውር ፡ የሌለው ፡ ሆኖ ፡ ተፈጥሮ ፡ ሲኖር ፡ ፡ ዘፍጥ ፡ ፪ ፡ ፳፭ ፡
ከሰይጣን ፡ ተንኰል ፡ የተነሣ ፡ ወደ ፡ ኃጢአት ፡ ቢወ
ድቅ ፡ እንኳ ፡ በጸጋው ፡ ኪዳን ፡ ዓለምን ፡ ሳይፈጥር ፡ ፡ ዘፍጥ ፡ ፫ ፡ ፩-፯ ፡
የመደበውን ፡ ተስፋ ፡ በሰው ፡ መውደቅ ፡ ጊዜ ፡ የመ ፡ ቈላስ፡ ፩፡ ፳፮፡ ፳፯ ።
ልሶ ፡ ማዳን ፡ ቃል ፡ ኪዳኑን ፡ ጉልህ ፡ አድርጎ ፡ በሰ
ጠበት ፡ መሠረት ፤ ለአለቅነትና ፡ ለሥልጣን ፡ ራስ ፡ ፤ ዘፍጥ ፡ ፫ ፡ ፲፭ ።
ሆኖ ፡ የመለኮትም ፡ ሙላት ፡ ሁሉ ፡ በሰውነቱ ፡ ተገ
ልጾ ፡ ቤዛ ፡ የሆነውን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ተቀብ ፡ ቈላስ ፡ ፪፡ ፱፡ ፲ ።
ለውና ፡ መንፈሱን ፡ ተመልተው ፡ ፍጹማን ፡ እንደ ፡ ፩ ፡ ጢሞ፡ ፩፡ ፲፭ ፡ ፡ ኤፌ፡ ፩፡ ፲፫፡ ፲፬ ፡
ሚሆኑ ፡ የሚያምኑ ፡ የሰው ፡ ልጆች ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ፡ ገላ ፡ ፬ ፡ ፯ ፡
በጸጋው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ ይሆናሉ ። ። ዮሐ፡ ፩፡ ፲፪፡ ፲፫ ።

ለእነዚህም፡ እግዚአብሔር፡ በክርስቶስ፡ ለማ
ድረግ ፡ እንደ ፡ ወደደ ፡ እንደ ፡ አሳቡ ፡ የፈቃዱን ፡
ምሥጢር ፡ አስታውቆ ፡ በመደበውና ፡ በወሰነው ፡

ገንዘብ ፡ "ወሜምኮ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ ግብረ ፡ እደ ፡ ኤፌ ፡ ፩ ፡ ፳፪ ።
ዊከ። በእጅህ፡ ሥራ፡ ሁሉ ፡ ላይ፡ ሾምኸው፡" ተብሎ፡ ፡ መዝ ፡ ፰ ፡ ፮ ።
ለሰው ፡ የተነገረለት ፡ አምላካዊ ፡ ቃል ፡ ፍጻሜ ፡
እስከ ፡ አገኘ ፡ ድረስ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ ስለ ፡ ፡ ቈላሳ፡ ፫ ፡ ፫ ፡ ፱ ።
ሰው ፡ ሁሉ ፡ ሞትን ፡ እንዲቀምስ ፡ ከመላእክት ፡
ጥቂት ፡ አንሶ ፡ የነበረው ፡ ኢየሱስ ፡ የክብርን ፡ የም
ስጋናን ፡ ዘውድ ፡ ተቀዳጅቶ ፡ መታየቱ፤ ዳግም፡ ሁሉ፡ ፤ ዕብ ፡ ፪ ፡ ፱ ፡
ከእግሩ ፡ በታች ፡ የሚገዛለት ፡ የደኅንነታቸው ፡
አለቃ ፡ የአባላቶቹ ፡ ራስ ፡ ሆኖ ፡ በኃይል ፡ ቀኝ ፡ መቀ ፡ ዕብ ፡ ፪ ፡ ፲ ፡
መጡ ፤ የተስፋቸው ፡ ዋና ፡ ግብ ፡ ነው ። ስለሆነ ፡ ከእ ። ኤፌ፡ ፩፡ ፳-፳፫ ።
ርሱ ፡ ጋር ፡ እንዳላቸው ፡ የመወሐድ ፡ ኅብረት ፡ ልክ፡ ፡ ዕብ፡ ፪፡ ፲፩-፲፰ ፡
እርሱን ፡ ለመምሰል ፡ የተጠሩበትን ፡ ለልጅነታቸው፡
የሚገባውን ፡ ውርስ ፡ ተቀብለው ፡ በሰማያዊ ፡ አባታ ፡ ሮሜ፡ ፰፡ ፳፱፡ ፴፡
ቸው ፡ መንግሥት ፡ ይነግሣሉ ። ። ፪ጢሞ፡፪፡፲፩፡፲፪።

ይህንም፡ በማመን፡ የዳኑበትና፡የተስፋቸውን፡
ክብር ፡ እንዲያረጋግጡበት ፡ የተሰጣቸው ፡ ወንጌለ ፡
ጸጋ ፡ መላእክት ፡ ሊያዩት ፡ የሚመኙ ፡ ከመሆኑ ፡ ፡ ሮሜ፡፲፮፡፳፭፡፳፮።
ጋር ፡ የሰው ፡ ልጆች ፡ የሚወርሱትን ፡ ክብር፡ ማለት ፡- ፡ ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፩፡ ፲፪፡
የሚመጣውን ፡ ዓለም ፡ ለመላእክት ፡ እንኳ ፡ እንደማ
ያስገዛ ፡ በቃሉ ፡ ሲያስረዳ ፡ በሥጋም ፡ የአምላክነቱን፡ ዕብ ፡ ፪ ፡ ፫ ፡ ፲፮ ።
ሙላት ፡ ሲገልጽ ፡ በመንፈስም ፡ ሲያጸድቀው ፡ በመ ዕብ፡ ፪፡ ፬፡ ቍ፡፲፮።
ገኘቱ ፡ ማኅተምነቱ ፡ ተረጋግጦአል ። ። ፩ ፡ ጢሞ፡ ፫፡ ፲፮።

ስለዚህም፡ ኍልቍ፡ መሣፍርት፡ከሌላቸውና ፡
ታላላቆች ፡ ከሆኑ ፡ ሠርዌ፡ ፍጥረታት ፡ ላይ፡ ይልቅ ፡
በሰው ፡ ላይ፡ ያረፈው፡ የእግዚአብሔር ፡ ፍቅር፡ ባለ ያዕ ፡ ፩ ፡ ፲፰ ።
ጸግነት ፡ መሠረቱ ፡ "በእንዲያው ፡ እንዲሁ ፡ መው ማቴ ፡ ፲፰፡ ፲፩-፲፬።
ደድ ፡ ብቻ!" እንጂ ፡ መቸም ፡ መች ፡ ሌላ ፡ መልስ ፡ ኤር ፡ ፴፩ ፡ ፫ ። ዮሐ ፡ ፫ ፡ ፲፮ ።
ወይም ፡ ምክንያት ፡ እንደማይኖርበት ፡ በማድነቅ ፡ ሮሜ ፡ ፭ ፡ ፰-፲ ። ፩ ፡ ዮሐ ፡ ፫ ፡ ፩ ።
ተረድተን ፡ ስለ ፡ ሰው ፡ መነሻና ፡ መድረሻ ፡ ያለው ፡ ፡ ሆሴ ፡ ፲፩ ፡ ፬ ።
ጥንታዊ ፡ ኀሳቡ ፡ ዘለዓለማዊ ፡ ምክሩ ፡ ሁሉ ፡ በልጁ፡ ፡ ኤፌ ፡ ፩ ፡ ፫-፲፬ ።
በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መደብ ፡ ማድረጉን ፡ ለይቶ ፡
እንዳስታወቀ ፡ በምስጋና ፡ ተቀብለን ፡ እናምናለን ። ። ኤፌ ፡ ፫ ፡ ፰-፲፫።





እፈ ፡ ወርቅ ፡ ስለ ፡ ሰዎች፡ የተናገረውን፡ ክብር፡ እንዲ ፡-

ጥቅስ ፡ «ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ናንክር ፡ ሶበ ፡ ንሰምዕ ፡ ከመ ፡ እግዚአብሔር ፡ አንበሮ ፡ ለባሕቲቱ ፡ ለዘውእቱ ፡ እምኔነ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ መላእክት ። ዝንቱ ፡ ዘረሰዮ ፡ እግዚአብሔር ፡ መልዕልተ ፡ ኵሉ ፡ ኃይላት ፡ ሰማያውያን ፡ ይቤ ፡ እምኵሉ ፡ ስም ፡ ዘይሰመይ ፡ አኮ ፡ በዝ ፡ ዓለም ፡ ባሕቲቱ ፡ አላ ፡ በዘይመጽእኒ ፡ ዓለም ፤ እስመ ፡ ቦ ፡ ስም ፡ ለኃይላት ፡ እለ ፡ ኢነአምሮሙ ፡ ወኢንጤይቆሙ ። ወይቤ ፡ ወኵሎ ፡ አግረረ ፡ ሎቱ ፡ ታሕተ ፡ መከየደ ፡ እገሪሁ ። ወኢረሰየ ፡ ከመ ፡ ያክብርዎ ፡ ባሕቲቱ ፡ ወዳዕሙ ፡ ረሰየ ፡ ኵሉ ፡ ይግነዩ ፡ ሎቱ ፡ ታሕተ ፡ እገሪሁ ፤ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ይቤ ፡ ወኵሎ ፡ አግረረ ፡ ሎቱ ፡ ታሕተ ፡ እገሪሁ ፤ ወኪያሁ ፡ ረሰዮ ፡ ርእሳ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ፈድፋደ ፡ እምነ ፡ ኵሎሙ ፡ ዘውእቱ ፡ ፍጻሜ ፡ ለኵሉ ፡ ፍጹም ።

ትርጓሜ፡ በሰማያውያን ፡ ኃይላት ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ያደረገው ፡ እግዚአብሔር ፡ በመላእክት ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ይህን ፡ የእኛውን ፡ ለብቻው ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳስቀመጠው ፡ በሰማን ፡ ጊዜ ፡ ስለዚህም ፡ እንደነቃለን ።

በዚህ ፡ ዓለም ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በሚመጣው ፡ ዓለምም ፡ ስም ፡ ካለው ፡ ሁሉ ፡ በላይ ፡ ማለቱም ፡ የማናውቃቸውና ፡ የማንረዳቸው ፡ የኃይላት ፡ (ፍጥረታት) ፡ ስም ፡ አለና ፡ ነው ። "ሁሉን ፡ ከእግሩ ፡ በታች፡ አስገዛለት ፡ ማለቱም ፡ "እንዲያከብሩት ፡ ብቻ ፡ አላደረገም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ከእግሩ ፡ በታች ፡ ሆነው ፡ እንዲገዙለት ፡ ጭምር፡ አድርጎአል ። ስለዚህም ፡ ፍጹም ፡ ለሚሆን ፡ ሁሉ ፡ ፍጻሜን ፡ የሚሆን ፡ ከሁሉም ፡ ይልቅ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ራስ ፡ ያደረገውን ፡ ሁሉን ፡ ከእግሩ፡ሜማ ፡ በታች ፡ አስገዛለት ፡" ብሎአል ።

እንኪያስ ፡ ለዚህ ፡ ሁሉ ፡ ክብር ፡ ባለመብት ፡ የሆነውን ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ እንስሳት ፡ አድርገው ፡ የሚቈጥሩት ፡ ወይም ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰውን ፡ መውደዱን ፡ የሚክዱት ፡ ሁሉ ፡ ተሳስተዋል ፡ እንላለን ።

## ስለ ፡ ኃጢአት ፡ ምክንያት ።

ክጥንት ፡ ከዘለዓለም ፡ ብቻውን ፡ ሆኖ ፡ ይኖር ፡
የነበረ ፡ ቅዱስ ፡ እግዚአብሔር ፡ የበጎ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ፤ መዝ ፡ ፺ ፡ ፪ ። ፤ መዝ፡ ፻፵፭፡ ፱፡ ፲፭-
ምንጭ ፡ እንደ ፡ መሆኑ ፡ ፍጥረታትን ፡ ሁሉ ፡ ሲፈ ፲፮ ።
ጥር ፡ ከበጎነቱና ፡ ከሕይወቱ ፡ ብርሃን ፡ ስለ ፡ ፈጠራ ፤ ኢሳ፡ ፵፡ ፳፮-፳፰ ።
ቸው ፡ በሥራው ፡ ሁሉ ፡ ይደሰት ፡ ነበር ። ግን ፡ ከመ ፤ ዘፍጥ ፡ ፩ ፡ ፴፩ ።
ላእክት ፡ አንዱ ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ፡ ያልነበረውን ፡
ክፉ ፡ ፈቃድ ፡ ከገዛ ፡ ራሱ ፡ ስላወጣ ፡ ይህ ፡ ለክፋት ፡ ሕዝ፡ ፳፰፡ ፲፫-፲፰ ፤ ዮሐ ፡ ፰ ፡ ፵፬ ።
የዘነበለው ፡ ፈቃዱ ፡ የኃጢአት ፡ ምንጭ ፡ ሆነ ። ፤ ራዕ፡ ፲፪፡ ፱ ።

የዚህም ፡ መገኛ ፡ (መነሻ ፡) ዓይነተኛ ፡ ምክን
ያት ፡ ሰይጣን ፡ ከሚገባው ፡ በላይ ፡ አልፎ ፡ ለእግዚ
አብሔር ፡ ባሕርዩ ፡ የሆነውን ፡ ክብር ፡ በመመኘቱ ፡
ነው ፡ እንጅ ፤ ሰይጣን ፡ መልአክ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ እንዳ ፤ ኢሳ፡ ፲፬፡ ፲፫-፲፬ ።
ይወድቅበት ፡ ተብሎ፡ ሊቀንስ፡ የማይቻለው ፡ የእግዚ
አብሔር ፡ ክብር ፡ ሙላት ፡ ለኃጢአት ፡ ምንጭ፡ በመ
ሆኑ ፡ ምክንያት ፡ አይደለም ። ፤ ሮሜ ፡ ፫ ፡ ፮ ፡ ፰ ።

በዚሁም ፡ መጠን፡ የአእምሮ፡ ፍጥረታት፡ ሁሉ ፡
በተሰጣቸው ፡ ነፃነት ፡ ፈቃዳቸውን ፡ ወደ ፡ ክፉ ፡ ፤ ሕዝ ፡ ፳፰ ፡ ፲፭ ።
ምኞት ፡ በማዘንበል ፡ ኃጢአትን ፡ ከገንዘባቸው ፡
ያወጣሉ ፡ እንጅ ፡ እግዚአብሔር ፡ የኃጢአት ፡ ፈ ፤ ኢሳ ፡ ፶፱ ፡ ፪ ።
ጣሪ ፡ እንዳልሆነና ፤ ፤ ኢዮብ፡ ፴፬፡ ፲፡ ፲፪

ሰይጣን ፡ ወደ ፡ ክፉ ፡ ባዘነበለው ፡ ፈቃዱ ፡
ከፈለሰፈው ፡ በቀር ፡ ኃጢአት ፡ በዘለዓለማዊነት ፡ ፤ ፩ዮሐ ፡ ፫ ፡ ፰ ።
ነዋሪ ፡ እንዳል ሆነ ፡ እናምናለን ።

ጥቅስ ፡ ብንያሚን ፡ የተባለው ፡ ሊቅ ፡ "ኢይምሰልከ ፡ ከመ ፡
እግዚአብሔር ፡ ያመጽእ ፡ ለእኪት ፡ ሐሰ ፡ ወባሕቱ ፡ እኪትሰ ፡ እም
ኀበ ፡ ሰይጣን ፡ ውእቱ ፤ ወዘይብል ፡ እኪትሰ ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡

ውእቱ ፡ ውእቱኬ ፡ ይከውን ፡ ነኪረ ፡ እምአብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወይወርድ ፡ ውስተ ፡ ሲኦል ፡ ወማኅደሩ ፡ እሳተ ፡ ገሃነም ። ------ለእመ ፡ ሠምረ ፡ ገቢሮቶ ፡ ለእከይ ፡ ለሊሁ ፡ ይከውን ፡ ገባሬ ፡ እኪት ፡ ወለእመ ፡ ሠምረ ፡ ይግበር ፡ ሰብእ ፡ አበሳ ፡ ወኃጢአተ ፡ ናሁ ፡ ይከውን ፡ ገባሪሃ ፡ ለአበሳ ፡ ወለኃጢአት ፤ ወለእመ ፡ ትብል ፡ ጸኮኑ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈጠሮ ፡ ለሰይጣን ፤ እብለከ ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቀዳሚሁ ፡ ኢፈጠሮ ፡ እንዘ ፡ ሰይጣን ፡ ዘእንበለ ፡ እንዘ ፡ መልአክ ፡ ወለሊሁ ፡ እምርእሱ ፡ ነበበ ፡ ሐሰተ ።

ትርጓሜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ክፋትን ፡ እንዳመጣ ፡ አታስብ ። አይደለም ፡ ክፋትስ ፡ ከሰይጣን ፡ ነው ። ክፋት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ነው፡ የሚለው ፡ ሰው ፡ ከአብና ፡ ከወልድ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ የተለየ፡ ነው ። ወደ ፡ ሲኦልም ፡ ይወርዳል ፡ መኖሪያውም ፡ ገሃነም ፡ ነው ።

የክፋትን ፡ ሥራ ፡ ከወደደ ፤ ራሱ ፡ ክፋትን ፡ የሚያደርግ ፡ ሆነ ፡ ማለት ፡ ነው ። ሰውንም ፡ ኃጢአትንና ፡ በደልን ፡ እንዲሠራ ፡ ከወደደ ለት ፤ ራሱ ፡ የኃጢአትና ፡ የበደል ፡ ሠሪ ፡ ሆነ ፡ ማለት ፡ ነው ። እንዲሁም ፡ ሰይጣንን ፡ የፈጠረ ፡ እግዚአብሔር ፡ አይደለምን ? ብትለኝ ፤ ከመጀመሪያው፡ እግዚአብሔር፡ ሰይጣንን፡ ሰይጣን ፡እንደሆን፡ አልፈጠረውም ፡ መልአክ ፡ አድርጎ፡ እንጂ ፤ ብቻ፡ ከራሱ፡ ውሸትን፡ ተናገረ ፤" እያለ ፡ አስረድቶአል ።

በዚሁም ፡ መሠረት ፡ የምናምን ፡- ኃጢአትን ፡ የፈጠረ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፡ የሚሉትን ፡ ወይም ፡ ኃጢአት ፡ ከጥንት ፡ ከዘለዓለም ፡ ነበረ ፡ የሚሉትን ፡ ትምህርት ፡ አንቀበልም ።



፯ኛ ፡ አንቀጽ ።

## ስለ ፡ ኃጢአት ፡ ዘር ።

ክፉ ፡ ሥራ ፡ በትምህርት ፡ ወይም ፡ ሰው ፡
የሚያደርገው ፡ ታይቶ ፡ በመለመድ ፡ የሚመጣ ፡ እን ምሳ ፡ ፳ ፡ ፲፰ ።
ዳልሆነ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አባታችን ፡ አዳም ፡ ኃጢአትን ፡ ፤ ዘፍ ፡ ፰ ፡ ፳፩ ፡
ከሰይጣን ፡ በመቀበሉ ፡ ምክንያት ፡ በውስጡ ፡ ሆኖ ፡ ዘፍጥ ፡ ፫ ፡ ፩-፭ ፡ ሮሜ ፡ ፭ ፡ ፲፱ ፡
የእግዚአብሔርን፡ ትእዛዝ፡ እንዲተላለፍ፡ ያደረገውና፡ ፤ ያዕ ፡ ፩ ፡ ፲፭ ፡
አዳምና ፡ሔዋን ፡ ዛፉን ፡ ስንኳ ፡ ከመቁረጣቸው ፡
አስቀድሞ ፡ በልባቸው ፡ ውስጥ ፡ በማደሩ ፡ የዚያን ፡ ፤ ዘፍ ፡ ፫ ፡ ፮ ።
ጊዜ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ እንደተላለፉ ፤ ፤ ፩ ፡ ዮሐ ፡ ፪ ፡ ፲፮ ።
ያ ፡ የኃጢአት ፡ ፍትወት ፡ በልባቸው ፡ ካረፈ፡ ዘንድ ፡
ሲገፋፋቸው ፡ ያን ፡ ዛፍ ፡ ከመብላት ፡ እንዳልተመ ሮሜ ፡ ፯ ፡ ፲፭-፲፯ ። ዘፍ ፡ ፫ ፡ ፯ ።
ለሱ ፤ እንዲሁም ፡ በአዳምና ፡ በሔዋን ፡ ላይ ፡ ለአ ፤ ዘፍ ፡ ፮ ፡ ፭ ።
ንድ ፡ ጊዜ ፡ ማለት ፡ ዛፍን ፡ ለማስበላት ፡ ብቻ ፡
አድሮ ፡ ያሠራቸው ፡ ሳይሆን ፡ በውስጣቸው ፡ በሥ ሆሴ ፡ ፮ ፡ ፯ ።
ጋና ፡ በደም ፡ ተዋሕዶ ፡ በሕይወታቸው ፡ ዘመን ፡ ፤ ፩፡ ቆሮ፡ ፲፭፡ ፵፱።
ሁሉ ፡ እየተገለጸ ፡ ዳግም ፡ በዘር ፡ መጠን ፡ ወደ ፡ ልጆ ፤ ዘፍ፡፫፡፳፡ ፲፫፡፳፪።
ቻቸው ፡ እንደ ፡ ተላለፈ ፤ ፤ ዘፍ ፡ ፭ ፡ ፫ ።

ስለዚህም ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በአዳም ፡ ምሳሌ ፡
ስለ ፡ ተወለደ ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ አእምሮ ፡ ምንም ፡ ፤ ኢዮብ፡ ፲፭፡፯፡፲፬፡
አልሠራም ፡ ተብሎ ፡ የሚገመት ፡ ሕፃን ፡ እንኳ ፡ ፤ ማቴ ፡ ፲፪ ፡ ፴፬ ።
በኃጢአት ፡ ተረግዞ ፡ እንደሚወለድ ፤ የዚህም ፡ መግ መዝ ፡ ፶፩ ፡ ፭ ። ፤ ሮሜ ፡ ፭ ፡ ፲፪ ።
ለጫ ፡ ሞት ፡ እንደሆነ ፤ ፤ ኢሳ ፡ ፵፰ ፡ ፰ ።

ሊቁ ፡ አቡሊዲስም፡—

ጥቅስ ፡ "እስመ፡ ኃጢአት ፡ የኃድር ፡ ውስተ፡ ሰብእ ፡ ወሞት ፡ ይትልዎ ። ወሶበ ፡ አበሰ፡ አዳም፡ ወለደ ፡ ዘከመ፡ አምሳሊሁ ፤ ወእምውእቱ፡ መዋዕል፡ በጽሐ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ አሐዱ ፡ ትእዛዝ ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘይብል ፡ መሬት ፡ አንተ ፡ ወትገብእ ፡ ውስተ ፡ መሬት ።

ትርጓሜ፣ ኃጢአት፣ በሰውነት፣ ውስጥ ፣ አድሮአልና ፣ ሞትም ፣ ይከተለዋል ። አዳም ፣ በበደለ ፣ ጊዜ ፣ በመልኩ ፣ ምሳሌ ፣ ወለደ ። ከዚያን ፣ ጊዜ ፣ አንሥቶ ፣ ከእግዚአብሔር ፣ ዘንድ ፣ አፈር ፣ ነህና ፣ ወደ ፣ አፈር ፣ ትመለሳለህ ፣ የሚል ፣ ትእዛዝ ፣ ወደ ፣ እያንዳንዱ ፣ ሰው ፣ ዘንድ፣ መጣ ፣ ደረሰ ፤" ብሎአል ። ኤር ፣ ፫ ፣ ፳፱ ፣ ፳፫ ።

የምንወደውን ፣ መልካሙን ፣ ነገር ፣ እንዳና
ድርግ ፣ ከልክሎ ፣ የምንጠላውንና ፣ እግዚአብሔርን ፣
ደስ ፣ የማያሰኘውን ፣ እንድናደርግ ፣ የሚያስገድደን ፣
ይህ ፣ መጥፎ ፣ የተወረሰው ፣ ኃጢአት ፣ ነውና ፣ በኢ ፣ ሮሜ ፣ ፯ ፣ ፲፱-፳፬ ።
የሱስ ፣ ክርስቶስ ፣ ለሌሉ ፣ ሁሉ ፣ በዘለዓለማዊ ፣ ገሃ
ነም ፣ ያስኰንናቸዋል ። ይሁን፣ እንጅ፣ እግዚአብሔር፣ ። ሮሜ ፣ ፰ ፣ ፲፰ ።
በሕይወት ፣ መንፈስ ፣ ሕግ ፣ የሚመላለሱት ፣ ሁሉ ፣
ድል ፣ እንዲነሡት ፣ ሲል ፤ እርሱ ፣ ያለበትን ፣ አሮጌ ፣ ቈላሳ፣ ፪ ፣ ፲፩፣ ፲፬ ።
ሰውነት ፣ በክርስቶስ ፣ አካል ፣ በመስቀል ፣ ላይ ፣ ቀጣ ሮሜ ፣ ፰ ፣ ፪ ፣ ፫ ፣ ፩ ፣ ጴጥ ፣ ፪ ፣ ፳፬ ።
ውና ፣ ኰነነው ። ። ሮሜ ፣ ፮ ፣ ፮ ።

ስለዚህ ፣ አዲስ ፣ የተወለዱ ፣ ስንኳ ፣ ቢሆኑ ፣
በመንፈስ ፣ ካልተመላለሱ ፣ ለዚህ ፣ ኃጢአት ፣ በመ ፣ ገላ፣ ፭ ፣ ፲፯፣ ፲፮ ።
ታዘዝ ፣ እንደገና ፣ መጨነቃቸውንና ፣ መቸገራቸውን፣
ያውቃሉና ፣ ኃጢአቱ ፣ በክርስቶስ ፣ በተቀጣላቸውና፣ ፣ ሮሜ ፣ ፯ ፣ ፭ ።
በተኰነነላቸው ፣ ጊዜ ፣ ሥጋ ፣ ስለ ፣ ኃጢአት ፣ ምክ ፣ ፪፣ ቆሮ፣ ፭፣ ፳፩ ።
ንያት ፣ እንደ ፣ ሞተ ፣ አምነው ፣ ዘወትር ፣ በየጊዜው ፣ ፣ሮሜ ፣ ፰፣ ፲ ፣ ፲፩ ።
ከክፉ ፣ ምኞቱና ፣ መሻቱ ፣ ጋር ፣ ራስን ፣ በመግደል ፣ ፣ ሉቃ ፣ ፱ ፣ ፳፫ ።
ልባቸውን ፣ በዚያ ፣ መስቀል ፣ ላይ ፣ ያኖራሉ ። እን ። ገላ ፣ ፭ ፣ ፳፬ ።
ዲሁም ፣ በመንፈስ ፣ እየተመላለሱ ፣ ሲጋደሉ ፣ ቆይ
ተው ፣ በኋለኛው ፣ ትንሣኤ ፣ በሚደረገው ፣ መለወጥ ፣ ፣ ፩፣ ጴጥ፣ ፬፣ ፩-፪ ።
ጭራሹን ፣ ጠፍቶ ፣ የዚያን ፣ ጊዜ ፣ ብቻ ፣ የሥጋ ፣ ፩ቆሮ ፣ ፲፭፣ ፶፩-፶፬ ፣ ፩ ፣ ጴጥ ፣ ፩ ፣ ፱ ።
ፍጹም ፣ መዳን ፣ እንደሚሆን ፤ እናምናለን ። ። ሮሜ ፣ ፰ ፣ ፳፫ ።

ዮሐንስ ፣ ኤጲስ ፣ ቆጶስ ፣ ዘኢየሩሳሌም ፣—

ጥቅስ፣ "ኢይትከሃል ፣ የሀሉ ፣ ሰብእ ፣ እንበለ ፣ ኃጢአት ፣ ወፈድፋደሰ ፣ እንተ ፣ ትከውን ፣ እምሕሊናት ፤ እስመ ፣ ሕሊናሁ ፣ ልሳ





ብእ ፣ ይትወላወል ፣ እምጊዜ ፣ ልደቱ ፣ እስከ ፣ ዕለተ ፣ ሞቱ ። መክ ፣ ፺ ፣ ፳ ፤

ትርጓሜ፣ ሰው ፣ ያለ ፣ ኃጢአት ፣ ይኖር ፣ ዘንድ ፣ አይቻለውም፣ ይልቁንም ፣ በኀሳብ ፣ ከሚሆን ፣ ኃጢአት ፤ የሰው ፣ ኀሳብ ፣ ከዕለተ ፣ ልደቱ ፣ ጀምሮ ፣ እስከ ፣ ዕለተ ፣ ሞቱ ፣ ድረስ ፣ ሲያወላውል ፣ ይኖራል፤" ሲል ፣ የተናገረው ፣ ስለዚህ ፣ ነው ።

እንግዲያውስ ፣ የዚህ ፣ ዓይነት ፣ ኃጢአት ፣ ከመማር ፣ ይመጣል ፣ የሚሉት ፣ በመንፈስ ፣ ቅዱስ ፣ ኃይል ፣ ሳይሆን ፣ በሥጋዊ ፣ ጉልበት ፣ ይህን ፣ ኃጢአት ፣ ለማጥፋት ፣ የሚጥሩት ፣ ወይንም ፣ ደግሞ ፣ እንደግኖስቲኮች ፣ በሰውነታችን ፣ ግዘፍ ፣ ምክንያት ፣ የተገኘ ፣ ነገር ፣ ነውና ፣ ሰውነታችንን ፣ ብናጐሳቍል ፣ ይጠፋልናል ፣ የሚሉት ፣ እንዲሁም ፣ ኃጢአትን ፣ በመውረስ ፣ ሳይሆን ፣ ሰይጣን ፣ በየቀኑ ፣ ስለሚያስተን ፣ ነው ፣ የሚሉት ፣ ደግሞ ፣ ሰይጣን ፣ አዳምን ፣ ባሳተ ፣ ጊዜ ፣ ለተወለዱት ፣ ልጆቹ ፣ ሁሉ ፣ አንዳንድ ፣ ሰይጣን ፣ ዳረጋቸው ፣ እንጅ ፣ አዳም ፣ ከሰይጣን ፣ ተቀብሎ ፣ ከአባታቸው ፣ በዘር ፣ መጠን ፣ የወረሱት ፣ ነገር ፣ የለም ፣ ብለው ፣ የሚክዱት ፤ እንዲሁም ፣ ሞት ፣ የተፈጥሮ ፣ ነውና ፣ ሞት ፣ የሚመጣብን ፣ ኃጢአትን ፣ በመውረሳችን ፣ አይደለም ፣ የሚሉት ፣ ሁሉ ፤ ከቅዱሳት ፣ መጻሕፍት ፣ ኀሳብ ፣ መውጣታቸውን ፣ እንገልጻለን ።

፯ኛ ፡ አንቀጽ ።

## ስለ ፡ ፈቃድ ፡ ነፃነት ።

አሞኔዎስ ፡ አውሳብዮስ ፡ ስለ ፡ ሰው ፡ ሕይወት ፡ ሲናገሩ ፡–

ጥቅስ ፡ "ወገብረ ፡ ላቲ ፡ ሥልጣነ ፡ በውስቴታ ፡ ትግበር ፡ በከመ ፡ ኃርየት ፡ እንዘ ፡ አልቦ ፡ ዘይኬንና ፡ ወዘይጌይላ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ሠናያቲሃ ፡ ወእከያቲሃ ፡ በሥምረተ ፡ ሕሊናሃ ፡ በአምሳለ ፡ መላእክት ።

ትርጓሜ ፡ እንደ ፡ መላእክት ፡ በሕሊናዋ ፡ ፈቃድ ፡ በጎነትዋና ፡ ክፋትዋ ፡ ከራስዋ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ማንም ፡ የሚገዛት ፡ ሳይኖር ፡ የወደደችውን ፡ እንድታደርግ ፡ ሥልጣንን ፡ በውስጥዋ ፡ አድርጎላት ፡ ነበር ፤ "እንዳሉት ፡ ሁሉ ፤

እውነት ፡ ነው ፡ ሰው ፡ በጥንተ ፡ ተፈጥሮው ፡ ዘፍ ፡ ፩ ፡ ፳፮ ፡ ፳፯ ፡
በእግዚአብሔር ፡ ምሳሌ ፡ ስለ ፡ ተፈጠረ ፤ እንደ ፡ ኤፌ ፡ ፬ ፡ ፳፬ ።
እግዚአብሔር ፡ ሥርዓት ፡ ለመኖር ፡ ነፃነት ፡ ነበ
ረው ። ግን ፡ ወዲያውኑ ፡ የሰው ፡ ሁሉ ፡ አባት ፡ የሆነ ፡ ። ኢሳ ፡ ፵፫ ፡ ፳፯ ።
አዳም ፡ በአሳቹ ፡ በሰይጣን ፡ ምክንያት ፡ በጎ ፡ የነበረ ዘፍ ፡ ፫ ፡ ፮ ።
ውን ፡ ፈቃዱን ፡ ለክፉ ፡ ምኞት ፡ ባዘነበለ ፡ ጊዜ ፡ ፡ ሆሴ ፡ ፮ ፡ ፯ ።
ነፃነቱን ፡ ለባርነት ፡ በመለወጡ ፡ ከዚህ ፡ የክፉ ፡ ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፩ ፡ ፲፱ ።
ምኞት ፡ ዝንባሌ ፡ በኋላ ፡ ኃጢአት ፡ በአዳምና ፡ በተ ዮሐ ፡ ፰ ፡ ፴፬ ፡ ፴፮ ።
ወለዱት ፡ ልጆቹ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ ገዛቸውና ፡ ከሥልጣኑ ፡ ሮሜ ፡ ፮ ፡ ፲፯ ።
በታች ፡ በመሆናቸው ፡ መንፈሳዊ ፡ ነፃነት ፡ ፈጽሞ ፡ ፡ ገላ ፡ ፭ ፡ ፲፯ ።
የሌላቸው ፡ ሆነ ። ። ቲቶ ፡ ፫ ፡ ፫ ።

ብቻ ፡ ኃጢአተኛ ፡ ጠባይ ፡ በሚፈቅደው ፡
መጠን ፡ በምድራዊ ፡ ክበብ ፡ (በሥጋና ፡ በደም ፡ ፪ ፡ ጢሞ ፡ ፪ ፡ ፳፭ ፡ ፳፮ ፡
አጥር ፡ ) ሊሄዱና ፡ ሊቀመጡ ፡ ሊነግዱና ፡ ሊያርሱ ፡ ኢሳ ፡ ፭ ፡ ፲፰ ።
ይህን ፡ የመሳሰለውንም ፡ ሊያደርጉ ፡ ነፃነት ፡ አላ
ቸው ። ። ኢሳ ፡ ፶፱ ፡ ፲፫ ፡ ፲፬ ።

ከዚህም ፡ ሌላ ፡ በውስጡ ፡ ግብዝነትና ፡ ኃጢ ዮሐ ፡ ፫ ፡ ፲ ።
አት ፡ ሳለ ፤ መንፈሳዊ ፡ ነገር ፡ መስሎ ፡ ለሰው ፡ የሚ ሉቃ ፡ ፲፩ ፡ ፴፱-፵፰
ታይ ፡ እንደ ፡ ተለሰነ ፡ መቃብር ፡ ላይ ፡ ላዩ ፡ የተጌ ማቴ ፡ ፳፫ ፡ ፳፯ ።
ጠን ፡ ከ.ን ፡ ምግባር ፡ ሊሠሩ ፡ ይችላሉ ። ። ሉቃ ፡ ፲፮ ፡ ፲፭ ።

እንደዚሁም ፡ በእርሱ ፡ ጥበቃ ፡ ውስጥ ፡ መሆ
ናቸውን ፡ እስኪረሱ ፡ ድረስ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ዮሐ ፡ ፰ ፡ ፴፱-፵፮ ፡
ሥራ ፡ የሚሠሩ ፡ የሚመስሉበትን ፡ ተመሳሳይ ፡ አም
ልኮን ፡ ለማምለክ ፡ እግዚአብሔር ፡ በክርስቶስ ፡ ታር ፡ ሕዝ ፡ ፰ ፡ ፮-፲፮ ።
ቆኛል ፡ ለማለት ፡ በማያስደፍር ፡ በራስ ፡ ጽድቅ ፡ ፩ ጢሞ ፡ ፩፡፮-፲ ።
ለመመካት ፡ ሰይጣናት ፡ የሚያምኑበትንም ፡ ሃይማ ፡ ሮሜ ፡ ፲ ፡ ፱ ።
ኖት ፡ ለማመን ፡ ይችሉ ፡ ዘንድ ፤ መቼም ፡ አይድኑበ ፤ ማር፡ ፩፡ ፳፱፡ ፳፬።
ትምና ! መብት ፡ ሰጥቶ ፡ ስድ ፡ ለቅቆአቸዋል ። ። ኤር ፡ ፮ ፡ ፳፪ ።

ነገር ፡ ግን ፡ ይቅርታ ፡ የሚገኝበትን ፡ የክርስ
ቶስን ፡ ጽድቅ ፡ ለመልበስ ፡ የክርስቶስ ፡ ምግባሩንና ፡ ፡ ኤር ፡ ፳፱ ፡ ፯ ።
ትሩፋቱን ፡ ለመገንዘብ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ ፡ ፊል ፡ ፱ ፡ ፰ ፡ ፱ ።
ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ የሚያስችላቸውን ፡ ሕያዉን ፡ ሃይማ
ኖት ፡ ለመቀበል ፡ ስጦታው ፡ እንኳ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፡ ዮሐ፡ ፩፡ ፲፪፡ ፲፱ ።
ጸጋ ፡ እንጅ ፡ ከማናቸው ፡ የማይመጣ ፡ መሆኑ ፡ ቢታ ፡ ዘካ ፡ ፲፪ ፡ ፲ ።
ወቅም ፤ እነርሱ ፡ ራሳቸው ፡ ለአንድ ፡ ጊዜ ፡ እንኳ ፡ ፲፱፡ቆሮ፡፩፡፳፩፡፳፪።
ፈቃደኞች ፡ ለመሆን ፡ የሚበቁበትን ፡ የማሰብ ፡ መብ
ት ፡ የማይሰጣቸው ፡ መሆኑን ፡ እናምናለን ። ። ፪ቆሮ ፡ ፮ ፡ ፯ ።

ይህን ፡ በመረዳት ፡ በድራን ፡ ወልደ ፡ ሲማ
ዖን ፡ የተባለው ፡ የአርማንያ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ እንደ
ሚከተለው ፡ ተናገረ ።

ጥቅስ ፡ "እስመ ፡ ለሊሁ ፡ (ሰይጣን፡ )እምቀዳሚ ፡ ዘሠረቀ ፡ ምሥጢረ ፡ እግዚአብሔር ፡ እምአዳም ፡ ወሔዋ ፡ ወሄጦሙ ፡ በሐሰቱ ፡ ከመ ፡ ዘይገብር ፡ ሎሙ ፡ ሠናይተ ፡ ወይመርሆሙ ፡ ፍኖተ ፤ ወፈለጠ ፡ ማዕከሌሆሙ ፡ ወማዕከለ ፡ እግዚአብሔር ፤ ወአውደቆሙ ፡ እምስብሐቲሆሙ ፡ ወክብሮሙ ፤ ወአግኅሦሙ ፡ እምዓለመ ፡ ብርሃን ፡ ኀበ ፡ ዓለመ ፡ ጽልመት ፤ ወይገብር ፡ ቦሙ ፡ ኵሎ ፡ እኪተ ፡ በጥበበ ፡ ጠባይዓ ፡ ሥጋ ፡ ዕበድ ፡ ወሕጋቲሃ ፡ ወግዕዛ ፡ እንተ ፡ ባቲ ፡ አስሐተ ፡ ኵሎ ፡ ዓለመ ፤ ወአኅጐሎሙ ፡ በምግባረ ፡ ከንቱ ፡ ዘኀዱር ፡ በባሕርየ ፡ ሥጋ ፡ ወደም ፡ መስተቃርኒ ፡ ለሕገ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወትእዛዛቲሁ ፡ ዘርኩብ ፡ በኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ በመንፈሱ ፡ ቅዱስ ።





ትርጓሜ ፡ በጎ ፡ ነገር ፡ የሚያደርግላቸውና ፡ በቀና ፡ መንገድ፡ የሚመራቸው ፡ ይመስል ፡ ከአዳምና ፡ ከሔዋን ፡ ከመጀመሪያው ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ምሥጢር ፡ የሠረቀና ፡ በውሸቱም ፡ የሸነገላቸው ፡ እርሱ፡ ሰይጣን ፡ ነው ። በእነርሱና ፡ በእግዚአብሔር ፡ መካከልም ፡ መለየትን ፡ አመጣ ፤ ከግርማቸውና ፡ ከክብራቸው ፡ ጣላቸው ፤ ከብርሃን ፡ ዓለምም ፡ ወደ ፡ ጨለማ ፡ ዓለም ፡ አስወገዳቸው ፤ ዓለምን ፡ ባሳተባት ፡ በደካማ ፡ ሥጋ ፡ ጠባይ ፡ ብልሃት ፡ በሕጎችዋና ፡ በልማድዋ ፡ ክፋትን ፡ ሁሉ ፡ ይሠራባቸዋል ። ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ በቅዱስ ፡ መንፈሱ ፡ የተገኘውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሕግና ፡ ትእዛዛቶቹን ፡ ተቃራኒ ፡ በመሆን ፡ በሥጋና ፡ በደም ፡ ጠባይ ፡ ባደረገው ፡ በከንቱ ፡ ሥራ ፡ አጠፋቸው ።"

ጥቅስ ፡ ሌላውም ፡ ሊቅ ፡- "ንሕነሰ ፡ ሥጋውያን ፡ ንሔሊ ፡ ሕገ ፡ ሥጋ ፡ ወንገብር ፡ ግብረ ፡ ሥጋ ፡ ወንሐውር ፡ በፍኖተ ፡ ሥጋ ፤ አንተ ፡ ባሕቱ ፡ መሀረነ ፡ ምግባረ ፡ መንፈስ ፡ ወአለብወነ ፡ ሕገ ፡ መንፈስ ፡ ወምርሃነ ፡ አንተ ፡ ፍኖተ ፡ መንፈስ ።

ትርጓሜ ፡ እኛ ፡ ሥጋውያን ፡ ስለሆንን ፡ የሥጋን፡ ሕግ ፡ እናስባለን ፤ የምንሠራውም ፡ የሥጋን ፡ ሥራ ፡ ነው፤ የምንሄደውም፡ በሥጋ፡ መንገድ ፡ ነው ። አቤቱ ፡ ሆይ ፡ አንተው ፡ ራስህ ፡ የመንፈስን ፡ ሥራ ፡ አስተምረን ፤ የመንፈስን ፡ ሕግም ፡ አሳስበን ፤ የመንፈስ ፡ መንገድንም፡ ምራን ።" እያለ ፡ የልብ ፡ ጩኸቱን ፡ አቅርቦአል ።
በመ.ቅዳ.ተመልከት ።

፭ኛ ፡ አንቀጽ ።

## ሕግና ፡ ሰው ።

ሕግ ፡ መንፈሳዊ ፡ ባሕርይ ፡ ያላት ፡ ከሰዎ ፡ሮሜ፡ ፯፡ ፲፪፡ ፲፬፡
ችም፡ ሚዳዊ ፡ አድራጎትን፡ ብቻ፡ ሳትመለከት ፡ ፍጹ ፡ማቴ፡ ፭፡ ፲፯-፵፰፡
ምነትን፡ የምትፈላለግ፡የእግዚአብሔር፡ፈቃድ፡ ናት ፤ ፤ሮሜ ፡ ፪፡ ፲፯ ፡ ፲፰፡
ስለዚህም ፡ የሚጠብቃት ፡ ሰው ፡ ቢገኝ ፡ ኖሮ፡ ጽድ ፡ ፩፡ ጢሞ፡ ፩ ፡ ፰ ።
ቅን ፡ አረጋግጣለት ፡ ሕይወትንም ፡ ልትሰጠው ፡
ትችል ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በውስጡ ፡ ። ሕዝ ፡ ፳ ፡ ፲፩ ።
ባለው ፡ በኃጢአተኛ ፡ ሥጋ ፡ አገዛዝ ፡ ምክንያት ፡
ነፃነትን ፡ አግኝቶ ፡ ሊጠብቃት ፡ ባለመቻሉ ፡ ከመ ፡ሮሜ፡ ፯፡ ፳፪፡፳፫።
ርገምዋ ፡ በታች ፡ ስለሆነ ፡ ሥጋ ፡ የለበሰ ፡ ሁሉ ፡ ፡ ገላ ፡ ፫ ፡ ፲ ፡ ፲፩ ።
ሕግን ፡ በማድረግ ፡ ሊጸድቅ ፡ አይችልም ፡ ተባለ ። ። ሮሜ ፡ ፫፡ ፲፱፡ ፳።
ምንም ፡ እንኳ ፡ ሞት ፡ የኃጢአት ፡ መግለጫ ፡ ቢሆን፡ ፡ሮሜ ፡ ፭ ፡ ፲፪ ፡ ፲፫፡
የኦሪት ፡ ሕግ ፡ ባልነበረችበት ፡ ጊዜ፡ ኃጢአት፡ ራሱ ፡
ኃጢአት ፡ መሆኑን ፡ ባለመታወቁ ፡ ኃጢአትን ፡ በመ
ግለጽና ፡ መቅሰፍትን ፡ በማምጣት ፡ እስከ ፡ ክርስ ፡ሮሜ ፡ ፯፡ ፲፩ ።
ቶስ ፡ ድረስ ፡ የመሪነትን ፡ ሥልጣን ፡ ተግባር ፡ ይዛ ፡
የቆየች ፡ ነበረች ። ። ገላ፡ ፫፡ ፲፱-፳፭ ።

ሆኖም ፡ በሕግ ፡ የምናየው ፡ ሁሉ ፡ ሰው ፡ ፡ዕብ ፡ ፯ ፡ ፲፱ ።
ይጠብቃት ፡ ዘንድ ፡ መርዳቱን ፡ አትችልም ፡ እንጅ ፡ ፡ የሐዋ ፡ ፲፫፡ ፴፱ ፡
ኃጢአቱን ፡ እያባባሰች ፡ በቁጣዋና ፡ በመርገምዋ ፡
ከመጉዳትዋ ፡ በስተቀር ፡ ደካማው ፡ ሰው ፡ እርስዋን ፡ ፡ ሮሜ ፡ ፯ ፡ ፲፩ ።
በማወቁ ፡ የዳነበት ፡ ጊዜ ፡ አለመኖሩን ፡ ነው ። ግን ፡ ዮሐ ፡ ፯ ፡ ፲፱ ።
ትፈጸም ፡ ዘንድ ፡ ያላት ፡ ልከኛና ፡ መደበኛ ፡ ሰው ፡ ሮሜ ፡ ፫ ፡ ፲፫ ።
የሚፈቅዳት ፡ የማትሻር ፡ የእግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ ማቴ ፡ ፭ ፡ ፲፯-፲፱ ። ።ሮሜ ፡ ፯ ፡ ፳፪ ።
ናት ።

ስለዚህም ፡ ክርስቶስ ፡ ከእርስዋ ፡ በታች ፡ ገላ ፡ ፬ ፡ ፬ ፡ ፭ ።
ሆኖ ፡ ፈጽሞአት ፡ ከኦሪት ፡ በታች ፡ የነበሩትን ፡ሁሉ፡
ስለዋጃቸው ፡ የሚያምኑበት፡ ይጸድቁ ፡ ዘንድ፡ እርሱ፡ ፡ገላ ፡ ፫ ፡ ፲፫ ፡ ፲፬ ።

ራሱ ፡ የኦሪት ፡ ፍጻሜ ፡ ሆኖአልና ፡ ከማያምኑበት ፡ ፡ ሮሜ ፡ ፲ ፡ ፬ ።
በቀር ፡ በሃይማኖቱ ፡ የጸደቁት ፡ ሁሉ ፡ ከዚህ ፡ ጊዜ ፡ ፡ ሮሜ ፡ ፫ ፡ ፳፩ ፡ ፳፫ ፡
ወዲህ ፡ በጸጋ ፡ ውስጥ ፡ እንጅ ፡ ከኦሪት ፡ በታች ፡ ሮሜ ፡ ፯ ፡ ፲፬ ።
አይደሉም ። ፡ ኤፌ ፡ ፪ ፡ ፲፭ ።

በዚህም ፡ በሃይማኖት ፡ በሆነው ፡ በጽድቅ ፡ ቲቶ ፡ ፫ ፡ ፯ ፡ ፰ ፡
መሠረት ፡ ላይ ፡ ምዕመናኑ ፡ ቅድስናን ፡ በሙሉ ፡ ፡ ኤፌ ፡ ፪ ፡ ፲ ።
ለመፈጸም ፡ የሚችሉበት ፡ ዘዴ ፡ ራሳቸውን ፡ በክር ፡ ሉቃ ፡ ፩ ፡ ፸፭ ።
ስቶስ ፡ ሥጋ ፡ ለሕግ ፡ እንደ ፡ ሞቱ ፡ ካልቈጠሩ ፡ ፡ ሮሜ ፡ ፯ ፡ ፬ ፡ ፮ ።
ለእግዚአብሔር ፡ የሚሆነውን ፡ ፍሬ ፡ ማስገኘታቸው ፡
ቀርቶ ፡ ስለ ፡ ሞት ፡ ፍሬ ፡ በሕግ ፡ የሚሆነው ፡ የኃ ፡ ቲቶ ፡ ፪ ፡ ፲፬ ።
ጢአት ፡ ምኞት ፡ በብርታት ፡ ሲነሣባቸውና ፡ ሲያሠ
ቃያቸው ፡ ያገኙታል ፤ ግን ፡ በክርስቶስ ፡ ሥጋ ፡ እነ ፤ ሮሜ ፡ ፯ ፡ ፭ ።
እርሱ ፡ ራሳቸው ፡ ለሕግ ፡ እንደ ፡ ሞቱ ፡ ቢቈጥሩ ፡ ፡ ገላ ፡ ፪ ፡ ፲፱ ፡ ፳ ።
የሕግ ፡ ጽድቅ ፡ በእነርሱ ፡ ሲፈጸም ፡ መልካም ፡ የሆ ፡ ሮሜ ፡ ፰ ፡ ፬
ነችውና ፡ ፍጹም ፡ የሆነች ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡
በሕይወታቸው ፡ አብርታ ፡ ትታያለች ። ቢሆንም ፡ ። ሮሜ ፡ ፲፪ ፡ ፪ ።
ለዚህ ፡ ድል ፡ መንሣት ፡ የበቁት ፡ በመንፈስ ፡ እየተ ፡ ፩ቆሮ ፡ ፲፭ ፡ ፶፮ ፡ ፶፯ ።
መላለሱ ፡ ለሕግ ፡ በመሞታቸው ፡ እንጅ ፡ በሕግ ፡ ፡ ገላ ፡ ፭ ፡ ፲፰ ።
እርዳታ ፡ ወይም ፡ እነርሱ ፡ ሕግን ፡ ስለጠበቁአት ፡
እንዳልሆነ ፡ እናምናለን ። ። ገላ ፡ ፭ ፡ ፲፩-፲፯ ።

እምቃለ ፡ ጳውሎስ ፡ ገላትያ ፡ ፊልጎስ ፡ ሲተጕረም ፡ እንደ ፡ ገለጠው ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለን ፡ የጻፍነውን ፡ ማየት ፡ ይጠቅማል ።

ጥቅስ ፡ ‹‹ኦሪትሰ ፡ ለእለ ፡ ኢፈጸሙ ፡ ገቢሮታ ፡ ትረግም ፡ ወትብል ፡ ውጉዝ ፡ ወርጉም ፡ ውእቱ ፡ ዘኢፈጸመ ፡ ገቢረ ፡ በተጠናቅቆ ፡ ኵሎ ፡ ዘጽሑፍ ፡ -----ወዕበ ፡ ስሕተ ፡ በአሐቲ ፡ እስከ ፡ ጥቀ ፡ በአልፋ ፡ ነያ ፡ እንተ ፡ አሐቲ ፡ ቀርጸታ ፡ ርጉም ፡ ውእቱ ፡ ወስሕተ ፡ በኵሉ ፡ ዘውስቴታ ፡ በወንጌልሰ ፡ ዘአምነ ፡ ይጸድቅ ፡ በከመ ፡ አብርሃም ፡ አሚኖ ፡ ጸድቀ ፡ ወዘእንበለ ፡ አሚን ፡ ኢይጸድቁ ፡ እስመ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ኢአምኑ ፡ ወኢተጠምቁ ፡ ውስተ ፡ መርገመ ፡ ኦሪት ፡ ይነብሩ ፡ እስመ ፡ ኢክህሉ ፡ ፈጽሞታ ፡ ---------ወተሣየጠነ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸዊሮ ፡ መርገመነ ፡ ወተዐገሠ ፡ በእንቲአነ ፡ በዲበ ፡ ዕፀ ፡ መስቀል ፡ ተመሲሎ ፡ አምሳለ ፡ አርዌ ፡ ምድር ፡ ወዓዲ ፡ ውእቱ ፡ መጽሐፈ ፡ ሕግ ፡ ይቤ ፡ ርጉም ፡ ኵሉ ፡ ዘስቁል ፡ ዲበ ፡ ዕፅ ፡ ወአምላክነሰ ፡ ተመሲሎ ፡ ኪያነ ፡ ወነሢአ ፡ መርገመነ ፡ አግብአ ፡ በረከቶ ፡ ለአብርሃም ፡ ላዕሌነ ፡ እስመ ፡ አመነ ፡ ቦቱ ፡ ወአብርሃምኒ ፡ አሚኖ ፡ ጸድቀ ፡ ወረከብነ ፡ ጸጋሁ ፡ ለአብርሃም ፡ ወዝ ፡ ውእቱ ፡ ጥምቀትነ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ።

ትርጓሜ ፡ ኦሪት ፡ ግን ፡ ማድረጓን ፡ ላልፈጸሙ ፡ ትረግማለች ፤ የተጻፈውንም ፡ ሁሉ ፡ በጥንቃቄ ፡ ያልፈጸመ ፡ ውጉዝ ፡ ርጉም ፡ ነው ፤ ትላለች ። -------- አንዲት ፡ ነጥብ ፡ በምትሆን ፡ በአልፋ ፡ እንኳን ፡ ቢስት ፡ በእርስዋ ፡ ባለው ፡ ሁሉ ፡ የሳተ ፡ ነውና ፡ ርጉም ፡ ነው ። በወንጌል ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ አብርሃም ፡ አምኖ ፡ እንደ ፡ ጸደቀ ፡ ሁሉ ፡ ያመነ ፡ ይጸድቃል ። ያለሃይማኖት ፡ ግን ፡ ለመጽደቅ ፡ አይቻልም ። መፈጸምዋን ፡ አይችሉምና ፡ ያላመኑ ፡ ያልተጠመቁ ፡ ሁሉ ፡ ከኦሪት ፡ መርገም ፡ በታች ፡ ናቸው ። ----- ክርስቶስ ፡ ግን ፡ መርገማችንን ፡ ተሸክሞ ፡ ከኦሪት ፡ መርገም ፡ ገዛን ። በአርዌ ፡ ምድር ፡ ምሳሌ ፡ ተመስሎም ፡ በዕፀ ፡ መስቀል ፡ ላይ ፡ ስለኛ ፡ ታገሠልን ። ዳግም ፡ እርሱ ፡ መጽሐፈ ፡ ሕግ ፡- "በእንጨት ፡ ላይ ፡ የተሰቀለ ፡ ርጉም ፡ ነው ፡" ይላል ። አምላካችን ፡ ግን ፡ እኛን ፡ መስሎ ፡ መርገማችንን ፡ ተሸክሞ ፡ የአብርሃምን ፡ በረከት ፡ ለእኛ ፡ መለሰልን ፤ አምነንበታልና ! አብርሃምም ፡ የጸደቀው ፡ አምኖ ፡ ነው ። የአብርሃምን ፡ ጸጋ ፡ አገኘን ፤ ይኸውም ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የሚሆን ፡ ጥምቀታችን ፡ ነው ።" ብሎአል ።

ጥቅስ ፡ ቅዱስ ፡ ቄርሎስም ፡- "ናሙት ፡ ሥጋነ ፡ እምኦሪት ፡ ከመ ፡ ናዕርፍ ፡ እምቅኔ ፤ ወንኩን ፡ ለካልዕ ፡ ዘተንሥአ ፡ እሙታን ፡ ዘውእቱ ፡ ክርስቶስ ፡ ወንትሉ ፡ ትእዛዘ ፡ ወንጌሉ ፡ በጸጋሁ ፡ ከመ ፡ ንኩን ፡ ፍሬ ፡ ለእግዚአብሔር ፤ ወቃለ ፡ ትእዛዙሰ ፡ ለወንጌል ፡ ይእቲ ፡ ሃይማኖት ፡ እንተ ፡ ኮነት ፡ ቦቱ ።

ትርጓሜ ፡ በባርነት ፡ ከመገዛት ፡ እናርፍ ፡ ዘንድ ፡ ሥጋችንን ፡ ከኦሪት ፡ እንግደል ፤ ከሙታን ፡ ለተነሣው ፡ ለሌላው ፡ ይኸውም ፡ ለክርስቶስ ፡ እንሁን ፤ የእግዚአብሔር ፡ ፍሬም ፡ እንሆን ፡ ዘንድ ፡ በጸጋው ፡ የወንጌሉን ፡ ትእዛዝ ፡ እንከተል ። የወንጌል ፡ ትእዛዝ ፡ ስንልም ፡ በእርሱ ፡ የምትሆን ፡ ሃይማኖት ፡ ናት ፤" ብሎአል ።

## ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቁጣ ፡ (መዓት) ።

በባሕርዩ ፡ ቅዱስ ፡ የሆነ ፡ እግዚአብሔር ፡ በቅዱስ ፡ ፍቅሩ ፡ ሰውን ፡ ሲፈጥር ፡ ከቅድስናው ፡ ሥርዓት ፡ ወጥተው ፡ የተገኙት ፡ ሁሉ ፡ ቅዱስ ፡ ሕጉን ፡ ተላልፈውና ፡ ፈቃዱን ፡ በመርገጥ ፡ ተቃውመው ፡ ስለሚያያቸው ፡ ከተቀደሰ ፡ ሕይወቱ ፡ ጋር ፡ ሊኖሩና ፡ ሊካፈሉ ፡ ካለመቻላቸው ፡ በላይ ፡ እነርሱን ፡ በወደደ በት ፡ ፍቅሩ ፡ መጠን ፡ ቁጣው ፡ ወርዶባቸው ፡ በዘለ ዓለም ፡ ሥቃይ ፡ ቢኰንናቸው ፤ "የሚገባ ፡ የበጎ ፡ ባሕርዩ ፡ ሥርዓት ፡ ነው ፡ ቢባል ፡ እንጅ ፡ ቁጣው ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ነው ፡" ተብሎ ፡ መታሰብ ፡ እንደሌለ በት ፤

፩ ሳሙ ፡ ፪ ፡ ፪ ። ኢሳ ፡ ፶፫ ፡ ፳፭ ። ዘሌዋ ፡ ፲፱ ፡ ፪ ። ዕብ ፡ ፲ ፡ ፳፰ ፡ ፴፩ ። ኢሳ ፡ ፳፭ ፡ ፲፩ ፡ ፲፱ ። ኤር ፡ ፲፯ ፡ ፲፬ ። ዘሌዋ ፡ ፲ ፡ ፪ ። ዮሐ ፡ ፫ ፡ ፲፰ ፡ ፴፮ ። ሶፎ ፡ ፫ ፡ ፭ ። እንባ ፡ ፪ ፡ ፰ ።

ይህም ፡ መዓቱ ፡ ዱሮውኑ ፡ ቅድስናው ፡ በሚ ፈቅድለት ፡ መጠን ፡ በጽድቅና ፡ በርትዕ ፡ ተስተካ ክሎ ፡ የሚወጣ ፡ በመሆኑ ፡ ልቡን ፡ በሚያለዝብለት ፡ ራሱ ፡ ባቆመው ፡ ማስተሥረያነትና ፡ ኃጢአተኛም ፡ ይህ ፡ መከራ ፡ እንደሚመጣበት ፡ አይቶ ፡ በንስሓ ፡ ራሱን ፡ ዝቅ ፡ አድርጎና ፡ በእምነትም ፡ በአምላካዊ ፡ ማስ ተሥረያ ፡ ተማፅኖ ፡ ከሚያገኘው ፡ ምሕረት ፡ በስተቀር ፡ የተሰነዘረው ፡ ቁጣ ፡ በገሃነም ፡ እስኪጥል ፡ ድረስ ፡ ይቃጠላል ፡ እንጅ ፡ እንዲሁ ፡ ሊበርድ ፡ እንደማይችል ፡ እናምናለን ።

እንባ ፡ ፩ ፡ ፲፫ ፡ ፲፭ ። ራዕ ፡ ፲፩ ፡ ፫ ፡ ፯ ። ሮሜ ፡ ፫ ፡ ፳፩ ። ኢሳ ፡ ፩ ፡ ፲፰-፳ ። መዝ ፡ ፴፪ ፡ ፭ ። ዕብ ፡ ፬ ፡ ፲፮ ፡ ኢሳ ፡ ፲፬ ፡ ፳፩ ፡ ፳፯ ። ራዕ ፡ ፲፬ ፡ ፲ ፡ ፲፩ ። ናሆ ፡ ፩ ፡ ፪-፰ ። ኢሳ ፡ ፩ ፡ ፳፬ ፡ ፳፭ ።

ስለዚህም ፡ ቅዱስ ፡ ያሬድ ፡-

ጥቅስ ፡ "ጽድቅ ፡ ቃሉ ፡ ወጽድቀ ፡ ይኴንን ፡ በመንግሥቱ ፡ ወአልቦ ፡ ዐመፃ ፡ በኀቤሁ ።

ትርጓሜ ፡ ቃሉ ፡ ጽድቅ ፡ ነው ፡ በመንግሥቱም ፡ በጽድቅ ፡ ይፈርዳል ፡ የዐመፃ ፡ ነገርም ፡ በእርሱ ፡ ዘንድ ፡ የለም" ፡ ብሎአል ።

ጥቅስ ፣ መተርጕምም ፡ - "እግዚአብሔር ፡ ቀናኢ ፡ ወመስተ በቅል ፡ ዘይቤ ፡ አኮ ፡ እምግዕዙ ፡ ወልማዱ ፣ አላ ፡ ለእለ ፡ አበዩ ፡ ተመ ይጠ ፡ እምግባር ፡ ዘኢያሠምሮ ።

ትርጓሜ ፣ እግዚአብሔር ፡ ቀናተኛና ፡ ተበቃይ ፡ ነው ፡ የተባለ በት ፡ ከማያስደስተው፡ ተግባር ፡ መመለስን፡ እንቢ ፡ ለሚሉ ፡ ነው ፡ እንጅ ፣ ጠባዩና ፡ ልማዱ ፡ በመሆኑ ፡ አይደለም ።" ሲል ፡ ተርጉሞአል።

ጥቅስ ፣ ብንያሚንም ፡- " ዘይብል ፡ ሶበሰ ፡ ፈቀደ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ እምኢኰነኖሙ ፡ ለሰብእ ፡ ይደመሰስ ፡ ስሙ ፡ እመጽሐፈ ፡ ሕይ ወት ።

ትርጓሜ ፣ እግዚአብሔር ፡ ሲያሻው ፡ ሰዎችን ፡ ላይፈርድባ ቸው ፡ ይችላል ፡ ለሚል ፡ ሰው ፡ ስሙ ፣ ከሕይወት ፡ መጽሐፍ ፡ ይደመ ሰሳል ።" ብሎ ፡ አስረድቶአል ።

ስለዚህ ፣ የነመርቄሎንና ፡ የተከታዮቹን ፣ የመሐመድን ፡ ትም ህርት ፣ እንደዚሁ ፡ ይህ ፡ ቁጣ ፡ ኃጢአት ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፣ ከእርሱ ፡ እንደሚወጣ ፡ አድርገው ፡ የሚያስቡት ፤ ደግሞ ፡ የሚሳነው ፡ ነገር ፡ የለም ፡ እያሉ ፡ ሲያፌዙ ፡ ከባሕርያዊ ፡ ቅድስናው ፡ መደብ ፡ አውጥተው ፡ ኃጢአት ፡ ሠሪ ፡ ለማድረግ ፡ የሚሞክሩት ፤ እንዲሁም ፡ በራሱ ፡ ማስተሥረያነት ፡ ሳይሆን ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ እንደሚቀርና ፡ እንደ ሚበርድ ፡ አድርገው ፡ የሚያስተምሩት ፡ ሁሉ ፤ መዓቱ ፡ ዱሮውኑ ፡ በጽድቅና ፡ በርትዕ ፡ እንዳልወጣ ፡ ማድረጋቸው ፡ ነውና ፣ ኃጢአት ፡ እንዳለበት ፡ በማሰባቸው ፡ ቅዱስ፡ ጠባዩን ፡ ክደዋል ፤ ስንል ፡ መናፍ ቅነታቸውን ፡ እንገልጻለን ።



## ፪ ፡ ክፍል ።

### ፲ኛ ፡ አንቀጽ ።

### ስለ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስና ፡ ስለ፡ መድኃኒትነቱ ።

በመለኮቱ ፡ ከአብ ፡ ጋር ፡ አንድነት ፡ ያለው ፣ ፣ ዮሐ ፣ ፲ ፣ ፴ ።
የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወልድ ፣ ልጅነቱ ፡ ተገቢና ፡ ፣ ዮሐ ፣ ፩ ፣ ፩ ፣ ፲፰ ።
ባሕርያዊ ፣ ብርሃን ፡ ዘእምብርሃን ፡ የሆነ ፡ የአብ ፡
ዘለዓለማዊ ፡ ልጁ ፡ ነው ። ከዚያውም ፡ ዘንድ ፡ በእግ ። መዝ ፣ ፪ ፣ ፯ ።
ዚአብሔር ፡ መልክ ፡ ሲኖር ፣ በሕግ ፡ አኳኋንና ፡ በማ ፣ ሕዝ ፣ ፩ ፣ ፳፮ ።
ናቸውም ፡ አድራጎት ፡ ሊድን ፡ ላልተቻለው ፡ ዓለም ፣ ፣ ሮሜ ፣ ፫ ፣ ፲፱ ።
ከኩነኔ ፡ ከኃጢአትም ፡ አድኖ ፡ የዘለዓለምን ፡ ሕይ
ወት ፡ ይሰጥ ፡ ዘንድ ፣ በፈቃዱና ፡ በሥምረቱ፡ ራሱን ፡ ፣ ቲቶ ፣ ፫ ፣ ፬-፯ ።
ዝቅ ፡ ዝቅ ፡ ባደረገበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፣የክብሩንና ፡ የተ ፣ ፪ቆሮ ፣ ፰ ፣ ፱ ።
ድላ ፡ መንግሥቱን ፡ ምልዓት ፡ እንደ ፡ መቀማት ፡
ያህል ፡ አድርጎ ፡ ሳይቈጥር ፣ ከድንግል ፡ ማርያም ፡ ፣ ፊልጵ ፣ ፪ ፣ ፮ ፣ ፯ ።
ተወልዶ ፣ ሰው ፡ ሆነና ፣ ከኃጢአት ፡ በቀር ፡ እኛን ፡ ፣ ማቴ ፣ ፩ ፣ ፲፰-፳፭ ።
መሰለ ። ። ዕብ ፣ ፬ ፣ ፲፭ ።

ስለዚህም ፡ በእግዚአብሔርና ፡ በሰው ፡ መካ
ከል ፡ ሆኖ ፡ የሚያስታርቅ ፡ መካከለኛ ፣ እኛንም ፡ ፣ ፩፣ ጢሞ፣ ፪፣፭፣፮።
የሚያድን ፡ ማሕየዊ ፣ ይኸው ፡ በአምላክነትና ፡ በሰ ፣ ሆሴ ፣ ፮ ፣ ፪ ።
ውነት ፡ አንድ ፡ የሆነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ። ። ሮሜ ፣ ፩ ፣ ፫ ፣ ፬ ፣

በመሢሕነቱ ፡ ፍጹም ፡ ጠባቂ ፣ ታላቅ ፡ ነቢ ፣ የሐዋ፣ሥ፣ ፲ ፣ ፴፰ ።
ይና ፡ ዓይነተኛው ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፣ ዘለዓለማዊም ፡ ፣ ዕብ ፣ ፲፫ ፣ ፰ ።
ንጉሣችን ፡ የሆነ፣ በአንዲት ፡ ተዋሕዶተ ፡ ህላዌ ፡ ፣ ኢሳ ፣ ፱ ፣ ፮ ፣ ፯ ።
የሚሰገድለት ፡ ይህ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ብቻ፡ ነው። ። ዳን ፣ ፯ ፣ ፲፫፣፲፬ ።

ለዘመዶቹ ፡ እየታዘዘ ፡ አድጎ ፣ በ፴ ፡ ዓመቱ ፡ ፣ ሉቃ ፣ ፪ ፣ ፶፩ ።
ከዮሐንስ ፡ በዮርዳኖስ ፡ ሲጠመቅ ፣ እውነተኛ ፡ መሢ
ሕና ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ መሆኑን ፡ ከአብና ፡ መዝ ፣ ፪ ፣ ፯ ፣ ፲፪ ።
ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በግልጽ ፡ ተመሰከረለት ። ከሰይ ። ሉቃ፣ ፫፣ ፳፩-፳፪ ።

ጣንም ፡ ተፈትኖ ፡ ድል ፡ ካደረገ ፡ በኋላ ፡ ምስክሮቹ ፡ ፤ ማቴ ፡ ፬ ፡ ፩-፲፩ ።
የሚሆኑትን ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ መርጠ ፡ የእግዚአ ፤ ዮሐ፡ ፲፩፡ ፲፭፡ ፲፱፡
ብሔርን ፡ መንግሥት ፡ ጽድቅንም ፡ አስተማረ ። ።፩፡ጴጥ፡፪፡፳፩-፳፫።
ያስተማረውንም ፡ በሕይወቱ ፡ ይገልጸው ፡ ነበር ፤
ሥራውንም ፡ በአምላካዊ ፡ ተአምር ፡ አጸደቀው ። ። ሉቃ ፡ ፳፬ ፡ ፲፱ ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ኃጢአትን ፡ ሳያውቅ ፡ እንደ ፤ ፪ ፡ ቆሮ፡ ፭፡ ፳፩ ።
ኃጢአተኛ ፡ እስኪቈጠር ፡ ድረስ ፡ ለእኛ ፡ ሲል ፡ በመ ፤ ኢሳ፡፶፫፡ ፲፩፡ ፲፪።
ስቀል ፡ ላይ ፡ ሞቶ ፡ ተቀበረና ፤ ከሙታን ፡ ተለይቶ ፡ ፤ ማቴ ፡፳፯፡ ፶ ፡ ፳፰።
በሥጋና ፡ በዐፅም ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ በመነሣቱ ፡ ፤ የሐ፡ሥ፡፪፡፳፬-፴፪።
ስለ ፡ እኛ ፡ ጽድቅ ፡ የተደረገውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡
ፈቃድ ፡ ምክሩንም ፡ ገለጸ ። ለዓለም ፡ ኃጢአት ፡ ።ሮሜ፡፬ ፡ ፳፬፡፳፭።
ሁሉ ፡ ባደረገው ፡ መታረቂያ ፡ ወይም ፡ ማቅረቢያ ፡ ኤፌ ፡ ፩ ፡ ፯ ።
መሥዋዕትና ፡ በቅዱስ ፡ ታዛዥነት ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ ፤ ዕብ ፡ ፩ ፡ ፮-፲ ።
በመገዛቱ ፡ ጽድቅን ፡ ሁሉ ፡ ከፈጸመ ፡ በኋላ ፡ በእርሱ፡ ፤ ዕብ ፡ ፲ ፡ ፲ ፡ ፲፬ ።
በኩል ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሚመጡት ፡ ሁሉ ፡ ፤ ም ፡ ፯ ፡ ፳፭ ።
አንድ ፡ ጊዜ ፡ በሆነው ፡ አስታራቂነቱ ፡ ሳያቋርጥ ፡
ወደሚቀበልበት ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ዐረገና ፡ በታላቅ ፤ ፩፡ ዮሐ፡ ፪፡፩ ፡ ፪ ።
ነት ፡ ዙፋን ፡ በአባቱ ፡ የኃይል ፡ ቀኝ ፡ ተቀመጠ ። ዕብ ፡ ፰ ፡ ፩ ። ። መዝ ፡ ፻፲ ፡ ፩ ።
የአዲስ ፡ ሕይወት ፡ ኃይልና ፡ የጸጋው ፡ ምላት ፡ የሆነ፡
ራሱን ፡ እንዲያካፍላቸው ፡ በሚያምኑበት ፡ ልብ ፡ ፤ ዮሐ፡ ፮፡ ፶፩፡ ፶፯ ።
ውስጥ ፡ አድሮ ፡ ለሁል ፡ ጊዜ ፡ ይኖራል ። እንዲሁም፡ ። ኤፌ፡ ፫፡ ፲፯-፲፱ ።
በሕያዋንና ፡ በሙታን ፡ ሊፈርድ ፡ ዳግመኛ ፡ ተመ
ልሶ ፡ ይመጣል ። ።ማቴ፳፭፡፴፩-፵፮።

እንግዲያውስ ፡ እርሱ ፡ መንገድ ፡ ሕይወት ፡
የሰማይና ፡ የምድር ፡ መሰላል ፡ የመድኃኒት ፡ ቀንድ ፡ ዮሐ ፡ ፲፬ ፡ ፮ ።
የማዕዘን ፡ ደንጊያ ፡ የሕይወት ፡ ብርሃን ፡ የሕይወት ፡ ሉቃ፡ ፩፡ ፸፰ ፡ ፸፱።
ራስ ፡ ከሞት ፡ ወደ ፡ ሕይወት ፡ የምንሸጋገርበት ፡ ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፬ ፡ ፶፱ ። ዮሐ ፡ ፭ ፡ ፳፬ ።
ድልድይ ፡ ሆኖ ፡ በተረጋገጠ ፡ አምላካዊ ፡ ድርጅት ፡ ፤ ኤፌ ፡ ፩ ፡ ፳-፳፪ ።
ከሰማይ ፡ በታች ፡ ለሰው ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ ደኅንነት ፡
የተሰጠን ፡ የእርሱ ፡ አዳኝ ፡ ስም ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ስንል፤ የሐዋ ፡ ፬ ፡ ፲-፲፪ ።
እናምናለን ። ። የሐዋ፡ሥ፡፬፡፳፫ ።





ይህንም ፡ እምነት ፡ የጥንት ፡ ኦርቶዶክሳውያን ፡ መምህራን ፡ በየድርሳናቸው ፡ አስረድተው ፡ ጽፈዋል ። ከእነዚህም ፡ ኤራቅሊስ ፡ በሃይማኖተ ፡ አበው ፡ በድርሳነ ፡ ትሥጉት ፡ ክፍል ፡ የሚቀጥለውን፡ ቃል ፡ ተናገረ ።

ጥቅስ ፡ "ኮነ ፡ ወልደ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡ ዘበአማን ፡ ወውእቱ ፡ ፍኖት ፡ ዘይመርሀነ ፡ ኀበ ፡ አቡሁ ፡ ቅዱስ ፤ ወውእቱ ፡ አንቀጽ ፡ ዘያበውዕ ፡ ውስተ ፡ ገነተ ፡ ተድላ ፡ ውእቱ ፡ ኖላዊ ፡ ዘይሴአል ፡ በእንተ ፡ በግዑ ፤ዘተገድፈ ፡ ውእቱመ ፡ በግዕ ፡ ዘተጠብሐ ፡ በእንተ ፡ ሕይወተ ፡ ኵሉ ፡ዓለ ም ፡ ወአንጽሐ ፡ ኵሎ፡ ዓለመ፡ እንበለ ፡ ርኵስ። በዓይ ፡ አምሳል ፡ ናስተማስል ፡ ሥርዓቶ ፤ ውእቱ ፡ እንበለ ፡ ውላጤ ፡ በህላዌ፡ መለኮቱ ፡ ውእቱ ፡ አምላክ ፡ በዘቦቱ ፡ ውእቱ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ በዘኮነ ፡ ቦቱ ፡ ወውእቱ ፡ እንበለ ፡ እም ፡ በዘይፈደፍድ ፡ እምኔነ ።

ትርጓሜ፡ እርሱም ፡ በእውነት ፡ ሰው ፡ የሆነ ፡ ወደ ፡ ቅዱስ ፡ አባቱ ፡ የሚመራን ፡ መንገድ ፡ ነው ። ወደ ፡ ተድላ ፡ ገነት ፡ የሚያገባ ፡ በር ፡ እርሱ ፡ ነው ፤ ስለ ፡ ጠፋው ፡ በጉንም ፡ የሚፈልግ ፡ እረኛ ፡ እርሱ፡ ነው ፤ ስለ ፡ ዓለም ፡ ሁሉ ፡ የታረደ ፡ ዓለሙንም ፡ ሁሉ ፡ ያለነውር ፡ ያነጻ ፡ በግ ፡ እርሱ ፡ ነው ፤ የሥርዓቱን ፡ አኳኋን ፡ በምን ፡ ምሳሌ ፡ እና መሳስል ? በመለኮቱ ፡ አንዋንዋር ፡ ያለመለወጥ ፡ ነው ። ባለበትም ፡ አምላክ ፡ ነው ። በሆነበትም ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ነው ። ከእኛ ፡ በሚበልጥበት ፡ ረገድም ፡ ያለእናት ፡ የሆነ ፡ እርሱ ፡ ነው ፤" ብሎአል ።

ስለዚህ ፡ በክርስቶስ ፡ ከሚገኘው ፡ ደኅንነት ፡ በቀር ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በሚያምነውና ፡ በሚያስታውቀው ፡ ሥርዓት ፡ ራሱም ፡ ፈልስፎ ፡ ባወጣው ፡ ወይም ፡ ኀሳቡን ፡ ተከትሎና ፡ ምትሐትን ፡ ተመልክቶ ፡ በሚያደርገው ፡ መለየት ፡ የሰማይ ፡ መልአክ ፡ ስንኳ ፡ ቢያስተምረው ፡ ይድናል ፡ ማለት ፡ ይህን ፡ እምነት ፡ ይቃወማል ። እንዲሁም ፡ የየማኅበሩ ፡ መከፋፈል ፡ በማየትና ፡ በምትታይ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥም ፡ ክፉዎችን ፡ ሰዎች ፡ በመመልከት ፡ እውነተኛይቱ ፡ የክርስትና ፡ ሃይማኖት ፡ የት ፡ እንዳለች ፡ አትታወቅምና ፡ ማንም ፡ ቢሆን ፡ የአባቶቹን ፡ ልማድ ፡ ቢጠብቅ ፡ ይድናል ፡ የሚሉትን፤ ተስፋቸውንም ፡

በኦሪትና ፡ በሰው ፡ ሥራ ፡ ጽድቅ ፡ ጥለው ፡ እንድናለን ፡ ብለው ፡ ራሳቸውን ፡ የሚያታልሉትን፡ ሁሉ ፤ ለእኛ ፡ ክርስቶስ ፡ ብቻ ፡ መድኃኒት ፡ ሆኖልናልና ፡ አንከተላቸውም ።



፲፩ኛ ፡ አንቀጽ ።

## ምሥጢረ ፡ ትሥጉት ፡ (ተዋሕዶ) ።

ነዋሪና ፡ እውነተኛ ፡ አምላክ ፡ የሆነ ፡ በዘለዓለማዊ ፡ ልደትም ፡ ከአብ ፡ የተወለደ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወልድ ፡ በኋለኛው ፡ ዘመን ፡ እኛን ፡ ሊያድን ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ የሰው ፡ ጠባይዕ ፡ የሆኑትን ፡ ነፍስን ፡ ሥጋን ፡ መንፈስን ፡ ተገንዝቦ ፡ ከኃጢአት ፡ በቀር ፡ ፈጽሞ ፡ መወሐዱን ፤

ፍጹማንና ፡ ምሉዓን ፡ የሆኑት ፡ መለኮቱና ፡ ሰውነቱም ፡ የባሕርይ ፡ መደባለቅና ፡ መለወጥ ፡ የአቅዋም ፡ ሽረትና ፡ ፍልሰት ፡ ሳይኖርባቸው ፡ ጭራሹን ፡ ያለመለየትና ፡ ያለመከፈል ፡ በአንዱ ፡ የአካል ፡ ተዋሕዶ ፡ አንድ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መሆኑን ፤ እናምናለን ።

ይህችም ፡ ጥንቁቅ ፡ የሆነችና ፡ የደኅንነታችን ፡ ኃይል ፡ ያላት ፡ የተዋሕዶ ፡ እምነታችን ፡ እዚሁ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ባሉት ፡ አንቀጾች ፡ እንደሚከተለው ፡ እየዘረዘረች ፡ ከምታሳጣቸው ፡ መናፍቃንና ፡ ስሕተቶች ፡ ሁሉ ፡ ትጠብቀናለች ።

፭ኛ ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ አምላክነትና ፡ ፍጹም ፡ ሰውነት ፡ የምትክደውን ፡ አርዮሳዊት ፡ ትምህርትንና ፡ ተከታዮችዋን ፡ እንርቃለን ። ምክንያቱም ፡ የተዋሕዶ ፡ ሃይማኖታችን ፡ መሠረት ፡ የሆነው ፡ ቅዱስ ፡ መጽሐፍ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ በተሰጠን ፡ ሃይማኖት ፡ እንዴት ፡ አድርገን ፡ ልንመካ ፡ እንደምንችል ፡ ሊካድ ፡ ከማይቻል ፡ መጽናናቱ ፡ ጋር ፡ እየገለጸ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መካከለኛ ፡ ሆኖ ፡ ሰውንና ፡ እግዚአብሔርን ፡ ማስታረቁን ፤ (፩ ፡ ጢሞ ፡ ፪፡ ፭፡ ፮። ዕብ፡ ፱፡ ፲፭፡) እኛን ፡ ማዳኑን ፤ (ዕብ ፡ ፪ ፡ ፲፬ ፡ ፲፭ ።)

እርሱ ፡ ሰይጣንን ፡ በቅን ፡ ፍርድ ፡ ማስሸነፉን ፤ (ዮሐ ፡ ፲፪ ፡ ፴፪ ። ፩ ፡ ዮሐ ፡ ፫ ፡ ፰ ።)

በእርሱ ፡ ከአብ ፡ ጋር ፡ አንድነት ፡ ማግኘታችንን ፤ (ዮሐ ፡ ፲፯ ፡ ፳፩-፳፫። ፩ ፡ ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፫ ።)

በእርሱም ፡ እግዚአብሔር ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ መሆኑን ፤ (ሮሜ ፡ ፰ ፡ ፴፮ ። ቆላ ፡ ፪ ፡ ፱ ፡ ፲ ።) እንደ ፡ ሠራልን ፡ ነግሮናል ።

እንግዴህ ፡ አምላክ ፡ ዘእምአምላክ ፡ የሚሆን ፡ ራሱ ፡ ሰው ፡ ባይሆንልን ፤ በሰውና ፡ በእግዚአብሔር ፡ መካከለኛ ፡ ሳይኖር ፡ ዕርቁ ፡ እንዴት ፡ ተገኘልን ? (ዕብ ፡ ፩ ፡ ፩-፫ ። ፪ ፡ ቆሮ ፡ ፭ ፡ ፲፱ ። ቆላ ፡ ፩ ፡ ፲፱ ፡ ፳ ።)

መዳናችንስ ፡ ከመለኮትነቱ ፡ ባይሰጠን ፤ ነዋሪው ፡ ደኅንነት ፡ እንዴት ፡ ጸናልን ? (ሉቃ ፡ ፩ ፡ ፳፰-፴፭ ። የሐዋ ፡ ሥ ፡ ፬ ፡ ፲፪ ። ማቴ ፡ ፩ ፡ ፳፩ ። ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፩ ፡ ፫-፭ ። መዝ ፡ ፫ ፡ ፰ ።)

ፍጹም ፡ ሰው ፡ በመሆን ፡ ታዝዞ ፡ የሰዎችን ፡ ጠላት ፡ (ሰይጣንን) ፡ ካላስሸነፈ ፤ ጠላቱ ፡ ቅን ፡ በሆነው ፡ ፍርድ ፡ እንዴት ፡ ተሸነፈ ? (ዕብ ፡ ፭ ፡ ፰ ፡ ፱ ። ም ፡ ፪ ፡ ፱-፲፰ ። ፩ ፡ ዮሐ ፡ ፬ ፡ ፫ ። ቆላ ፡ ፪ ፡ ፱-፲፭ ።)

አምላክነቱና ፡ ሰውነቱ ፡ ባይዋሐድልን ፤ ከአብ ፡ ጋር ፡ ያለው ፡ አንድነታችን ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ የሆነልን ? (ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፲፬-፲፯ ። ፩ ፡ ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፫-፯ ።)

አምላክነቱ ፡ ከሰውነቱ ፡ ጋር ፡ በመዋሐድ ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ካል ሆነ ፤ ስሙ ፡ ለምን ፡ አማኑኤል ፡ ተባለ ? (ማቴ ፡ ፩ ፡ ፳፫ ። ፪ ፡ ጴጥ ፡ ፩ ፡ ፬ ። ቆላ ፡ ፪ ፡ ፱ ። ፩ ፡ ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፲፭ ፡ ፲፯ ።) እያልን ፡ ብንጠይቃቸው ፡ የዚህን ፡ ማስረጃ ፡ ጥቅም ፡ ያልተረዱ ፡ ወይም ፡ የማይፈልጉ ፡ በመሆ ናቸው ፡ አፋቸው ፡ ይዘጋል ፡ እንጅ ፡ የእውነተኛ ፡ ተነሳሒና ፡ የክርስ ቲያን ፡ መልስ ፡ አይሰጡንምና ፡ በዚህ ፡ ማስረጃችን ፡ እየተቃወምና ቸው ፡ ሕፀፅ ፡ የሌለበት ፡ አምላክነትና ፡ (ዮሐ ፡ ፲ ፡ ፴ ። ም ፡ ፲፬ ፡ ፱-፲፩ ። ጉድለት ፡ የሌለው ፡ ሰውነት ፡ (ዕብ ፡ ፪ ፡ ፲፯ ፡ ፲፰ ።) በአንድ ፡ ተዋሕዶ ፡ በአዳነን ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እናምናለን ።

፪ኛ ፡ ተዋሕዶ ፡ በመደባለቅ ፡ መጠን ፡ እንደሆነ ፡ ከምታስብ ፡ ወይም ፡ የክርስቶስ ፡ ሰውነት ፡ ወደ ፡ አምላክነቱ ፡ ተለውጦአልና ፡ የክርስቶስ ፡ የሞቱ ፡ ሥቃይና ፡ መከራ ፡ እንደምትሐት ፡ ነበረ ፡ እንጅ ፡ ፈጽሞ ፡ አልተሰማውም ፡ ከምትለው ፡ ከአውጣኬ ፡ ከንቱነት ፡ የማንገ ናኝበት ፡ ቀጥሎ ፡ ተጽፎአል ። "የክርስቶስ ፡ ተዋሕዶ ፡ በመደባለቅ ፡ ወይም ፡ በመለወጥ ፡ መጠን ፡ ነበር ፡ ማለት ፡ " ሥጋም ፡ ጽንዓተ ፡





አካሉን ፡ ትቶ ፡ ህላዌ ፡ መለኮት ፡ ሆኖአል ፡ ማለትን ፡ የሚያስከትል ፡ ነው ። "ሥጋ ፡ ደግሞ ፡ ጽንዓተ ፡ አካሉን ፡ ትቶ ፡ ህላዌ ፡ መለኮት ፡ ሆኖአል ፡ ሲባል ፡" ኢየሱስ ፡ ከልደቱ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዕርገቱ ፡ ያደረ ጋቸው ፡ እንደ ፡ መድከም ፡ እንደ ፡ መራብ ፡ እንደ ፡ መሰቀል ፡ እንደ ፡ መሞት ፡ ከሙታንም ፡ እንደ ፡ መነሣት ፡ የመሳሰሉ ፡ ሁሉ ፡ (ዮሐ ፡ ፬ ፡ ፮ ፡ ሉቃ ፡ ፬ ፡ ፪ ። ማቴ ፡ ፳፯ ፡ ፴፭ ። ማር ፡ ፲፭ ፡ ፴፯ ። ዮሐ ፡ ፲፱ ፡ ፴ ።) በምትሐት ፡ እንጅ ፡ በእውነት ፡ አላደረጋቸውም ፡ ማለት ፡ ነው ። መቼ ም ፡ ቢሆን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ በተረጋገጠው ፡ መሠረት ፡ ክርስ ቶስ ፡ መከራን ፡ ባይቀበልና ፡ ባይሞት ፡ ዓለም ፡ አይድንም ፡ ነበረና ። (ማቴ ፡ ፲፮ ፡ ፳፩-፳፫ ።) መከራንና ፡ ሞትን ፡ የሚቀበልበት ፡ ሰውነት ፡ ተገንዝቦ ፡ ዓለምን ፡ ካላዳነ ፤ እሺ ! እንግዲህ ፡ በመደባለቅ ፡ ወይም ፡ በመለወጥ ፡ መጠንስ ፡ ቢሆን ፡ ለምን ፡ አምላክ ፡ ሰው ፡ ሆነ ? በእው ነቱ ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ተዋሕዶ ፡ ማመን ፡ ፍጹም ፡ ግድፈት ፡ ነው ።

እኛ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ አትናቴዎስ ፡ ሐዋርያዊ ፡ ትርጓሜ ፡ "አም ላክ ፡ ሰው ፡ ሆነ ፡ "ማለትን ፡ የሰውን ፡ ህላዌ ፡ ወሰደ ፡ ተቀበለ ፡ ተገ ነዘበ ፡ የራሱን ፡ አደረገ ፡ (ሉቃ ፡ ፩ ፡ ፴፭ ። ፊልጵ ፡ ፪ ፡ ፯ ። ፩ ፡ ጢሞ ፡ ፪ ፡ ፭ ።) በማለት ፡ እናምናለን ። ይህንም ፡ ስላልን ፡ "አምላክ ፡ በቅ ዱሳኑ ፡ እንደሚያድር ፡ ልክ ፡ በትስብእቱ ፡ አደረ ፡ " ማለታችን ፡ አይ ደለም ። ሊቁ ፡ ቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡- "ተዋሕዶተ ፡ እሳት ፡ ምስለ ፡ ዕፅ ፡ ልምልምት ፡ እንተ ፡ ርእየ ፡ ሙሴ ፡ በኮሬብ ፡ ያጤይቅ ፡ ተዋሕዶተ ፡ መለኮት ፡ ወትስብእት ። እሳት ፡ አምሳለ ፡ መለኮት ፡ ውእቱ ፤ ዕፅኒ ፡ አምሳለ ፡ ትስብእት ፡ ውእቱ ። ወኢመጽልዎቱ ፡ ለልምላሜ ፡ ዕፅ ፡ በተዋሕዶተ ፡ እሳት ፡ ያጤይቅ ፡ ከመ ፡ ኢጠፍአ ፡ ህላዌ ፡ ትስብእት ፡ ወአካለ ፡ ትስብእት ፡ በተዋሕዶተ ፡ መለኮት ፡ ወኢጠፊእቱ ፡ ለእሳት ፡ በተዋሕዶተ ፡ ዕፅ ፡ ልምልምት ፡ ያጤይቅ ፡ ከመ ፡ ኢጠፍአ ፡ ህላዌ ፡ መለኮት ፡ ወአካለ ፡ መለኮት ፡ በተዋሕዶተ ፡ ትስብእት ። ----ዝንቱ ፡ ምሳሌ ፡ አስተጻደለ ፡ ራዕዮ ፡ ለፍና ፡ ትስብእት ።

ሙሴ ፡ በኮሬብ ፡ ያየው ፡ የእሳትና ፡ የቁጥቋጠ ፡ መወሐድ ፡ የአምላክነትንና ፡ የሰውነትን ፡ መዋሐድ ፡ ያስረዳል ። እሳት ፡ የመለ ኮት ፡ ምሳሌ ፡ ነው ፤ ቁጥቋጠውም ፡ የትስብእት ፡ ምሳሌ ፡ ነው ። እሳት ፡ የተዋሐደው ፡ የቁጥቋጡው ፡ ልምላሜ ፡ አለመጠውለጉ ፡ የሰ

ውነት ፡ ህላዌና ፡ አካል ፡ መለኮትን ፡ በመዋሐድ ፡ አለመጥፋቱን ፡ ያስረዳል ። የቁጥቋጦው ፡ ልምላሜ ፡ የተዋሐደው ፡ እሳትም ፡ አለመጥፋቱ ፡ የመለኮት ፡ ህላዌና ፡ አካል ፡ በሰውነት ፡ መዋሐድ ፡ አለመጥፋቱን ፡ ያስረዳልና ፤ ይህ ፡ ምሳሌ ፡ የመዋሐድ ፡ ስልት ፡ ራዕይን ፡ አብራርቶአል ። ”ብሎ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፤ በዚህ ፡ ምሳሌ ፡ መጠን ፡ ቃል ፡ ራሱ ፡ ሳይጠፋና ፡ ሳይለወጥ ፡ የሰውን ፡ አካል ፡ የራሱን ፡ አካል ፡ አደረገ ። ሰውነትም ፡ ራሱ ፡ ሳይጠፋና ፡ ሳይለወጥ ፡ የአምላክነትን ፡ ህላዌ ፡ ተገነዘበ ። ስንል ፤ ያለመደባለቅና ፡ ያለመለወጥ ፡ መዋሐዱን ፡ በመግለጽ ፡ ስለእኛ ፡ ሲል ፡ በእውነት ፡ የሆነውን ፡ የክርስቶስን፡ ሥቃይና ፡ ሞት ፡ ምትሐት ፡ ለማድረግ፡ የተነሣውን ፡ የአውጣኬን ፡ ዐመፃ ፡ ከእኛ ፡ እናስወግዳለን ።

፫ኛ ፡ ከዚህም ፡ ጋር ፡ በእግዚአብሔር ፡ የፍቅር ፡ ስጦታ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ለሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ቤዛ ፡ ምትክ ፡ ሆኖ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ የተቀበለውን ፡ የአሪት ፡ መርገምና ፡ የእግዚአብሔር ፡ የፍርዱ ፡ መዓት ፡ በሞቱ ፡ የሆነውን ፡ የማዳን ፡ ኃይል ፡ ሁሉ ፡ ጥቅም ፡ እንደማይሰጥ ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ ቈጥረውት ፡ በራሳቸው ፡ ተግባር ፡ ለመጽደቅ ፡ የሚጣጣሩት ፡ ሁሉ ፡ “በመዋሐድ ፡ ጊዜ ፡ ሰውነቱ ፡ ወደ ፡ አምላክነቱ ፡ ስለ ፡ ፈለሰ ፡ የክርስቶስ ፡ ሰውነት ፡ ልዩ፡ ነበረ ።” የምትለውን ፡ የመንክዮንን ፡ ጥርጥር፡ ደግሞ ፡-“ገላው፡ አርያማዊ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የሰው ፡ ገላ ፡ አልነበረምና ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ሥቃያት ፡ በሰውነቱ ፡ አልተቀበለም ።” የምትለውን ፡ ግናስቲካዊት ፡ ስሕተት ፡ የሚከተሉ ፡ ናቸው ። ስለዚህም ፥ “የክርስቶስ ፡ መራቡ ፡ መጠማቱ ፡ መድከሙ ፡ መከራንም፡ መቀበሉ ፡ በመስቀል ፡ ላይም ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ መሆኑ ፡ ለቤዛነት ፡ ሳይሆን ፡ ለአርአያነት ፡ ብቻ ፡ አድርጎልናልና ፡ እኛም ፡ እንደ ፡ እርሱ ፡ መሆን ፡ ይገባናል ።” እያሉ ፡ በተዋሕዶ ፡ ሃይማኖት ፡ ምሥጢር ፡ (ይገዳደራሉ ፡) ያሾፋሉ ።

እኛም ፡-“እግዚአብሔር ፡ አዲስ ፡ እንወለድ ፡ ዘንድ ፡ በእኛ ፡ ላይ ፡ በሚያደርገው ፡ አምላካዊ ፡ መለወጥና ፡ በቅዱስ ፡ አካሄዱ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መልካም ፡ ምሳሌያችንና ፡ መሪያችን ፡ ነው ።” በማለት ፡ እንጸናለን ። ሆኖም ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ተቀድሞ ፡ የሚገኝ ፡ ለአዲስ ፡ ልደትና ፡ ለክርስቲያናዊ ፡ አካሄድ ፡ በር ፡ ከፋች ፡





የሚሆን፡ ከተፈረደው፡ ኵነኔ፡ መዳንና፡የኃጢአትን፡ ይቅርታ፡ማግኘት ፡ በመሆኑ፡ አስቀድመን፡ ይህን፡ እንገነዘብ፡ ዘንድ፡ ጌታችን፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ ፡ ከኃጢአት ፡ በቀር ፡ በፍጹም ፡ ተዋሕዶ ፡ በተገነዘበው ፡ ሰውነቱ ፡ በእውነት ፡ ሥቃይ ፡ እየተሰማው ፡ በመሰቀሉና ፡ እሙን ፡ በሆነው ፡ ሞቱ ፡ ቤዛችንና ፡ ተለዋጫችን ፡ ፈንታ ፡ የሆነልን ፡ ዋሳችን ፡ ምትካችንም ፡ ነው ። ያለዚያማ ፡ እግዚአብሔር ፡ በቅን ፡ ፍርዱ ፡ ሊያጸድቀን ፡ ሲሻ ፤ በቅዱስ ፡ ሕጉ ፡ የፈለገብንን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ተሳክቶ ፡ ሊሆንለት ፡ ተሟልቶም ፡ ሊፈጸምለት ፡ ባልተቻለም ፡ ነበር ። (የሐዋ ፡ ሥራ ፡ ፲፫ ፡ ፴፰ ፡ ፴፱ ። ሮሜ ፡ ፭ ፡ ፲፮-፲፰ ። ም ፡ ፰ ፡ ፱-፬ ። ፩ኛ ፡ ቆሮ ፡ ፮ ፡ ፲፬ ፡ ፲፮ ፡ ፲፱-፳፩ ። ገላ ፡ ፪ ፡ ፲፮-፳፩ ። ም ፡ ፫ ፡ ፫-፲፫ ። ሮሜ ፡ ፲ ፡ ፫ ፡ ፬ ።) እያልን ፡ የመንክዮንና ፡ የግናስቲኮች ፡ ስሕተት ፡ እስከዚህ ፡ ውድቀት ፡ ላደረሳቸው ፡ ከማስረዳታችን፡ በላይ ፡ ፍልሰተ ፡ ህላዌን ፡ በማስተማር ፡ ላሳሳቱዋቸው ፡ አስተማሪዎቻቸው ፡ ደግሞ ፡ ሲወሐድ ፡ ሰውነቱ ፡ ወደ ፡ አምላክነቱ ፡ የማይፈልስ ፡ ነው ፤ በማለት ፡ እንቃወማቸዋለን ። ይኸውም ፡ “ኢያፈልሶ ፡ ለህላዌ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡ ህላዌሁ ፡ ለመለኮት ፡ ወኢተኃየሎ፡ ሶበ፡ ተዋሐደ፡ ምስሌሁ ፡ ወኢይትረከብ ፡ በዘኢኮነ፡ ሎቱ ። ወባሕቱ፡ ፍጹም ፡ ውእቱ ፡ በዘዚአሁ፡ወዓዲ ፡ ፍጹም ፡ ውእቱ ፡ በዘነሥአ ፡ እንበለ ፡ ፍልጠት ፡ ወቱስሕት ።”

ትርጓሜ፡ የመለኮት፡ ህላዌ፡ የሰውነትን፡ ህላዌ ፡ አያፈልሰውም ፤ በተዋሐደበት ፡ ጊዜም ፡ አልተደፋፈረውም ፤ ለራሱ ፡ ባልሆነውም ፡ አይገኝም ። ነገር ፡ ግን ፡ በራሱ ፡ ፍጹም ፡ ነው ። ደግሞ፡ ባለመለየትና፡ ባለመደባለቅ ፡ በተገነዘበው ፡ ፍጹም ፡ ነው ። ሲል ፡ ማሪ ፡ ኤፍሬም ፡ በተናገረው ፡ መሠረት ፡ ፍልሰተ ፡ ህላዌ ፡ የሌለበትን ፡ ተዋሕዶ ፡ ሃይማኖታችንን ፡ እናጸናለን ። (ቆለሳ ፡ ፪ ፡ ፱ ፡ ፲ ።)

፬ኛ ፡ “ቃል ፡ ሰው ፡ የሆነው ፡ እስከ ፡ መሰቀሉ ፡ ድረስ ፡ ነው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ሥጋውን ፡ በመቃብር ፡ ተወ ፤ ወይም ፡ እግዚአብሔር ፡ በአንድ ፡ ስፍራ ፡ ሠወረው ፤” እያለች ፡ በክርስቶስ ፡ ተዋሕዶ ፡ መሻር ፡ እንዳለ ፡ አድርጋ ፡ ከተነሣችው ፡ የዎች ፡ ታወር ፡ ማኅበር ፡ ትምህርት ፡ ፈጽመን ፡ ስንለይ ፤ “ዘለዓለማዊ ፡ ቃል ፡ የተገነዘበው ፡ ሥጋ ፡ ለዘለዓለሙ ፡ በመዋሐዱ ፡ የማይሻር ፡ ስለ ፡ ሆነ ፤ ከሙታን ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ በሥጋና ፡ በዐጥንት ፡ በጠቅላላውም ፡ ለሰው ፡ የተገባ

ውን ፡ ምሉዕና ፡ ፍጹም ፡ አካላዊ ፡ ጠባይውን ፡ ይዞ ፡ በመነሣቱ ፡ የተቸ ነከረውን ፡ ገላውን ፡ አሳይቶአል ። ይህም ፡ ከዳዊት ፡ ዘር ፡ የመጣው ፡ ሥጋ ፡ በኃይል ፡ ከሙታን ፡ በመነሣቱ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ መሆኑን ፡ ከገለጸ ፡ በኋላ ፡ ለአባላቶቹ ፡ ራስ ፡ ሆኖ፡ በመናብርትና ፡ በአጋዕዝት ፡ በመላእክትም ፡ ላይ ፡ በኃይል ፡ ቀኝ ፡ በመቀመጡ ፡ ሥጋው ፡ የምትሆን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አሁን ፡ ለምትኖርበት ፡ ሕይወትና ፡ ኋላ ፡ ለምታገኘው ፡ ክብር፡ መያገሮዋ፡ ነው ።'' (ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፲፬ ፡ ፲፰ ። ም ፡ ፫ ፡ ፴፮ ፡ ፴፯ ። ም ፡ ፲ ፡ ፲፯ ፡ ፲፰ ። ሉቃ ፡ ፳፬ ፡ ፴፮-፵ ። ዮሐ ፡ ፳ ፡ ፲፱ ፡ ፳-፳፯ ። የሐዋ ፡ ሥ ፡ ፩ ፡ ፪ ፡ ፫ ፡ ፱ ። ሉቃ ፡ ፳፬ ፡ ፶፩ ። ዕብ ፡ ፱ ፡ ፳፰ ። ም ፡ ፰ ፡ ፩፡ ም፡ ፲ ፡ ፲፱ ፡ ፳። ሮሜ፡ ፩፡ ፫፡ ፬። ቆለሳ፡ ፩፡ ፲፰፡ ኤፌ ፡ ፩ ፡ ፳-፳፫ ። ም ፡ ፫ ፡ ፮ ። ም ፡ ፬ ፡ ፲፭ ፡ ፲፮ ። ፊልጵ ፡ ፪ ፡ ፮-፲፩ ። ፊል ፡ ፫ ፡ ፳-፳፩ ።) አፈወርቅም ፡- "ለዘውእቱ ፡ እምኔነ ፡ አንበሮ ፡ ዲበ ፡ ዝክቱ ፡ መንበር ፡ ወለነሂ ፡ ዓዲ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሰሐበነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኀቤሁ ፡ በከዊኖቱ ፡ ርእሰ ፡ ዚአነ ፡ እስመ ፡ ውስተ ፡ መካን ፡ ኀበ ፡ ሀሎ ፡ ርእስ ፡ ህየ ፡ ይሄሉ ፡ ሥጋ ።" ሲል ፡ ያጸደቀው ፡ ነው ፡ እያልን ፡ መሻር ፡ የሌለበትን ፡ ተዋሕዶ ፡ እናምናለን ።

፭ኛ ፡ "ቃል ፡ የጥንት ፡ አንዋንዋሩን ፡ ትቶ ፡ ጥንት ፡ ሆኖት ፡ የማያውቅ ፡ ሆነ ፤" የሚለውን ፡ አነጋገር ፡ የቃል ፡ ባሕርይ ፡ ወደ ፡ ሥጋ ፡ ተመለሰ ፡ ወይም ፡ ተለወጠ ፡ እንደሚሉ ፡ እንደ ፡ ሐራጥቃ ፡ መናፍቃን ፡ አጣምመን፡ አንተረጕመውም ። አስቀድመን ፡ "አምላካዊ ፡ ባሕርይ ፡ በማናቸውም ፡ ነገር ፡ አይለወጥም ፤" (ሚልክ ፡ ፫ ፡ ፮ ። ዕብ ፡ ፩ ፡ ፲፩ ።) ብለን፡ እየተቃወምናቸው ፤ "ቃል፡ ቀድሞ፡ ያልሆነው፡ ሆነ ፤" ስንል ፡ የቃልን ፡ ብቸኝነት ፡ በማያሳይ ፡ ትርጉም ፡ "ቃል፡ ከትሥጉት ፡ በኋላ ፡ እንደገና ፡ ተለይቶ ፡ ያለ ፡ ሥጋ ፡ ሊኖር ፡እስከማይችል ድረስ፡ በአምላክ ፡ ሥምረትና ፡ ፈቃድ ፡ ተዋሐደ ፤" ብለን ፡ በማመን ፡ ከሐራጥቃ ፡ ዳሕፅ ፡ እንሸሻለን ።

፮ኛ ፡ "መዋሐዱ ፡ ከሥጋ ፡ ብቻ ፡ ነበረ ፡ እንጅ ፡ ከነፍስ ፡ ወይም ፡ ከመንፈስ ፡ ጋር ፡ አልነበረም ፤ ነፍስ ፡ ወይም ፡ መንፈስ ፡ ስላልነበረው ፡ በነፍሱ ፡ ወይም ፡ በመንፈሱ ፡ ፈንታ ፡ መለኮቱ ፡ ገብቶ ፡ ተዋሐደው ፤" የሚለውን ፡ የአቡሊናሪስን ፡ ትምህርት ፡ የምንነቅፍበት ፡ ምክንያት ፡ መድኃኒታችን ፡ በሰው ፡ ሁለንተና ፡ (በሥጋ ፡ በነፍስ ፡





በመንፈስ) ፡ ፈጽሞ ፡ ባይወሐድ፡ የሰውን፡ ሙሉ ፡ ጠባይዕ ፡ ባላዳነም፡ ነበር ። የሰው ፡ ሙሉ ፡ ጠባይዕንም ፡ ላያድን ፡ ለምን ፡ ሰው ፡ ሆነ ! ሰው ፡ ለመሆንም ፡ ከተዋሐደ ፡ የሰውነትን፡ ግማሽ፡ ወዴት ፡ አስቀረ ? ለሚል ፡ ጥያቄያችን ፡ አጥጋቢ ፡ መልስ ፡ የማይገኝለት ፡ ነው ። "ስለ ሆነ ፡ ከኃጢአት ፡ በቀር ፡ ሰው ፡ ሲሆን ፡ በነፍሱና ፡ በመንፈሱ ፡ የሰውን ፡ ልጆች ፡ ኀዘን ፡ ጥቃት፡ ጉስቍልና ፡ ውርደት ፡ ይሰማው ፡ ነበረና ፡ ሕማማት ፡ በተቀበለበትና ፡ በተፈተነበት ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ የታመነ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ሆኖ ፡ በፀዋትወ ፡ መከራ ፡ የሚፈተኑትን ፡ ለመርዳት ፡ እንደቻለ ፡ (ዕብ ፡ ፪ ፡ ፲፯፡ ፲፰ ። ም ፡ ፬ ፡ ፲፬-፲፮ ፡ ም፭፡ ፯፡ ፰ ። ም ፡ ፲፪ ፡ ፪ ፡ ፫ ።) እያስረዳን ፡ የሰውን ፡ ሙሉ ፡ ጠባይዕ ፡ ወስዶ ፡ ፍጹም ፡ አምላክ ፡ ጥዩቅ ፡ ሰውነት ፡ ሆኖአል ፤" ስንል ፡ እናምናለን ።

፯ኛ ፡ "ከመዋሐድ ፡ በኋላ ፡ በክርስቶስ ፡ ሁለት ፡ ህላዌና ፡ ሁለት ፡ ገጽ ፡ አለ ፤" ከሚል ፡ ንስጥሮሳዊና ፡ ተከታዮቹ ፡ ትምህርት ፡ የምንለየው ፡ በሚከተለው ፡ ምሥጢራዊ ፡ ሐተታ ፡ ነው ።

ከመዋሐድ ፡ በኋላ ፡ በአንድ ፡ ክርስቶስ ፡ ሁለት ፡ ህላዌ ፡ አለ ፡ ማለት ፡ የአምላክነትንና ፡ የሰውነትን ፡ ህላዌ ፡ ፍርቅ ፡ በማድረግ ፡ በተዋህዶም ፡ ቡዓዴን ፡ በማምጣት ፡ "ለአንዱ ፡ የሚሰገድለት ፡ ለሌላውም ፡ የማይሰገድለት ፡ ሁለት ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ፡" ማለት ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ አቡሊድስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡—

"አልቦ ፡ ለሥጋሁ ፡ ህላዌ ፡ ፍሉጥ ፡ እመለኮት ፡ ኀበ ፡ ገጸ ፡ ፍና ፡ ወኢለመለኮት ፡ አልቦቱ ፡ ህላዌ ፡ ፍሉጥ ፡ እምትስብእት ፡ ኀበ ፡ ገጸ ፡ ፍና ፤ አላ ፡ ከመ ፡ ብእሲ ፡ ዘአሐዱ ፡ ህላዌሁ ፡ ከማሁ ፡ ውእቱ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘኮነ ፡ በአርአያ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ።

ትርጓሜ፡ የክርስቶስ ፡ ሥጋ ፡ በባዕድነት ፡ ረገድ ፡ ከመለኮቱ ፡ የተለየ ፡ አቅዋም ፡ የለውም ። መለኮቱም ፡ በባዕድነት ፡ ረገድ ፡ ከሥጋው ፡ የተለየ ፡ አቅዋም ፡ የለውም ። ነገር ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አቅዋሙ ፡ አንድ ፡ እንደሚሆን ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ልጆች ፡ የሆነ ፡ ክርስቶስም፡ እንዲሁ ፡ ነው ፤" ሲል ፡ እንደተናገረ ፤ እኛም ፡ በዚሁ ፡ መጠን፡ በብዙ፡ ሊቃውንት፡ የታመነውን፡ ምሳሌና፡ ማስረጃ፡ እንሰጣለን።

ይኸውም ፡- በነፍስና ፡ በሥጋ ፡ የቆመ ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ እንጅ ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ ለመሆን ፡ እንደማይቻል ፡ ወይም ፡ ሁለት ፡

ሰዎች ፡ እንደማይባል ፡ ሁሉ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ከሆነ ፡ በኋላ ፡ በዚህ ፡ መዋሐድ ፡ ሳይከፈል ፡ አንድ ፡ ክርስቶስ ፡ በመሆኑና ፡ ለዚህም ፡ ለአንዱ ፡ ክርስቶስ ፡ መከፈልን ፡ የማያሳይ ፡ አምልኮትና ፡ ስጊድ ፡ በመስጠቱ ፡ የህላዌውን ፡ መንትያ ፡ ከማየት ፡ ተከልለናልና ፡ በአንድ ፡ ክርስቶስ ፡ አንድ ፡ ህላዌነትን ፡ እንጅ ፡ ሁለት ፡ ህላዌ ፡ አለ ፡ ብለን ፡ ከማመን ፡ እንጠበቃለን። (ፊልጵ ፡ ፪ ፡ ፭-፲፩። ዮሐ ፡ ፲፯ ፡ ፬ ፡ ፭ ።)

በጠቅላላውም ፡- ኢየሱስ፡ ክርስቶስ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወልደ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡ ዘትማልም ፡ ወዮም ፡ ወከመ ፡ ውእቱ ፡ እስከ ፡ ለዓለም ፡ አሐዱ ፡ ህላዌ ፡ ሎቱ ፡ ንስግድ ፡ ወንሰብሕ ፡ ስንል ፤ ተዋሕዶ ፡ እምነታችንን ፡ እናጸናለን ።



፲፪ኛ ፡ አንቀጽ ።

## ስለ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ።

በምሕረት፡ ባለጸጋ፡ የሚሆን፡ እግዚአብሔር ፡ ፡ ኤፌ ፡ ፩ ፡ ፬ ።
የወደቀውን ፡ ሰው ፡ ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ በነበረ ፡
በጥንታዊ ፡ ምክሩ ፡ እንዲያድንና ፡ ከራሱም ፡ ጋር ፡ ኤር ፡ ፳፱ ፡ ፲፩ ።
እንዲያስታርቅ ፡ በዚህም ፡ ለሚያምኑ ፡ ሁሉ ፡ አን ፡ ሆሴ ፡ ፪ ፡ ፳፫ ።
ዳች ፡ እንከን ፡ የሌለው ፡ ፍጹምና ፡ ምሉዕ ፡ የሆነ ፡ ፡ ፩፡ ዮሐ፡ ፭፡ ፲-፲፫።
ጽድቅን ፡ ቅድስናን ፡ ክብርንም ፡ ሁሉ ፡ ሰጥቶ ፡
እንዲያወርስ ፡ በአንዱ ፡ ልጁ ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ዕብ ፡ ፪ ፡ ፲ ። ዘፍ ፡ ፫ ፡ ፲፭ ።
ክርስቶስ ፡ መካከለኛነትና ፡ ሊቀ ፡ ካህንነት ፡ የቆመ ፡ ፡ ዕብ ፡ ፱ ፡ ፲፭ ።
ሥርዓት ፡ እንዳኖረና ፡ እንደ ፡ መደበ ፡ የጸጋ ፡ ቃል ፡
ኪዳንም ፡ እንደ ፡ ገባ ፤ ፤ ኢሳ ፡ ፶፭ ፡ ፫-፭ ።

የቃል፡ኪዳኑ፡ጌታም፡(ባለቤት፡)ደግሞ፡በጊዜው፡ ፡ ሚል ፡ ፫ ፡ ፩ ።
ከአብርሃምና ፡ ከዳዊት ፡ ዘር፡ በዚህ፡ ዓለም፡ ተገኝቶ ፡ ፡ ማቴ ፡ ፩ ፡ ፩ ።
የጽድቅና ፡ የሰላም ፡ ንጉሥ ፡ የታመነ ፡ ይቅር፡ ባይ ፡ ፡ ኤር፡ ፳፫፡ ፭ ፡ ፮ ።
ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ሆኖ፡ ከጥንት፡ የተመደበውን ፡ ምድ
ብና ፡ ሥርዓት ፡ በዘለዓለም ፡ ኪዳን ፡ ደም ፡ በመ ፡ ፩ጴጥ፡ ፩ ፡ ፲፱፡ ፳፡
ፈጸሙ ፡ ምክንያት ፡ ያለፀፀትና ፡ ያለኀዘን ፡ በራሱና፡ ፡ ዕብ ፡ ፲፫ ፡ ፳ ።
በሰው ፡ መካከል ፡ ያቆመው ፡ መሆኑን ፡ ሊለወጥ ፡ በ ፡ ፩ ፡ ጢሞ፡ ፪፡ ፭ ።
ማይቻል ፡ ቃለ ፡ መሐላ ፡ እንዳጸናልን ፤ ፤ ዕብ፡ ፯፡ ፳፩፡ ፳፪ ።

ከዚያ ፡ በኋላም ፡ ሌላ፡ ቃል፡ ኪዳን፡ እንደማያ ፡ ገላ ፡ ፫ ፡ ፲፮-፲፯ ።
ስፈልግና ፤ እግዚአብሔርም ፡ የክብሩ ፡ ብርሃን ፡ የአ ፤ ኢሳ፡ ፵፰፡ ፲፩-፲፰፡
ካሉ ፡ ምሳሌ ፡ በሚሆን ፡ በአንዲያ ፡ ልጁ ፡ ያልተፈ ቈላ፡ ፩፡ ፲፭-፳፪ ።
ጸመለት ፡ ነገር ፡ ኖሮ ! በሌላ ፡ ይፈጸምልኛል ፡ ብሎ ፡ ! ዕብ ፡ ፩ ፡ ፩-፫ ።
ቃል፡ ኪዳኑን፡ ለሌላ፡ ሰው፡ እንዳላስቀረ ፤ በኢየሱስ ፡ ፤ዮሐ፡ሥ ፫፡ ፲፰-፳፯።
ክርስቶስ ፡ የተፈጸመ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ እግዚአብሔር ፡ ኤር፡ ፴፩፡ ፴፩-፴፬።
ለፈለገው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በቂ ፡ በመሆኑ ፡ ሊለወጥና ፡ ኢሳ ፡ ፵፪ ፡ ፩-፰ ።
ሊሻር ፡ እንደማይቻል ፤ እናምናለን ። ። ኤፌ ፡ ፩፡ ፫-፲፪ ።

## ቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡-

ጥቅስ ፡ "እግዚእነ ፡ ወመድኃኒነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ንጉሠ ፡ ጽድቅ ፡ ዘበአማን ፡ ውእቱ ፡ ንጉሠ ፡ ጽድቅ ፡ ወንጉሠ ፡ ሰላም ፡ ወዝንቱ ፡ ሰላም ፡ ኮነ ፡ ለነ ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ አቡሁ ። ወውእቱ ፡ አርአየነ ፡ ፍኖተ ፡ ጽድቅ ፡ በወንጌል ፡ ወኮነ ፡ ለነ ፡ ሰላመ ፡ እስመ ፡ ኮነነ ፡ በአተ ፡ ኀበ ፡ አብ ። ወነሰተ፡ ጥቅመ ፡ ዘማዕከለ ፡ ሐፁር ፡ ወተኀድገት ፡ ትእዛዘ ፡ ሕገ ፡ አሪት ፡ ወተሐደስነ ፡ ክልኤቱ ፡ ሕዝብ ፡ በአሐዱ ፡ ብእሲ ፡ ሐዲስ ፡ ዘማዕከሌነ ፡ ክርስቶስ ፤ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ሰላመ ፡ ዚአነ ፡ ወካህንነ ፡ ዐቢይ ፡ ወንጹሕ ፡ ወጻድቅ ፡ ወየዋህ ፡ ወአልቦ ፡ ነውር ፡ ወፍሉጥ ፡ እምብዙኃን ፡ ወልዑል ፡ እምሰማያት ።

ትርጓሜ፡ እውነተኛ ፡ የጽድቅ ፡ ንጉሥ ፡ የሆነ ፡ ጌታችን ፡ መድኃኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የጽድቅና ፡ የሰላም ፡ ንጉሥ ፡ ነው ። ይህም ፡ ሰላም ፡ ከአባቱ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ሆነልን ፡ (ተደረገልን ፡) እርሱም ፡ የጽድቅን ፡ መንገድ ፡ በወንጌል ፡ ገለጠልን ፡ ወደ ፡ አብ ፡ መግቢያ ፡ ሆኖልናልና ፤ በመካከል ፡ የቆመውን ፡ የአጥር ፡ ካብ ፡ አፈረሰ ፤ የኦሪት ፡ ትእዛዝም ፡ ተተወች ፡ መካከለኛችን ፡ በሚሆን ፡ በክርስቶስ ፡ በአንዱ ፡ አዲስ ፡ ሰውነት ፡ ሁለቱ ፡ ሕዝብ ፡ ታደስን ። እርሱ ፡ ሰላማችን ፡ ነውና ፡ ትልቁ ፡ ካህናችንም ፡ እርሱም ፡ ንጹሕና ፡ ጻድቅ ፡ የዋህ ፡ ነውር ፡ የሌለበትና ፡ ከብዙዎች ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ በሰማያትም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ የተቀመጠ ፡ ነው ፤" አለ ።

ጥቅስ ፡ እንዲሁም ፡ በቅዳሴ ፡ እግዚእ ፡- "ወበምክረ ፡ ዚአከ ፡ ወልድከ ፡ ኢየሱስ ፡ ዋህድ ፡ ዘተሰቅለ ፡ በእንተ ፡ መድኃኒትነ ፡ ዘበቃለ ፡ ኪዳንከ ፡ ቦቱ ፡ ገበርከ ፡ ሠሚረከ ፡ ቦቱ ።

ትርጓሜ፡ ለደኅንነታችን ፡ በተሰቀለው ፡ በአንዲያ ፡ ልጅህ ፡ በኢየሱስ ፡ በባሕርይህ ፡ ምክር ፡ ተሰኝተህበት ፡ ቃል ፡ ኪዳንህን ፡ ሁሉ ፡ በእርሱ ፡ አድርገሃል ፤" ይላል ።

ጥቅስ ፡ ዳግም ፡ በእልመስጠአግያ ፡- "ከመ ፡ ታእምሩ ፡ ፈቃዶ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወትሌብዉ ፡ ምሥጢረ፡ መድኃኒትክሙ፡ አ፡ አንትሙ ፡ እደው ፡ ወአንስት ፡ ቅዱሳት ፡ እለ ፡ ሀሎክሙ ፡ ውስተ ፡ ተመክሆ ፡ በክርስቶስ ፤ ወኩኑ ፡ አሐደ ፡ ምስለ ፡ ብእሲ ፡ ዘውስጥ ፡ አንትሙኬ ፡ እለ ፡ አጽንዓ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኪዳኖ ፡ ምስሌክሙ ፡ ወሜመ ፡ መንፈሶ ፡ ውስቴትክሙ ።





ትርጓሜ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ፈቃድ ፡ ታውቁ ፡ ዘንድና ፡ የደኅንነታችሁን ፡ ምሥጢር ፡ ታስተውሉ ፡ ዘንድ ፡ በክርስቶስ ፡ ትምክህት ፡ ያላችሁ ፡ እናንተ ፡ ወንዶችና ፡ ቅዱሳት ፡ ሴቶች ፡ ሆይ ፡ ከውስጣዊ ፡ ሰውነት ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ሁኑ ። እግዚአብሔር ፡ ኪዳኑን ፡ ከናንተ፡ ጋር ፡ ያጸና ፡ መንፈሱንም ፡ በውስጣችሁ ፡ ያሳደረ ፡ እናንተ ፡ ሆይ ፡ እናንተን ፡ ነው ።" ተብሎ ፡ ተጽፎአል ። ኢሳ ፡ ፵፱ ፡ ፳-፲ ።

ስለዚህም ፡ ሁሉ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የተፈጸመውን ፡ ቃል፡ ኪዳን ፡ እንደ ፡ ገና ፡ እያደሱ ፡ በእኛ ፡ ነው ፤ ወይም ፡ ለእኛ ፡ ነው ፤ እያሉ ፡ በየጊዜው ፡ የሚነሡትን ፡ ሐሳውያን ፡ መሢሕን ፡ ከእነርሱ ፡ መካከልም ፡ ብዙን ፡ ሕዝብ ፡ በማሳት ፡ የታወቁት ፡ እነማኒን ፡ እነመሐመድን ፡ አንከተልም ። እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የሆነው ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ፍጹም ፡ እንዳይደለና ፡ ቅርታ ፡ እንዳለው ፡ እያስመሰሉ ፡ ስለ ፡ ሰው ፡ ደኅንነት ፡ ስለ ፡ መታረቅ ፡ ስለ ፡ ኃጢአትም ፡ ሥርየት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አለ ፡ ብለው ፡ የሚያስተምሩትን ፡ ለክርስቶስ ፡ ሆነን ፡ እንቃወማቸዋለን ። ኢሳ ፡ ፴ ፡ ፩ ።

## ስለ፡ ንስሓ ።

ንስሓ ፡ በሠሩት ፡ ኃጢአት ፡ መፀፀት ፡ ፡ማቴ፡፳፯፡፫።
ወይም ፡ ማዘንና ፡ ማልቀስ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በእው ፡ሉቃ፡፲፰፡፳፫።
ነት ፡ ኃጢአትን ፡ ጠልቶ ፡ ማድረጉንም ፡ መተውና ፡ ፡ሕዝቅ፡፲፰፡፴-፴፪።
ወደ ፡ እግዚአብሐር ፡ መመለስን ፡ አሮጌ ፡ ጽድቅንና ፡ ፡ኤር፡፫፡፳፪።
ልማድን ፡ ጥሎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሥርዓት ፡ በመ
ታዘዝ ፡ ዝቅ ፡ ዝቅ ፡ ማለትን ፡ በእርሱ ፡ ለመኖርም ፡ ፡ዳን፡፱፡፩-፲፰።
እውነተኛንና ፡ ቊርጠኛን ፡ ፍላጎት ፡ ጠቅልሎ ፡ ፡ሉቃ፡፲፭፡፲፯-፳።
ይዞ ፡ ለመዳን ፡ የሚያደርስና ፡ እንደ ፡ አገባቡም ፡ ፡መዝ፡፶፩፡፲-፲፪።
የሚዳንበትን ፡ ሃይማኖት ፡ የሚያስከትል ፡ ነው ። ።፪፡ ቆሮ፡ ፯፡ ፱፡ ፲።

በዚህም ፡ የቅደም ፡ ተከተሉን ፡ እውነተኛ ፡
ምሥጢር ፡ ስንገልጽ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ለኃጢአተ
ኛው ፡ ኃጢአቱን ፡ በሚያስታውቅበት ፡ ጊዜ ፡ በደለ ፡ዮሐ፡፲፮፡፯-፱።
ኛው ፡ በሠራው ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ምንም ፡ እንዳ
ልተጠቀመበት ፡ ይልቁንም ፡ ዘለዓለማዊ ፡ ቅጣት ፡
እንደሚኖርበትና ፡ የዚሁም ፡ ቅጣት ፡ መከራ ፡ እንዲ
መጣበት ፡ ያደረገ ፡ ደስ ፡ ሲለው ፡ የሠራው ፡ ኃጢ
አቱ ፡ እንደሆነ ፡ ተረድቶ ፡ ጥፋቱንና ፡ ርኵሰቱን ፡
ይጠላል ። ስለ ፡ ራሱ ፡ ብቻም ፡ ሳይሆን፡ የወደደውን ፡ ።ሕዝ፡፴፮፡፴፩።
አምላኩን ፡ ስለ ፡ አሳዘነበት ፡ ስለ ፡ ክፉ ፡ ሥራው ፡
አዝኖ ፡ ያለቅሳል ፤ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ፤ሉቃ፡፯፡፴፰፡
ተመልሶ ፡ በፍጹም ፡ ኀሳቡ፡ ለእግዚአብሔር፡ ሕግ፡ ሊ ፡ማር፡፲፬፡፸፪።
ገዛ፡ ይሻል። ዳሩ፡ ግን፡ ለበደለው፡ በደሉና፡ ለሠራው ፡ ።ሉቃ፡፲፱፡፰።
ኃጢአቱ ፡ ዋጋ ፡ ያልተከፈለ ፡ ዕዳ ፡ እንዳለበት ፡ ፡ኤር፡፪፡፳፪።
ስለሚሰማው ፡ ንስሓው ፡ ደኅንነትን ፡ አያረጋግጥ ፡ማቴ፡፲፰፡፳፫-፳፭።
ለትም ። ቢሆንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ እየ ።ዕብ፡፱፡፳፪፡
ሰማ ፡ መታዘዝን ፡ ከቀጠለ ፡ ይህን ፡ ተራምዶ ፡ በኢ

የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሞት ፡ የተከፈለ ፡ የኃጢአት ፡ ዋጋ ፡
ለኃጢአቱ ፡ ይቅርታ ፡ በቤዛነት ፡ ዋስትና ፡ ያለፈ ማቴ ፣ ፳፮ ፣ ፳፯ ፣ ፳፰ ።
ለት ፡ የእርሱ ፡ ዕዳና ፡ ካሣ ፡ እንደሆነ ፡ ሲገለጽለት ፡ ቈላ ፣ ፪ ፣ ፲፫ ።
ይህን ፡ ተገንዝቦ ፡ በአዳኝ ፡ ሃይማኖት ፡ ደኅንነትን ፡ የሐዋ ፣ ፫ ፣ ፲፱ ፣ ፳ ።
ይጨብጣል ። ።የሐዋ ፣ ፪ ፣ ፴፰ ፣ ፴፱ ።

ስለዚህም ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ አዳኝ ፡ ሃይማኖት
ንና ፡ ደኅንነትን ፡ ሊያገኝ ፡ የሚችለው ፡ በንስሓ ፡
በኩል ፡ አልፎ ፡ እንጅ ፡ በንስሓ ፡ ብቻ ፡ ቆሞ ፡
ቢቀር ፡ አይደለም ። እውነተኛ ፡ ንስሓ ፡ መሆኑንም ፡ ። ማር ፣ ፩ ፣ ፲፭ ።
የሚታወቀው ፡ ራስን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ አዋ
ርዶ ፡ በመናዘዝና ፡ ከተቀያየሙት ፡ ሰውም ፡ በመተ ፣ ፩ ፣ ዮሐ ፣ ፩ ፣ ፰ ፣ ፱ ።
ራረቅ ፡ የንስሓንም ፡ ፍሬ ፡ በማድረግ ፡ ነው ፤ ስንል ፡ ፣ ማቴ ፣ ፫ ፣ ፰ ።
እናምናለን ። ያዕ ፡ ፭ ፡ ፲፮ ። ። የሐዋ ፣ ፳፮ ፣ ፳ ።

ጥቅስ ፣ ዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡- "እስመ ፡ ዘይፈቅድ ፡ ገቢረ ፡ ትሩፋት ፡ ወፍጻሜ ፡ ነሢአታ ፡ ይደልዎ ፡ ቅድመ ፡ ይትገሃሥ ፡ እምግብር ፡ እኩይ ፡ ወይመንን ፡ ብሔረ ፡ ዚአሃ ፡ ወይግድፍ ፡ እሊዓሃ ፡ ወዘድኅሬሃ ፡ ወይምጻእ ፡ መንገለ ፡ ትሩፋት ፤ ወንስሓሰ ፡ ባሕቲታ ፡ ኢትክል ፡ አንጽሖቶ ፡ ----እስመ ፡ ንስሓ ፡ ኢትበቍዖ ፡ ለአንጽሖ ፡ አላ ፡ ይትፈቀድ ፡ ጸጋ ፡ ጥምቀት ፡ ይደልዎ ፡ ለዘይፈቅድ ፡ ይጠመቅ ፡ ከመ ፡ ይእመን ፡ አበሳሁ ፡ ቅድመ ፡ ወይጽላእ ፡ ጌጋዮ ፡ ወይፍታሕ ፡ ላዕለ ፡ ነፍሱ ።

ትርጓሜ፡ ትሩፋትንና ፡ የመቀበያዋን ፡ ፍጻሜ ፡ የሚፈልግ ፡ ቢኖር ፡ አስቀድሞ ፡ ከክፉ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ይለይ ፡ ዘንድ ፡ ይገባዋልና ፡ የከፋት ፡ አንዋንዋርን ፡ ይናቅ ፡ እርስዋንና ፡ ተከታይዋንም ፡ ይጣል ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ትሩፋት ፡ ይምጣ ፡ ንስሓ ፡ ግን ፡ ብቻዋን ፡ ማንጻቱን ፡ አትችልም ፤ ---------ንስሓ ፡ ለማንጻት ፡ አትጠቅምምና ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ጸጋ ፡ ጥምቀት ፡ ያስፈልጋል ፡ መጠመቅ ፡ የሚሻም ፡ በደሉን ፡ አምኖ ፡ ይናዘዝ ፡ ዘንድ ፡ ኃጢአቱንም፡ ይጠላና ፡ በራሱም ፡ ይፈርድ ፡ ዘንድ ፡ ይገባዋል ፤ " ብሎአል ።





## ወንጌለ ፡ መንግሥት ።

ከሰማይ ፡ በታች ፡ ባለው ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡
ዘንድ ፡ የተሰበከና ፡ መላእክትም ፡ ማየቱን፡ የሚመኙ፣ ፣ ቈላ ፣ ፩ ፣ ፳፫ ።
ቅዱስ ፡ ወንጌል ፡ የእግዚአብሔር ፡ ኃይል ፡ ሆኖ ፡ የ ፣ ፩ጴጥ ፣ ፩ ፣ ፲፪ ።
ሚያምኑበትን ፡ ሁሉ ፡ ለማዳን ፡ የተሰጠ ፤ የእግዚአ ማቴ ፣ ፲፩ ፣ ፩ ።
ብሔር ፡ ጽድቅ ፡ የሚገለጥበት ፤ ሰውም ፡ ሁሉ ፡ ይህ ሮሜ ፣ ፩ ፣ ፲፮ ፣ ፲፯ ።
ንን ፡ የምሥራች ፡ ሰምቶ ፡ ከጨለማ ፡ ሥልጣን ፡ ወደ፡ ፣ ማር ፣ ፲፮ ፣ ፲፭ ።
እግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ለመግባት ፡ የሚመጣ ፣ የሐዋ ፣ ፳፮ ፣ ፲፰ ።
በት ፤ ብሥራታዊ ፡ አዋጅ፡ ነው ። የልብ ፡ መለወጥ ፡ ። ማር ፣ ፩ ፣ ፲፬ ፣ ፲፭ ።
ሥራም ፡ በእርሱ ፡ ስለሚገኝ ፡ በስሕተት ፡ ፈቃድ ፡ ፣ የሐዋ ፣ ፳ ፣ ፳፩ ።
ጠፍቶ ፡ ከተፈጠረው ፡ ሥጋዊ ፡ አለማወቅ ፡ መንፈ
ሳዊ ፡ ማስተዋል ፡ የሚገኝበት ፤ በዚሁም ፡ የጸጋ ፡ የም ፤ ፩ቆሮ ፣ ፪ ፣ ፮-፲፮ ፣
ሥራች ፡ ልጁን ፡ ሰጥቶ ፡ የታረቀው ፡ ሰማያዊ ፡ አባት፡ ፣ ዮሐ ፣ ፫ ፣ ፲፮ ።
ያጸደቀው ፡ ፈቃር ፡ አምላክ ፡ እንዳለው ፡ የሚያምን ፡ ፩ጴጥ ፣ ፩ ፣ ፳፫-፳፭ ።
ልብ ፡ ከሞት ፡ ወደ ፡ ሕይወት ፡ መሸጋገሩን ፡ የሚያረ ፣ ፪ጢሞ ፣ ፩ ፣ ፱ ፣ ፲ ።
ጋግጥበት ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ባደረገው ፡ ፤ ፩ተሰ ፣ ፩ ፣ ፭ ።
ሥራ ፡ ሁሉ ፡ የጽድቅና ፡ የቅድስና፡ የክብርም፡ መገኛ፡ ፣ ኤፌ ፣ ፫ ፣ ፭ ፣ ፮ ።
ማረጋገጫና ፤ የክርስቲያናዊ ፡ አካሄድ ፡ መምህር ፡ ፣ ፊል ፣ ፩ ፣ ፳፯ ።
የሰላማዊ ፡ ሕይወትም ፡ አስተዳዳሪና ፡ መሪ ፡ ነው ፤ ቲቶ ፣ ፪ ፣ ፲፩-፲፬ ።
ብለን ፡ እናምናለን ። ። ፪ቆሮ ፣ ፬ ፣ ፫-፮ ።

ይህም ፡ አዲስ ፡ ትርጉም ፡ ሳይሆን ፡ ትምህርተ ፡ ኅቡዓት ፡ በተባለው ፡ መጽሐፍ ፡ ስለ ፡ ወንጌል ፡ የተባለውን ፡ ቀጥሎ ፡ በተጠቀሰው ፡ ተመልከት ።

ጥቅስ ፣ "ወትእዛዛተ ፡ ጽድቅ፡ በወንጌል ፡ መጠወ ፤ ዘውእቱ ፡ ጸዋዒ ፡ ዘበመንግሥት ፡ ንሕየው ፡ ተምሂረነ ፤ ወበውእቱ ፡ ወንጌል ፡ ማዕሠረ ፡ ሰይጣን ፡ ተበትከ ፡ ከመ ፡ እሞት ፡ ሕይወተ ፡ ንትካፈል ፡ ወእምነ ፡ ኢያእምሮ ፡ ልቡና ፡ ንንሣእ ።

ትርጓሜ ፡ የጽድቅን ፡ ትእዛዝ ፡ በወንጌል ፡ ሰጠ ፤ ይኸውም ፡ ማለት ፡ እርሱን ፡ ተምረን ፡ ሕያዋን ፡ እንሆን ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ መንግሥቱ ፡ የሚጠራ ፡ ብሥራታዊ፡ አዋጅ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ በዚህም ፡ ወንጌል ፡ የሰይጣን ፡ ማሠሪያ ፡ ሲቆረጥ ፡ እኛ ፡ ከመሞት ፡ ይልቅ ፡ የሕይወት ፡ ተካፋዮች ፡ እንድንሆንና ፡ ካለማወቅም ፡ ማስተዋልን ፡ እንድንገነዘብ ፡ ነው ፡” ይላል ።

እንዲሁም ፡ አሞኔዎስና ፡ አውሳብዮስ ፡ ከተናገሩት ፡ ጠቅሰን ፡ የጻፍነውን ፡ በሚከተለው ፡ ተመልከት ፡-

ጥቅስ ፡ “ወትእምርተ ፡ ዝንቱ ፡ መጽሐፍ ፡ ክቡር ፡ ወንጌል ፡ እስመ ፡ ተሰብከ ፡ ውእቱ ፡ በእንተ ፡ ትስብእተ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዲበ ፡ ዘመድነ ፡ ወኀድረተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ላዕሌነ ፡ ወውስቴትነ ። ዐባይኬ ፡ ዛቲ፡ ብሥራት ፡ እንተ ፡ ባቲ ፡ ደለዎሙ ፡ ለሰብእ ፡ ከመ ፡ ይኩኑ ፡ ታቦተ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወማኅደረ ፡ መቅደሱ ፡ ወኮነ ፡ ሎሙ ፡ ዘይበዝኅ ፡ ክብር ፡ በክብረ፡ ዝንቱ፡ ዐበይ ። ኦ፡ ለዝንቱ፡ ክብር ፡ ዐቢይ ፡ ወኂሩት ፡ ዘእንበለ ፡ መሥፈርት ፡ ወዜነወነ ፡ ካዕበ ፡ ተሣህሎተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልዑል ፡ ለደቂቀ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፤ ወሠርዮ ፡ ጌጋይ ፤ ወአብጥሎ ፡ ሡነኔያት ፤ ወሰቢረ ፡ ሦክ ፡ መስሐቲ ፡ ጸላኢ ፤ ወድክመተ ፡ ትዝኅርቱ ። ወዓዲ ፡ ዘበቍዓነ፡ ቦቱ ፡ በጸውዖትነ፡ ውሉደ ። ወፍግዓ ፡ ዘድልው ፡ ለነ ፡ ውስተ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፤ ወሕይወት ፡ ለዝሉፉ ፤ ወናሁ ፡ ተበየነ ፡ ትእምርቱ ፡ ወምክንያተ ፡ ስሙ ።

ትርጓሜ ፡ የዚህ ፡ የከበረው ፡ ወንጌል ፡ ዓላማ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ከሥጋችን ፡ ስለ ፡ መወሐዱና ፡ መንፈስ፡ ቅዱስ ፡ በእኛ፡ በውስጣችን ፡ ስለ ፡ ማደሩ ፡ መሰበክ ፡ ነውና ፡ ሰዎች ፡ የእግዚአብሔር ፡ ታቦት ፡ የመቅደሱም ፡ ማደሪያ ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ ተገቢነትን ፡ ያገኙባት ፡ ይህች ፡ የምሥራች ፡ ምንኛ ፡ ታላቅ ፡ ናት! በዚሁ ፡ ታላቅ ፡ ክብር ፡ መጠን ፡ የበዛ ፡ ክብር ፡ ሆኖላቸዋልና ፡ ለዚሁ ፡ ታላቅ ፡ ክብር ፡ ሥፍርም ፡ ለሌለው ፡ ቸርነት ፡ አንክሮ ፡ ይገባል! ከዚሁም ፡ ሌላ ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሰው ፡ ልጆች ፡ ምሕረት ፡ ማድረጉን ፡ የኃጢአትን ፡ ሥርየት ፡ መስጠቱን ፡ ሡነኔን ፡ አጥፍቶልን ፡ የአሳች ፡ ጠላትን ፡ እሾህ ፡ መስበሩንና ፡ የሰይጣንን ፡ ትዝህርት ፡ ማድከሙን ፡ ነግሮናል ። ዳግም ፡ በምን





ጠቀምበት ፡ ረገድ ፡ እኛን ፡ ልጆች ፡ ማለቱን ፡ በሰማያት ፡ ስለ ፡ አዘጋጀልን ፡ ተድላና ፡ ስለ ፡ ዘለዓለማዊ ፡ ሕይወት ፡ ሁሉ ፡ ነግሮናል ። እንግዲህ ፡ ዓላማውና፡ የስሙ ፡ ምክንያት ፡ እነሆ፡ ዕውቅ ፡ ነው ።” ብለውታል ። ኤፌ ፡ ፩ ፡ ፲፫ ፡ ፲፬ ።